# ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልዎ

« ልትሆን ትችላለች ላትሆንም ትችላለች ። ይህማ ያሻማል- እታገኝ ። »በቀለ ራሱን ነቀነቀ ።

እንደወጣች ለአበበ እንደገና ደወለና « በላ ጓደኝነትህን እንየው ። ድቲክቲቭ እንብቤአለሁ ትላለህ» ብሎ በጉን እንዲያጣራለት ተመሣጠሩ ።

ማምሻውን በቀጠሮ ከዚያው ቡና ቤት ተገናኙ ፕላን አወጡ ። አበበ በአፈጻጸሙ እምብዛም የሚቸገር አልመሰለም ።

በቀለ ሊሄድ ዋዜማ ፤ ከነጻነት ጋራ ከመኪና ውስጥ ሆነው ቡና እየጠጡ የሚያመጣላትን ዕቃ ሲያማርጡ « ወር ? ወር ሙሉስ ረዘመ በቅዬ » አለችው ።

« አሁን ይህችን በመሰለች ንጽሕት ፍጥረት ላይ ምን አሰብኩ እባካችሁ ? የመጨረሻው አስቀያሚ ጭራቅ ነኝ » በቀለ ክፉኛ ተጸጸተ ። የጭንቅላቱን ቆሻሻነት ተጸየፈው ። የኦቴሎ ቍራኛ ። ሲሰነባበቱ በዐይኗ ዕንባ ችፍፍ አለባት ። በመሐረሟ እያመጠጠች ፤ « በል ደኅና ሁን ልቅበጥ ደግሞ እንዳትል ። አይዞህ ለየሱስዬ ደግሞ እጸልይልሃለሁ » አለችው ። መመርመር ቀርቶ በሄደችበት ዝር እንዳይል ለማስጠንቀቅ ማታ አበበን ቢፈልገው አጣውና ጢቱን በረረ ።



ምዕራፍ ፯ ።

# የጠወለገች አበባ ።

ለበቀለ አንድ ወር ጊዜ እንደዚያ ረዝሞበት አያውቅም ። ጢት በተነሣ ቍጥር አንዳንድ ቀን ቢቀንስለት የማይገባደድ ዘለዓለም መሰለበት ። የፓሪስ ከተማ ሰለቸው ። ሮም አስጠላው ። አተላ ቅራሪ ሆነችበት ፤ ያማረው — ያሸበረቀው — አውሮፓ ምኑም — ምኑም አላስደሰተውም ። ልቡ ከዚህ ነበር ። ግን እንዳያልቅ የለም አልቆ ተመለሰ ። አቤት ጥድፊያው ! ሻንጣውን በራፍ ላይ ለዘበኛ ጥሎ መኪና አስነሥቶ ወደ ቤቷ ከነፈ ። እንደ ጨው ሟሙታ ፥ እንደ መንፈስ ተሰውራ የምትቈይ መሰለው ። ቅቤ ተቀብታ አገኛት ።

« ሰው ሁሉ የት ሄደ ? » አለ ፤ ጭር ያለውን ግቢ ተመልክቶ ፤

« ሸርሽር ሄደዋል » ስትል መለሰችለት ።

« አንቺ ለምን አልሄድሽም » ።

« አላሰኘኝም » ከርሷ ክፍል ውስጥ ተቀመጡ ።

« ደኅና ነሽ ነጻነት »

« ደኅና ነኝ ። አንተስ ደኅና መጣህ ? »

« ተይኝ መምጣቴንስ መጣሁ ። አቋርጬ መምጣት ነው የቀረኝ ነጻነት » የእፎይታ ፈገግታ ሊያሳያት ሞከረ ።

« አቤት ? » አለች በፈዘዘ ድምፅ ። ትክ ብሎ አስተዋላት ። በርግጥ ፈዛለች ። እንደቤቷ ልዩ ፤ ቃና ድካም ፣ ሰቀቀን ፣ አዘኔታ ? የሆነ ነገር አለ ።

« ነጻነት ! ምን ሆነሻል ? »

« ምንም »

« በመምጣቴ ደስ አልተሰኘሽም እንዴ ? »

መልስ አልሰጠችውም ።

« ነጻነት ! ነጻነት ! » ከነበረበት ተነሣና ከጕኗ ቆሞ አለ ። ጨነቀው ። እንደዚህ በጠወለገ መንፈስ ሳይሆን በደኅና ስሜት ሊያገኛት ነበር ያሰበው ።

« ነጻነት »

« አለሁ ምን ዐሥር ጊዜ ትጠራኛለህ ። የምትናገረው እንዳለ ተናገር » ቍጣ አልነበረም ።

አገጯን ቀና አድርጎ በዐይኑ አቆላመጣት ። እስ ዋም ለመጀመሪያ ጊዜ ፈዛ ተመለከተችው ።

« እንዴት እንደምገልጠው አላውቅም » አለ በቀለ በለሰለሰ አንደበት « ትዝብት ይሰማኛል ፤ ሚስቴ ሁኚ አልልሽም ነጻነት ። ባልሽ ልሁንም አልልም ። እንጃ



እኔ ላንቺ የተገባሁ አድርጌ ራሴን አልገምተውም ። የምመካበት ቢኖር ስላንቺ ያለኝ ፍቅርና ታማኝነቴ ነው ። የምትቀበይው ቢሆን እኔነቴን በአገልጋይነት በፍጹምነት ልስጥሽ ። ሚስት ሳይሆን እመቤቴ ሁኚ ። ይኸው ነው የምለው ነጻነት »

ግንባሯን ከመዳፏ ላይ በማንተራስ አንገቷን ደፍታ ጥቂት ከቆየች በኋላ «የለም» ስትል ራሷን ነቀነቀች ፤ አስባ የወሰነች ይመስላል ። በቀለ ጆሮውን ማመን አቃተው ። መብረቅ ነው ። የግድግዳው ድምፅ ነው ። ወይስ በመካከላችን ጭራቅ መንፈስ አለ ? የነጻነት ድምፅ ግን ሊሆን አይችልም ።

« ነጻነት » አለ እንደ ገና በጣር ድምፅ ።

« አልችልም በቀለ ። አልችልም ። እመቤትም ሆነ ምንም ልሆንህ አልችልም — አልችልም » እንደ ዛር አን ዘፈዘፋት ። በቀለ ግራ ገባው ።

« እንዴ ! እንዴ ? አላምንም ። ጨረቃ ላይ ቤት አል ሠራንም ? አልተፋቀርንም ? በፍቅር አላመንም ? ነጻነት ምነው እንግዳ ሆንሽብኝ ? » መዝዝ ያለ ስሞታ ነበር ።

« የምን ማፍቀር ! እንደ ሰው ባትመስለኝ አመለ ከሁህ እንጂ ። ምነው እንደሌሎቹ ደንዳና ሆኜ ለመኖር ብችል ኖሮ ! እንደሌሎቹ እንዳልሆን አድርገህ ተውኸኝ። ባንተ አልፈርድም ። ምናልባት በፈጣሪዬ ተረግሚያለሁ ፤

ግን ምን በደልኩት ? » እሮሮዋ የርሱን ጉሮሮ ተናነቀው ።

« ምን መዓት ታወሪያለሽ ነጻነት፤ምን በደልኩሽ ? »

« ምን በደልከኝ አልኩህ ? »

« ታዲያ ጋብቻችንን የሚከለክል ምን ነገር አለ ? ቀለበቱ ተመልሷል ። ቦታ ገዝቻለሁ ። የምንሠራው ቤት ዩታየኛል ። ጨረቃንም ባልሰጥሽ እስከዚህም ድረስ ኑሮዋችን መጥፎ አይሆንም ። ግዴለሽም » ትከሻዋን አቅፎ እሹሩሩ አላት ።

« የምናገረው አማርኛ ነው ። አላገባም ። አንተን አላገባም ። ሌላም አላገባም ። ዓለም ይስፋ ። እጠፋላችኋለሁ ። ኧረ እንዲያው ብሞትስ ምኑ እንዳይቀር ! በቀለ እባክህ ተወኝ ። እባክህ ጥፋልኝ » ድንገት ከጉያው ሽጉጥ ብላ ዕንባዋ በአራት መንታ [ይወርድ ጀመር ። ሰውነቷ የሚረግፍ እስኪመስል ድረስ] አንሰቀሰቃት ። በቀለ የሚያደርገውን አጣ ። ሊያባብላት አልቻለም ። ለማስረዳት መሞከር ከንቱ ነበር ። ምንስ የሚያስረዳው ነገር አለ ። ካልፈለገች አልፈለገችም ማለት ነው ። ፍላጎቷን አይፃረርም ። ግን ለምን አልፈለገችም ? እንደ ተሰማው አሁንም ታፈቅረዋለች ። ሰው እንቆቅልሽ ነው ? ተንሰቅሰቃ ተንሰቅስቃ የደከመ ሰውነቷ ዘንፈል ሲል ከአልጋው ላይ አጋድሟት ወጣ ።



« ምንድናችሁ ሴቶች ? አይገባኝም » በበነጋው ጧት ሥራ እንደ ገባ እታገኘን አዋያት ።

« ምናልባት በጣም ስለምታፈቅርህ ! ወይም እንደም ታፈቅራት ስለምታውቅ ይሆናል » አለችው ታሪኩን በጥሞና ካዳመጠች በኋላ ።

« ሎጂኩ አይገባኝም » አለ በቀለ ።

« አንተስ ሳማክርህ እንደዚሁ አላልከም ? » ስትል ጠየቀችው ።

« ታዲያ ልክ አለመሆኔ ወዲያው ገባኝ ! »

« ለመሆኑ ልጃገረድ ናት ? » አጠያየቋ የጥርጣሬ ዐይነት ነበር ።

« እንዴ ! እኔ ምን አውቃለሁ » መጠየቋ አስገረመው ።

« ምናልባት ምክንያቱ እርሱ ሊሆን ይችላል » እታገኝ አሰበች ።

« ምኑ ? ልጃገረድ መሆኗ ? » በቀለ በመደነቅ ከት ብሎ ሣቀ ።

« አለመሆኗ ። በቀለ ወንድና ሴትኮ አንድ ዐይነት አያስቡም ። ሴቶች የተለየ ስሜት ፣ የተለየ ተፈጥሮ አለን ። ለፍቅራችንም የተለየ ግምት እንሰጠዋለን ። ለምሳሌ ፣ ታፈቅራታለህ ። ታፈቅርሃለች ። ልጃገረድ እንዳይደለችስ ? አለመሆኗን የደረስክበት ጊዜ ፍቅርህ የሚ

ቀንሰባት ፥ ማምትህ ዝቅ የሚልባት ይመስላታል ። ይህ እንዲሆን አትፈልግም ። ፍቅራችሁን ከሚያጠወልግ ከዚያ ገለጣ ለመዳን አለማግባትን መርጣ ይሆናል » እታገኝ ከቢሮው ልትወጣ ቃጣች ።

« ቆይ እንጂ ። ታዲያ እንደኔ አስተያየት ተሳስታለች ። በጣም ተሳስታለች ። ያፈቀርኩትኮ ድንግልናዋን አይደለም ። ድንግልና ከተፈለገ በደርዘን ይገኛል »

« ቢሆንም ሴቶች ስለድንግልናቸው ከፍተኛ ግምት አላቸው ። ይህንንም ክቡር ነገር ለሚወዱት ቢያበረክቱት ደስ ይላቸዋል ። ደግሞም መጥፎ አይደለም » አለችው እታገኝ ።

« ነው ። በሌላው አንጻር ደግሞ በጭውነት ስሜት፤ በፍቅር ጥበቃ ሳይሆን ለባል ማግኛ ሲባል ክብርናን ማስቀመጥ አንድ የሸርሙጥና ዝንባሌ ያለበት ይመስለኛል። ማለት ደንበኞቹ አሮጌ ዕቃቸውን ቢቸረችሩ እነዚህ ደግሞ አዲስ ዕቃቸውን በከፍተኛ ዋጋ ለመሸጥ ይጠባበቃሉ ። »

« መላ ቅጥ ያሳጣህኮ ይህ አጉል ፍልስፍናህ ነው በቀለ » እታገኝ ራሷን ነቀነቀች ።

« አዎ አንዳንድ ጊዜ ያቃዠኛል ። እንጂ ገና ብዙ ሳልቃዥ እቀራለሁ ? ምን ላድርግ ትይኛለሽ እታገኝ ? ምክንያቱ እንደምትይው ከሆነ ክርቧንቷ በተቀር ስለድ



ንግልናዋ ደንታ እንደሌለኝ ፍርጥ አድርጌ እነግራታለሁ ። »

እታገኝ አዲስ ሐሳብ እንደ ተገለጠላት ከበሩ ላይ ስትደርስ ዞር አለችና « ለመሆኑ ያንን አበበ የምትለውን ሰውዬ አግኝተኸዋል ? » ብላ ጠየቀችው ።

እርሱም አንድ ነገር ነው አለ በቀለ በሆዱ ። ረስቶት ነበር ። እታገኝ ምን ስምታ አስታወሰችው ? ወዲያው ደወለና አገኘው ።

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ « ታዲያስ ከመሄዴ በፊት ያጫወትኩህ ጉዳይ ከምን ደረሰ ? » አለና ጠየቀው ።

« እርሱማ ተያይዟል » አለ አበበ ።

« ምኑ ? » መልሶ ጠየቀው ።

« ከዚሁ ላይ ብንተወው ይሻላል ። ደኅና ሁን ሥራ አለብኝ » አበበ ቴሌፎኑን ከጆሮው ላይ ዘጋበት ። እንዴ ? ሰው ሁሉ ምን ነክቶታል ። ጭንቅላቱ ልክ ነው ? ነጻነት ተለውጣ ቆየችው ። አበበ በድንገት እንደ ጠበኛ ቴሌፎን ከጆሮው ላይ ዘጋበት ። ኧረ አነጋገሩም አልጣመወም ነበር ። ቀጥሎ ለነጻነት ደወለ ። ሥራ አልገባችም ። በቀለ ተቅበዘበዘ ። አበበንም ሊያገኘው አልቻለም ። ሰሞኑን ዕረፍት ሄደ ተባለ ።

ከሁለት ቀን በኋላ አላስችለው አለና ከቤቷ ሄዶ ጠየቀ ። የለችም ። የት ሄደች ? እነርሱም የማያውቁ

ወይም እያወቁ የሚደብቁት ጉድ ያለ ይመስል አደባባብ
ሰው ሸኙት ። አንደኛው ወንድሟ ዘመድ ጥየቃ ወደ
ውጭ አገር ሄደች አለው ። የት? እንጃ ። እኅቲቱ ደግሞ
ወደ ጠበል ነው አሉት ። ምን እንዳመማትና የት ጠበል
እንደ ሄደች ቢጠይቅ አቀርቅረው ወለል ወለሉን ተመ
ለከቱ ። ባንድ በኩል ጸጥታው ቤቱን የኀዘን ቤት
አስመስሎታል ። በመምጣቱና በጥያቄውም አለ መደ
ሰታቸውን አኳኋናቸው ይገልጥ ነበር ።

ምነው ዓለም በድንገት እንደዚህ ተለዋወጠበት?
ከፍቅሩ ፣ ከናፍቆቱ ፣ ከሰቀቀኑ ጋራ የነገሩ ዕንቆቅልሽ
ሕሊናውን በጠበጠው ።

በጨለማ ክፍል ውስጥ እንደ መጓዝ ዐይነት ነበር ።
በዚህም በዚያም ግንባሩ ከግድግዳ ጋራ ይጋጫል ። በቀ
ለንም በአእምሮው ውስጥ ልዩ ልዩ የሐሳብ ጭራቆች
እየመጡ ይደበድቡት ጀመር ። ሰላምና ጸጥታ ጓዛቸውን
ጠቅልለው ከሰውነቱ ወጡ ። የተተካበት የሕውከት ማዕ
በል በሳምንት ውስጥ ተፈጥሮውን እያንኰታኰተ
ጣለው ። ከሥራው ቀረ ። ቢሄድም ዋጋ አልነበረውም ።
አይበላም ። አይተኛም ። ቁጭ ብሎ ሲጫወትም ስለ
ነጻነት መቃዠት አምጥቶ ነበር ።

አካባቢና አየር መለወጡ ትንሽ ይረዳው ይሆናል
ተብሎ በዘመዶቹ ውትወታ ለጥቂት ጊዜ አሥመራ ሄዶ



እንዲቆይ ተደረገ ። ዋና አለኝታቸው ነበር ። ተሰባብሮ
እንዲወድቅ አልፈለጉም ። በመካከሉ ነገሩን እንደሚያ
ጣሩለት አጽናኑት ። እርሱ ግን በበኩሉ እታገኘን በጥ
ብቅ አደራ አላት ። «ምንም ዐይነት መሪር መርዶ ይሁን
እንዳትደብቂኝ ። አንድ ጊዜ ብወጣው ይሻለኛል ።
ወዲያው በቴሌፎን እንድታስታውቂኝ - እሺ » የሚገኝ
በትን ቊጥር ሰጣት ።

የአሥመራ ስንበታው አንድ ረጅም ሕልም ነበር ።
ምን እንዳደረገ ቀርቶ መኖሩን ስንኳ በሚገባ የማያስ
ታውስበት ጊዜ ነው ። አብዛኛውን ከዐልጋው ላይ
ተጋድሞ ይውላል ። መቅበዝበዙ ሲሻለው መፍዘዝ
ተተካበት ። ነፃነት ይኸኔ የት አለች? ምን ታደርጋለች?
ምን ታስብ ይሆን? ስትስቅ ትታየዋለች ። ስታለቅስ ያያ
ታል ። አብረው ያለሙት ፣ በጠራ ጨረቃ ሥር ተቀ
ምጠው የተጫወቱት--- ሐሳቡ ከአዲስ አበባና ከነጻነት
ትዝታ ጋራ ተጣብቆ አልላቀቅ አለ ። እኅቱ በብዙ ረገድ
ልትረዳው ሞከረች ። ስሜቱ ስለሚገባት እንደርሱው
ተጨነቀች ። ምናልባት ተብሎ ልጃገረድ ይመጣለት
የጀመረውም አሥመራ ሳለ ነበር ። እንዳቸውንም አላያቸ
ውም ። ዐይኑ ተጋርዶበታል ።

አንድ ወር ከሳምንት ያህል እንዳለፈ -ርሱ ግን
ቀን ቈጠራውን ትቶታል- የሚጠብቀው ቴሌፎን ከአ

ዲስ አበባ ተደወለለት ። አቤት መቍነጥነጥ ! አካላቱ ተንቀጠቀጠ ። ትንፋሽ አጠረው ። እታገኝ ነበረች ።

« አሎ አሎ ይሰማሃል ? » አለችው ።

« አዎ ! እሰማለሁ ምንድነው ንገሪኝ » ቍጣ ነበር ።

« አሎ ! በቀለ ደኅና ነህ ? »

« አፋ!ንገሪኝ ነው የምልሽ ምን ሐተታ ማብዛት ነው»

እታገኝ ጥቂት ሴኮንድ ዝም ብላ ቈየችና ተምጦ እንደ ወጣ ትንፋሽ « ነጻነት ልትዳር ነው » አለችው ።

« ኖ- ኖ ! » ጩኸቱ ቤቱን አደባለቀው ።

እኅቱ መጥታ ከአጠገቡ ቆመች ። በትእዛዝ ያስቀረው ይመስል « ኖ ! » አለ ወደ ርቢ ዞሮ ራሱን እየነቀነቀ፤ ውሸት ነው የሚል መልስ የሚጠብቅ ይመስል እኅቱን በመጨነቅ ተመለከታት ። ለማጽናናት እጅዋን ብቻ ከትከሻው ላይ ጫን አደረገችው ። እውነትነቱን መዋጥ አቃተው ። ከውስጥ ዕንባና ልቅሶ ይተናነቀው ነበር ።

« አሎ - አሎ ! » አለች እታገኝ እንደ ገና ።

« መቼ ነው ርሱ ? » በምሬት ጥርሱን አገጠጠ ።

« ነገ እሑድ ነው ። ትመጣ እንደሆን አንተም ለሠርጉ ተጠርተሃል » ፊዞ እንደ ዕብድ አንከተከተው ።

« መጣሁ » አለና ቴሌፎኑን አስቀምጦ ወደ ውጭ ተፈተለከ ።



« የት ነው የምትሄደው » አለች እኅቱ ከወደኋላው እየሮጠች ።

« አዲስ አበባ »

« አውሮፕላንኮ የሚበረው ነገ ቢት ነው » ። ቀኑ ዐርብ ነበር ።

«ይህ ጭንቅላቱ። ወይኔ አእምሮዬ ልክ አይደለም ። አሥመራ አዲስ አበባ ከቢሮው እንደ ፒያሳ ወጣ ብሎ የሚኬድበት መስሎታል ። ተመልሶ በሳሎኑ ላይ ዘንፈል አለ ።

## ምዕራፍ ፳ ።

## ጠፍ ጫሬቃ ።

ትዳሟ ቢት በቢሮው ሳሎን ተቀመጠና ሲጋራ እቀጣጥሎ ታሪኩን በዝርዝር እንድታጫውተው እታገኝን ጠየቃት ። መንፈሱ ትንሽ ተረጋግቶ ነበር ። ድካምም ነው ። እኅቱ እስከ እኩለ ሌሊት ስትመክረው አደረ ነበር ። ነገሩን እምብዛም አያስታውሰውም ። ነገር ግን ወደ አዲስ አበባ ሲበር አንዳንድ ጊዜ አእምሮው እየሳተ ቢያስቸግረውም በጥሞና አስቦ እውነትነቱን ወደ ማመን ደረሰ ። ሺንፈቱን እንዳወቀ ጀኔራል መቅበጥ በጡ ተገ አለለት ። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ያገረሽበታል ።

« ምኑን ላጫውትህ ? » አለችና እታገኘ ጠየቀችው ።

« እረ ለመሆኑ ማንን ነው የምታገባው ? »

እታገኘ በመልሷ ጥቂት አመነታች ። አነጠሰችና በመሐረብ ውስጥ « አበበን » አለችው ።

የነጻነት ተለውጦ መቁየት ፣ የአበበ ቴሌፎን አመላለስ ፣ ከዚያም የሁለቱ በአንድ ጊዜ መሰወር በመካከላቸው አንድ ጉድ እንዳለ የጥርጣሬ ፍንጭ ሳይቋጥር አልቀረም ነበር ። ግን ጋብቻ —

« ካልጠፋው ወንድ አበበን ? »

በአዘኔታ ራሱን ነቀነቀ ። ትዝብቱ ከፋኛ ተሽማቀቀ ። « አዬ ሴት ! አዬ ሴት ! ደግሞ አመለከሁህ ! አንተንም ሌላም አላገባም እጠፋለሁ አፈር ድቤ » ድምፁ እየጋለ ሄደ ። ትፍ ማለት ቃጣው ።

« እውነት ነው »

« ምኑ ነው እውነት ? »

ማንባሩን ኮስተር [አደረገው ።

« የነገረችህ አብዛኛው »

« ጥብቅና ቁሚላት » ገላመጣት ።

« ማትር ነህ በቀለ። ነገር አይገባህም ። እንደ ሰማሁት ከሆነ ተሳስታ ወይም አጥፍታ ይሆናል ። ግን ኀጢአተኛ አትመስለኝም ። »



« እንሰማዋ !» ሲጋራ አቀጣጥሎ ጢሱን ወደጣራ ያው ያቦን ጀመር ።

« ነገሩን በተቻለኝ መጠን ተከታትዬዋለሁ ። አንተ ወደ ውጭ አገር እንደሄድክ ፀሐይ በምትባለዋ ጓደኛዋ አማካይነት አበበ ይተዋወቃታል ። በመኪና አብረው ሽርሽር ይሄዳሉ ። ነጻነት አበበን የፀሐይ ወዳጅ አድርጋው ነበር ። መጠጥ ይጠጣሉ ፤ ከዚያ በኋላ የሆነውን በትክክል አታውቅም ። »

መጠጥና ነጻነት ? ይገባዋል ። አንድ ቀን አንዲት ጠብታ ቢርሙጥ አቅምሷት ቤቷ ተሸክሞ እንዳስገባት ያስታውሳል ። ያቺ አቃጣሪ ሸርሙጣ ! አለ በሆዱ ።

« ግን ሽርሽር ምን አስኬዳት ? ያው እግሬ ወጣ ሲል ወጣ መሆኑ አይደለም ? » ጥያቄው ራሱን ጭምር ነበር ።

« ልጂ ናፍቆትምኮ ያቅበዘብዛል ። አንተ የለህም ። ብቸኝነት ሲሰማት ትንሽ የሚቀላት መስሏት ይሆናል ። በዚህም በዚያም ፤ ይህ እንደ ሆነ ወዲያው በራ ጠፍታ ከደብረ ሊባኖስ ነው ተይዛ የመጣችው ። እመነኩሳለሁ ብላ ሰማይና ምድሩን ታደባልቀው ነበር አሉ ። በዚህ ጊዜ ነው አንተን እንቢ ያለችው ።»

« ከዚያ በኋላ አበበን ወደደችና ሐሳቧን ለወጠች ?» አነጋገሩ የሽሙጥ ነበር ።

« የለም» አለች ታገኝ «በዚያው ቅሪት ሆና ተገኝች ።
የቤቱ ሰብን ስም ከጉድ ለማዳን ለልጁም ሲባል ሁለቱ
ንም አስገደዷቸው እልሃለሁ ይኸው ነው ባጭሩ ። »

በቀለ ዐይኑን ጨፈን አደረገና ራሱን በቀስታ አወ
ዛወዘው ። « አይገባኝም ። ምኑም --- ምኑም አይገባኝ ።
አበበ እኔን ? ዋ - ዋ ! » የተነጋገረው ከራሱ ጋራ ነበር ።
ዐይኑን እንደ ገጠመ ያንቀላፋ መሰለ ። ሰው አስጠላው !
መረረው ።

« ከሥርጉ ትሄዳለህ ? ሙት ተጠርተሀል ! »

በቀለ ከእንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ ድንገት ቀና አለና
« አንገቱ እስኪበጠስ ነውና እንዲያውም የምዘፍነው »
ሲል ሣቁን ለቀቀው ። እንደ ዕብድ ደግሞ ደጋግሞ ተን
ከተከተ ። በምን ለምን እንደ ሣቀ አያውቀውም ! የመገ
ረም ጣቅ ነበር ። ዓለም የጠጣ ድራማ ሆነችበት ።

የሠርጓ ቀን እሑድ የሦስተኛው አፍሪቃ ዋንጫ
ውድድር በቀ. ኃ. ሥ. እስታዲየም የመጨረሻው ጨዋታ
የተፈጸመበት ዕለት ነበር ። በቀለ የአፍሪቃ ዋንጫ
ቀርቶ የጽርሐ አርአያም አክሊል ቢሆን ስለኳስ ጨዋታ
ደንታ አልነበረውም ። በዘጠኝ ሰዓት ላይ ልብሱን ለባበ
ሰና ወደ ፒያሳ ወጣ ። አይቶ የማይጠግበው ሌላ ነገር
ነበር ። አሁንም ምናልባት ለመጨረሻ ጊዜ ማየት አለ



በት ። ሙሽራዪቱን - የልቡን ሙሽራ - እንደ ባዳ - እንደ
ማንም ተራ ሰው በፒያሳ በረንዳ ላይ ቆሞ ሊያያት ?

ፒያሳው ካለወትሮው ጭልል ብሎ ነበር ። አብዛኛ
ውን እሑድ ሞልተው የሚታዩት ሲኒማ ቤቶች በራፋ
ቸውን እንደ ከፈቱ ናቸው ። ሕዝቡ ወደ ኳስ ሜዳ ወር
ዷል ። አልፎ አልፎ ግን ሰዎች በአንዳንድ ትራንሲስ
ተር ራዲዮ ዙሪያ ከምችች ብለዋል ። በየስፍራው የሚ
ሰማው የራዲዮ ድምፅ ነው ።

አቤት እትዬ ማርያም ! --- ጊላ በአስደናቂ ሁናቴ
ያዘ ። ለአዋድ ሰጠው --- አዋድ ለተስፋዬ --- ተስፋዬ
ለሉቺያኖ - ሉቺያኖ ለመንግሥቱ --- መንግሥቱ --- ለኢ
ታሎ --- ኢታሎ ለግብ ! ግብ ጠባቂው ያዘ ። ከኳስ ጋራ
አብሮ የሚከንፍ የሚመስለው የተናጋሪው እንደበት
ከፍና ዝቅ ባለ ቊጥር በየራዲዮው ያቀረቀረው አድማጭ
አብሮ ይቁነጠነጣል ። አንዳንዱም ራዲዮው መታ ! ሲል
እግሩን የሚያነሣ አለ ።

ሰው በስሜት የሚመራ ጦጣ ነው ልበል ? ኳስ ወዲ
ህና ወዲያ ተሯሯጠችና ይህንን ያህል መወራጨት ፣ ይህ
ንን ያህል መቦረቅ ምንድን ነው ? አለ በቀለ በሐሳቡ ።

ለወትሮው አላሳልፍ የሚሉት ሊስትሮች ዛሬ ሥራ
ቸውን ዘንግተው ዜናውን ብቻ ይከታተላሉ ። አንዱን
በመከራ ጠራና ከሳባ ቤተ መጻሕፍት በራንዳ ላይ ከተ

ደረደሩት የሊስትሮ ወንበሮች ካንዱ ላይ ተቀመጠ ።
ሊስትሮው ግን በብሩሽ ብቻ ነካ ነካ አድርጎለት ያኔውኑ
ዐሥር ጊዜ ግብ ገባ ? እያለ በመጠየቅ ጥሎት ሄደ ።

በቀለ እግሩን አጣመረና ሲጋራ አቀጣጥሎ ይጠብቅ
ጀመር ። የአዲስ አበባ ሠርገኛ ሁሉ መተላለፊያው ፒያሳ
ነው ። እነርሱም መምጣታቸው አይቀርም ።

በዐሥር ሰዓት ላይ ሠርገኞች መምጣት ጀመሩ ።
በማርቸዲስ ፥ በኦፔል ፥ በችቭሮሌት ፥ በሚሊቸንቶ ፥ በሰ
ይቸንቶ ፥ በአንድ ሰዓት ውስጥ ሰባት ያህል ቈጠረ ። እያን
ዳንዱ የሙሽራ አውቶሞቢል ብቅ ባለ ቍጥር በቀለ ዐይኑ
ተጐልጕሎ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ ያተኵር ነበር ። በሐ
ሳቡም ይተቻል ። ስንቱ ነው ለፍቅር በፍቅር የተጋባው ?
አሁን ይህቺ ወዳው ነው ? ወይስ ሌላ ምክንያት አላት ?
ያችን የመሰለች ቆንጆ ከጐኑ ያስቀመጠው ያ ሙሽራ
አሁን ምን ያስባል ? ነገ ሬቡዕ ስንቱ ይፋታል ? ስንቶቹ
በጸጸት ይኖራሉ ?

የነጸነት ዕጮኛ የነበረው ተሾመም ከአንዲት ወፍ
ራም ልጅ ጋራ ተሞሽሮ ሲያልፍ በቀለ ገርሞት ሣቀ ።

በመጨረሻ በግልጥ ቸቭሮሌት መጡለት ። በአበበ
ግዙፍ ሰውነት በሩቁ አወቃቸው ። ከተቀመጠበት ተነ
ሣና ወደመንገዱ ዳር ጠጋ ብሎ ቆመ ። በዐይነ ርግቡ
ሥር ያንን የሚያመልከውን ገጥታዋን ለቅጽበት አየ ። አይ



ታው ፈገግ ያለች መሰለው ። በዐይኖቿ ዕንባ ችፍፍ
ሲል ያየም መሰለው ። ዐይኑ ነው የሚጫወትበት ? ብቻ
ለሴኮንድ አንድ ዐይነት የተራት ደስታ ተሰማው ። የመ
ንፈሱ ንግሥት አሁን የፒያሳው እመቤት ናት ። ሁሉ
ያያታል ። ሁሉም ያደንቃታል ። በዙፋን ላይ ተቀምጣ
እንዳያት ያህል ነው ።

ሙሽሮቹ አለፉ ። አጃቢው ተከተለ ። በባንክ ቤት
ተጠምዝዘው እስኪጠፉ ድረስ አንገቱን አስግጎ በዐይኑ
ተከተላቸው ። ያን ጊዜ ነው ጀንበር የጠለቀች የመሰ
ለው ። ቀስ በቀስ የመንፈስ ጨለማ ዋጠው ። በቃ ። ተከ
ተተ ። አለቀ ደቀቀ ። ሕይወቱ ባዶ ሆነበት ። አለኝታ
የለም ። የሕልውና ምክንያት የለም ። ምንድነው የኔ
ሕይወት ትርጓሜ ? ብሎ ራሱን ጠየቀው ። ብቻውን
ሲነጋገር በአጠገቡ የሰሙት እየገላመጡ አስተዋሉት ።
ግምታቸው በቀኑ ሰክሯል ነበር ። እርሱ ግን ግድ አል
ነበረውም ።

ሙሽሮቹ በሄዱበት አቅጣጫ ደመ ነፍሱን እንደ
ተራመደ ኪንግ ጆርጅ ቡና ቤት ዘው ብሎ ገባ ።

ከባንኮው ላይ ተደግፎ « ደብል ጂን » አለ ።

ብዙ የቀን ሰካራም ማስተናገድ የለመደው ባሪስታ
እምብዛም ሳይደነቅ አንቈረቈረለት ። በቡና ቤቱ ውስ

ጥም ያው የኳስ ጨዋታ ትራንሲስተር ራዲዮ አለ ። በተለይ እርሱን ያስተዋለው አልነበረም ።

ጭንቅላቱን ወደኋላ መልሶ አንድ ጊዜ ጨለጠው ፤ ደረቱን እያቃጠለ ሲወርድ ደስ አለው ።

« ጋዳሚት ! ድገመኝ » ሲል አዘዘ ።

አሁንም ባንዴ ተጐንጨለት ። ሰውነቱ እየጋለ ሄደ ። ልጂ ፈውስ አይደለም እንዴ ? አለው ራሱን በራሱ። ብርጭቆውና ሰዎቹ ከዐይኑ ሥር ድብዝዝ እያሉ ሲሄዱ ሰውነቱ ይቃጠል ገባ ። ትዙሳት ተለቀቀበት ።

« በምን ወደድኳት ? » የቁጭትም የንዴትም ጥያቄ ነበር ። ሁለት ዓመት ሙሉ ራሴን ለርሷ አሳልፌ ሰጠሁ ። በውን ቀርቶ በሐሳቤ ሴት ሳልነካ ። ለምን ? ስለርሷ ያለኝን አለኝታና ፍቅር የማረክስ መስሎኝ ነዋ ! ምናልባት ገረዱ ለማጠብ እስክትጠየፍ ድረስ አንሶላውን ያበላሸበትን ጊዜ በጸጸት አስታወሰ ።

« ይህ ሁሉ በከንቱ ! » ሲል በሐሳቡ የነጻነትና የአበበ ጫጉላ ቤት ጭራቅ ሆኖ መጣበት ። ያንን ጠረንገሎ ሰውነቱን ከለስላሳው ጭኗ መካከል ሲያስገባው ታየው ። - እግዚኦ ! አለ አፍ አውጥቶ ። ሲያዳሽቃት ! አለ ዝቅ ባለ ድምፅ ። በዚህ ጊዜ የራሱም ስሜት ተቀሰቀሰበት ። የት እንቀላፍቶ ኖሯል ? ። መጠጡ ነው ? እሱዋን ለመበቀል ነው ? አልምርም ! እኔም ወንድ ነኝ ።



ደግሞ ለምኑ ነው ? ፍቅርን ከመካከሉ አንሥቶ ዐይንን ከጨፈኑ ቀዳዳ ፤ ቀዳዳ ፤ እንጥልጥልም እንጥልጥል ነው— እኔም ጫጉላ ቤት አላጣም አለና ከፍሎ ወጣ ።

ጊዜው ወደ ዐሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ይሆናል ። እየተንገዳገደ መንገዱን አቋረጠና ወደ እቴጌ ሆቴል በሚወስደው መንገድ መጀመርያ ካገኘው የመጋረጃ ቤት ሳያንኳኳ ገባ ። በጅግልም ተከትቦ እንደ ሰው ሁሉ ሰው ሆነ ።

ተ ፈ ጸ መ ።

# ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልዎ

# ወይኔ ፡ መውዘሬ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ባላምባራስ ፡ ክንፉ ፡ ሙገሜ ፡ ተፈልፍሎለት ፡ ከቀረ፡ የዋንዛ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ የወርሃ ፡ ታኅሣሥን ፡ ድርሳነ ፡ ሚካኤል ፡ ይደግማሉ ። ከብቶች ፡ ወጥተዋል ። ግቢው ፡ ጭር ፡ ብሏል ። የመላኩ ፡ ለት ፡ ባይሆንም ፡ እን ዲሁ ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ያንን ፡ ከመውዜራቸው፡ ቀጥሎ ፡ የሚኮሩበትን ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያሳዩትን ፡ ድርሳነ ፡ ሚካኤላቸውን ፡ ከዚህ ፡ የዋንዛ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ማንበብ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

አግኝቶ ፡ ያጣውን ፡ ተሹሞ ፡ የተሻረውን ፡ የአርባ ፡ ቀን ፡ ዕድሉ ፡ የጠመመበትን ፡ ፍጡነ ፡ ረዴት ፡ ስንቱን ፡ ይታደገዋል ? ያንን ፡ ከዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ የተ መላለሱበትን ፡ የዲረታእስና ፡ የቴዎብስቲያን ፡ ታሪክ ፡ አግኝቶ ፡ በማጣት ፡ ረገድ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ታሪኩ ፡ የራሳቸው ፡ እየመሰላቸው ፡ በአዲስ ፡ ስሜት ፡ ተመስጠው፡ ሲያነቡ ፡ « ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ዘንተ ፡ ሠለስተ ፡ ምዕተ ፡ ዲናረ ፡ » ከሚለው ፡ ላይ ፡ ብራናውን ፡ ሲገለብጡ ፡ ዓይና ቸውን ፡ እንደዋዛ ፡ ወደማዶው ፡ ጣል ፡ አደረጉ ። ሶስት ፡ ሰዎች ፡ ወደርሳቸው ፡ ቤት ፡ ሲመጡ ፡ አዩ ። አንደኛው ፡ በበርኖሳቸውና ፡ በጥምጥማቸው ፡ ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ፡ መሆናቸውን ፡ አወቁ ። የአቶ ፡ ገላግሌን ፡ መንደር ፡ አል ፈዋልና ፡ አመጣጣቸው ፡ ወደርሳቸው ፡ መሆን ፡ አለበት ። ለምን ፡ ይሆን ? ሲሉ ፡ በሐሳባቸው ፡ ጠየቁና ፡ ሳይደ ርሱ ፡ ድርሳናቸውን ፡ ለመጨረስ ፡ ፈጠን ፡ ብለው ፡

ይደግሙ ፡ ጀመር ። ግን ፡ ሳይጨርሱት ፡ ሰዎቹ ፡ ከግቢ
ያቸው ፡ ደረሱ ።

ባላምባራስ ፡ ክንፉ ፡ እልባት ፡ አርገው ፡ ድርሳኑን ፡
በግራ ፡ ክንዳቸው ፡ ሸጕጡና ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ጋቢያቸ
ውን ፡ ወደላይ ፡ ሰብስበው ፡ ወደሰዎቹ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ።

ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ፡ ከበርኖሳቸው ፡ ሥር ፡ መስቀል ፡
አውጥተው ፡ አሳለሙዋቸውና ፡ « አየ ! ጸሎት ፡ ይዘዋል ፡
መሰለኝ ። ይህችን ፡ ድርሳንዎን ፡ መቸም ፡ አይለቋት ፡ »
አሉ ።

« ታዲያንስ ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዘመኔ ፡ ከጾምና ፡
ከጸሎት ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይመረኝ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ አባ ።
ቢለመነኝ ፡ እሱኑ ፡ ደጅ ፡ ልጥናው ፡ እንጅ ፡ » ሲሉ ፡ መለ
ሱላቸው ።

«የርሱ ፡ ቸርነት ፡ ለርስዎ ፡ ለቆራቢው ፡ ክርስቲያን ፡
ቀርቶ ፡ ለስንቱ ፡ አረመኔ ፡ ይደርስየለ ! ይልቅስ ፡ አሁን ፡
ጸሎቱን ፡ ይጨርሱና ፡ አንድ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ አለብን ፡ »
አሉ ፡ ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ።

« መጨረሴ ፡ ነበር ። ታምሩ ፡ ነው ፡ የቀረ ፡ »

« ኧረ ፡ በቤዛይተ ፡ ዓለሟ ! ተአምሩስ ፡ ቢሆን !
ሲሆንስ ፡ እኔ ፡ ሱባኤ ፡ አስገባለሁ ፡ እንጅ ፡ ጸሎት ፡ ማቋ
ረጥ ፡ ይገባኛል ? ይበሉ ፡ ይጨርሱት ፡ ብየዎታለሁ ! ጉዳ
ያችንም ፡ የሚሰምረው ፡ ከጸሎት ፡ በኋላ ፡ ነው ። እኛ ፡
ወደ ፡ ጓሮው ፡ ገደማ ፡ ስንዘዋወር ፡ እንቆያለን ፡ » ሲሉ ፡
በአባትነት ፡ ገሠጹዋቸው ።

ባላምባራስ ፡ ሐሳባቸው ፡ ከእንግዶቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡
ታምሩን ፡ አነበነቡት ፡ እንጅ ፡ እንደወትሮዋቸው ፡ አልደ



ገሙትም ። ከዚያም ፡ ድርሳኑን ፡ አጥፈው ፡ በመዳፋቸው ፡
ላይ ፡ ቱፍ ፡ ቱፍ ፡ ብለው ፡ ፊታቸውን ፡ ቀባቡና ፡ ወደሰ
ዎቹ ፡ ሄዱ ።

« አየየ ፡ የኔው ፡ ነገር ! አቆምኳችሁ ፡ አይደለ !
ወደቤት ፡ እንግባ ፡ እንጅ ፡ » አሉ ።

« አቶ ፡ ደግፌንና ፡ ቀኛዝማች ፡ ሰይፈን ፡ ያውቋ
ቸው ፡ የለም ? የሟሂት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ » ሲሉ ፡ ቄስ ፡
ወልዳረጋይ ፡ ጠየቁ ።

« ምነዋ ! ሟሂት ፡ ያባቴ ፡ የደጃዝማች ፡ ባንቲደሩ ፡
አገር ፡ አይደለም ? ኧረ ፡ አንድ ፡ ነን ። ከቀኛዝማች ፡ ጋርማ ፡
ማይጨው ፡ ባንድ ፡ ውለን ፡ ነበር ፡ የመጣነው ፡» ሲሉ ፡
ባላምባራስ ፡ መለሱና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አስገቧቸው ። እራ
ቱም ፡ ለምድ ፡ በተነጠፈበት ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።

«ወለቱ ! ማነሽ ፡ አንቺ ፡ ወለቱ ! » በጭብጨባ ፡
ጭምር ፡ ተጣሩና ፡ « ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ሄደዋል ፡
መሰል» ፡ አሉ ፡ ባላምባራስ ። በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደጥ
ንቱ ፡ ባሪያ ፡ የመላ ፡ ለማስመሰል ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ አሽከ
ሮቻቸው ፡ ከተበታተኑ ፤ ያቺ ፡ ያሳደጓት ፡ ወለቱ ፡ ከተማ ፡
ከገባች ፡ ዘመን ፡ የለውም ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ፡ « ታዲያ፡
መምሬ ፡ በጧቱ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አመጣችሁ ? » ሲሉ ፡
ባላምባራስ ፡ እንደማመንታት ፡ ዓይነት ፡ መዳፋቸውን ፡
እያፋተጉ ፡ ጠየቁ ። በሆዳቸው ፡ ግን ፡ የመጡበትን ፡
ጉዳይ ፡ ተጠራጥረዋል ። አዎ ! ታዲያ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡
ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ?

« ከርስዎ ፡ ዘንዳ ፡ በጎ ፡ ጉዳይ ፡ እንጅ ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያመጣን ፡ ብለው ፡ ባላምባራስ ? ከብቶችዎኳ ፡ በአፈላማ ፡ ተይዘው ፡ አያውቁ ! » ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ፡ ብድግ ፡ ሲሉ ፡ ሁለቱም ፡ ሰዎች ፡ አብረው ፡ ተነሱ ።

«ኧረ ፡ በፍጡን ፡ ረዲቱ ፡ ቁጭ ፡ በሉ ! መቆሙ ፡ ታዲያ ፡ ለምን ፡ ይበጃል ! » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ራሳቸውም ፡ ከተቀመጡበት ፡ እየተነሱ ።

« የሚሂቱ ፡ ቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ አንድ ፡ ግሩም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አላቸው ፡ » አሉ ፡ ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ።

« ልጁን ፡ አላውቀውም ፡ እንጅ ፡ ቀኛዝማችማ ፡ አብሮ ፡ አደጌ ፡ ናቸው » ሲሉ ፡ ባላምባራስ ፡ አዳነቁ ።

«እርሳቸውም ፡ ዘወትር ፡ ካፋቸው ፡ አይለይዎትም ። ታዲያ ፡ ዝምድናዎን ፡ ፈልገው ፡ ለልጃቸው ፡ አባትነትዎን ፡ መርጠው ፡ ልጅዎን ፡ ለልጅነት ፡ እንዲሰጧቸው ፡ በድፍረት ፡ ሳይሆን ፡ በልመና ፡ ልከውናል ፡ » አሉና ፡ ቄስ ፡ ወልደአረጋይ ፡ ጭራቸውን ፡ በጣታቸው ፡ አበጣጠሩ ።

ባላምባራስ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አደረጉና ፡ ጥቂት እንደማሰብ ፡ አሉ ። « ለነገሩማ ፡ ከርሱ ፡ ማን ፡ ይበልጥብኛል ። ከደጃዝማች ፡ ጣሰው ፡ ቤትስ ፡ ማን ፡ ይቀርበኛል? ምንስ ፡ ቢሆን ፡ ገና ፡ እርም ፡ ታሀል ፡ ልጅ ፡ ናት ። ከናትዋ ፡ ጉያ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልነጥላት ? » ሲሉ ፡ በጥያቄ ፡ መልክ ፡ መልስ ፡ ሰጡ ።

« አየ ፡ ባላምባራስ ! ልጅዎ ፡ ብትሆን ፡ ያም ፡ ቤቷ ፡ ነው ። የናቷ ፡ ጉያ ፡ ነው ፡ » አሉ ፡ መምሬ ፡ ጭራቸውን ፡ እየነሰነሱ ።



« እሱስ ፡ ነው ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ደከም ፡ ባለ ፡ ድምፅ ።

«እኮይ ! ልጅ ፡ ደግፌ ፡ ተናገሩ ፡ እንጅ ፡ እናንተም !» አሉ ፡ ወደሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

« በርስዎ ፡ ያምራል ፡ ብለን ፡ ነው ፡ መምሬ ፡ »ሲሉ ፡ አንደኛው ፡ መለሱ ።

« ይበሉ ፡ ባላምባራስ። አንድ ፡ ይበሉንና ፡ ይሸኙን ። እንደታቦት ፡ ከፊትዎ ፡ ቁሜ ፡ ስለምን ፡ ? » ሲሉ ፡ ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ፡ እንደመቆጣት ፡ አሉ ።

« ኧረ ፡ ጠላትዎ ፡ ይገተር ፡ አባ ! ለሁሉም ፡ ጊዜ ፡ ስጡኝ ፡ እንጅ ። እናትዋም ፡ ነገሩን ፡ ትስማው ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ።

« እንዲያ ፡ ነው ፡ እንጅ ! እንዳከበሩን ፡ ያክብርዎት ። ትልቅ ፡ ሰው ፡ መቸም ፡ ትልቅ ፡ ነው ። እኛ ፡ መቸም ፡ አሁን ፡ ይፈጸም ፡ አላልንም ። መቸ ፡ አጣነው ! ታዲያ ፡ ቁርጡን ፡ ለማወቅ ፡ የምንመጣበትን ፡ ዛሬውኑ ፡ ወስነን ፡ ብንሄድ ፡ አይሻልም ? » ወደ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ።

« መቸ ፡ ይመችዎታል ? »

« ሰሞኑን ፡ ወዳዲሳባ ፡ ለመውረድ ፡ አስቤአለሁ ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ።

« የወዲያኛው ፡ ያቦ ፡ ለታስ ? »

በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ ሲያበቁ ፡ ቄስ ፡ ወልዳረጋይ ፡ «አቡነ ፡ ዘበሰማያትና ፡ እንበል ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ » ብለው ፡ አሳረጉ ። ከዚያም ፡ ባላምባራስ ፡ « እንዴት ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡

ትሔዳላችሁ ! ትንሽ ፡ አረፍ ፡ በሉባካችሁ ። ልጆቹ ፡ አሁን ፡ ይመጣሉ ፡» ብለው ፡ ትንሽ ፡ ካንገራገሩ ፡ ባኋላ ፡ እያዘኑ ፡ ሸኙዋቸው ።

እናትና ፡ ልጁ ፡ እንስራ ፡ አዝለው ፡ ከወንዝ ፡ ሲመጡ ፡ ሰዎቹ ፡ ከቤት ፡ ቆይተው ፡ ሲመለሱ ፡ከግቢው ፡ ውጭ ፡ ተገናኙ ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ በሃፍረት ፡ ተሸማቀቁ ። እንደወትሮዋቸው ፡ የአባን ፡ መስቀል ፡ ሳይሳለሙ ፡ አንገታቸውን ፡ አቀርቅረው ፡ አለፉ ።

እንስራውን ፡ ከጓዳ ፡ አወረዱና ፡ ወደባላቸው ፡ መጥተው ፡ « መምሩ ፡ እንግዶች ፡ ይዘው ፡ ዛሬ ፡ በጧቱ ፡ምን ፡ እግር ፡ ጣላቸው ? » ሲሉ ፡ ጠየቁ ።

«ያንቺው ፡ ልጅ ፡ ጉድ ፡ ነዋ» ! አሉ ፡ በላምባራስ ፡ በማዳነቅ ፡ እነጋገር ።

« የኔ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ጉድ ፡ መጣባት ? »

« የሚሂቱ ፡ ቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ለልጁ ፡ ጠይቋታል ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ በኩራት ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ « እምምም ! » አሉና ፡ መልሰው ፡ «ውይ ! አፈር ፡ በበላሁት ! ልጄን ፡ አጋልጫት ! » ሲሉ ፡ ደረታቸውን ፡ እንደመምታት ፡ ቃጣቸው ።

« ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ! ፈልገውን ፡ መጡ ፡ እንጅ ፡ ልንለምናቸው ፡ ሄልሄድን ፡ » ባላምባራስ፡ እንደመቆጣት ፡ አሉ ።

« ታዲያ ፡ ጨረሳችሁ ? » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ በጉጉት ፡ ጠየቁ ።



« ደግም ፡ አይደለሽ ፡ እልፉ ? » ባላምባራስ ፡ ባለቤታቸውን ፡ በመገረም ፡ ተመለከቱ ። « ምንስ ፡ ጋብቻው ፡ የተመጣጠን ፡ ቢመስል ፡ ልጄ ፡ ቁማ ፡ ቀርታለች ፡ እንዴ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሽማግሌ ፡ የምፈጣጠም ? መቼም ፡ እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ከመጣላት ፡ ከቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ የተሻለ ፡ ጋብቻ ፡ አናገኝም ። ለሁሉም ፤ ለእምቢታውም ፡ ሆን ፡ ለእሽታው ፡ ሳቦለታ ፡ ቀጥሬያቸዋለሁ ፡ » ሲሉ ፡ አስረዱዋቸው ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፤የሚሂቱ ፡ የደጃዝማች ፡ ጣሰው ፡ ቤት ፡ ልጄን ፡ ለምኖ ፡ እያሉ ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ተራ ፡ ሲያወጉት ፡ በጐረቤት ፡ ቡና ፡ ላይ ፡ ደጋግመው ፡ ሲተርኩት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲንሾካሾኩት ፡ በሐዘን ፡ ቤት ፤ በገበያ ፡ ሲተርቱት ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመላው ፡ ደብር ፡ ነዋሪ ፡ ተዳረሰ ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ለአንዲት ፡ የስለት ፡ ልጃቸው ፡ የሚጠምቁት ፡ ጠላ ፡ የሚጋግሩት ፡ እንጀራ ፡ የሚሠሩት ፡ ወጥ ፡ እንዲያው ፡ ዕድሜ ፡ ልካቸውን ፡ የተመኙት ፡ አደጋገስ ፡ በዓይናቸው ፡ ውልብ ፡ እያለ ፡ በእውን ፡ ደርሶ ፡ የማይፈጽሙት ፡ እየመሰላቸው ፡ ልጃቸውን ፡ በልዩ ፡ የስስት ፡ ዓይን፡ ይመለከቷት ፡ ጀመር ። እንደልጅ ፡ ማዘዛቸውንም ፡ ተዉ ። ምጣድ ፡ ብትጥድ ፡ ሰውነቷ ፡ ይጠቁራል ። ወፍጮ ፡ ብትፈጭ ፡ እጅዋ ፡ ይጐርባል ። ውሃ ፡ ብትቀዳ ፡ ቀጭ ፡ ይወጣባታል ። ጥጥ ፡ ስጥተው ፡ ስትፈትይ ፡ ዋይ ፡ ማለት ፡ ሆነ ። እርሷም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆነባት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ ባላምባራስ ፡ አዝመራውን ፡ ለማየት ፡ ወርደው ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እህል ፡ አስጥተው ፡ ሲለቅሙ ፡ በርኖሱ ፡ አሮጌ፡

መሳይ ፣ ቢሆንም ፣ ጥምጥሙ ፣ ክሽን ፣ ያለች ፤ ልጅ ፣ እግር ፣ ደብተራ ፣ የጉሬዛ ፣ ጭራውን ፣ እያወዛወዘ ፣ መጣና ፣ ለመጣራት ፣ ያህል ፣ እንደመሳል ፣ ብሎ ፣ ወይዘሮ ፣ እልፍነሽ ፣ እንገታቸውን ፣ ሲያቀኑለት ፣ « ደህና ፣ ሰንብታችኋል ? » አለ ፣ በተረጋጋ ፣ እንደበት ።

ወይዘሮ ፣ እልፍነሽ ፣ እንደመደንገጥ ፣ ብለው ፣ « እግዜር ፣ ይመስገን ! » ሲሉ ፣ መለሱ ።

« ድግሱን ፣ ደህና ፣ በጊዜ ፣ ተያይዘውታል ፣ እመቤቴ ፣ » አለና ፣ ቤት ፣ ለእንግዳ ፣ ሳይባል ፣ አልፎዋቸው ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ተዛነብ ፣ ሄደ ።

« የምን ፣ ድግስ ፣ ጌታዬ ? » ብለው ፣ በመደነቅ ፣ ጠየቁት ።

« አሄሄ ! እሜቴ ፣ ከኤፍራታ ፣ እስከ ፣ ግሂት ፣ መላው ፣ ሕዝብ ፣ በየገበያው ፣ የሚያወጋውን ፣ እንደምሥጢር ፣ ይደብቁታል ? » እንደቤተኛ ፣ ከድንጋይ ፣ ላይ ፣ ተዝናንቶ ፣ ተቀምጠ ።

« እናንተ ፣ አታውቁኝም ፣ እንጂ ፣ እኔማ ፣ እርስዎንም ፣ ከነቤተሰብዎ ፣ ባላምባራስንም ፣ በዝና ፣ በሚገባ ፣ አውቃለሁ ። »

በዝና ፣ አውቃለሁ ? ወይዘሮ ፣ እልፍነሽን ፣ የግብዝነት ፣ ደስታ ፣ አቅበጠበጣቸው ፣ « አዎ ! ዛሬ ፣ ዛሬ ፣ ነገር ፣ ዓለሙ ፣ እየቀረ ፣ እንደወትሮው ፣ ከብዙ ፣ ሰው ፣ ጋር ፣ ባንውልም ፣ የጥንቱን ፣ የማይረሳ ፣ ብዙ ፣ ሰው ፣ ያውቀናል ፣ »አሉ ።

« ጋብቻችሁ ፣ ደህና ፣ የሚሆን ፣ ነው ፣ » አለ ፣ ደብተራው ፣ ምክር ፣ አስቀድሞ ፣ እንደተጠየቀ ፣ ዓይነት ።



«ገና ፣ ቁርጥ ፣ ያላገኘ ፣ ቢሆንም ፣ እኛማ ፣ ይሆናል ፣ ብለን ፣ አስበናል ፣ » ሲሉ ፣ እልፍነሽ ፣ መለሱ ።

« አስበናል ፣ አሉ ? አይ ፣ እሜቴ ፣ የዋህ ፣ ነዎት ! »

« ምነዋ ? ኋላ ፣ የሚሆነውማ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፈቃድ ፣ ነው ፣» - አንተም ፣ ባይልልህ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እስከአሁን ፣ ወልደህ ፣ ከብደህ ፣ ነበር ፣ ብለው ፣ በሆዳቸው ፣ አዘኑለት ።

« ፈቃዱስ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ነው ፣ » አለ ፣ ደብተራው ፣ ለመጐተት ፣ ያልደረሰ ፣ ጢሙን ፣ እያሻሸ ፣ «ግን ፣ ደግሞ ፣ እንድናስብ ፣ እንድንመራመር ፣ እንድንጠነቀቅ ፣ የሚበጀንን ፣ እንድናደርግ ፣ ደግሞ ፣ ፈቅዶልናል ። »

« ታዲያስ ፣ እርሱ ፣ ይጠብቃቸው ፣ እንጅ ፣ ነገ ፣ የሚሆኑትን ፣ ምኑን ፣ ተመራመርነው ፣ » አሉ ፣ ወይዘሮ ፣ እልፍነሽ ፣ ቅር ፣ በተሰኘ ፣ አነጋገር ።

« አመጣጤማ ፣ ለርሱ ፣ ነበር ፣ »

« ለምኑ ? » ወይዘሮ ፣ እልፍነሽ ፣ ፈራ ፣ ተባ ፣ ብለው ፣ ነው ፣ እንጅ ፣ የነገሩ ፣ አዝማሚያ ፣ ታይቷቸው ፣ ነበር ። ንግርቱ ፣ ጠብ ፣ ስለማይለው ፣ ባሕታዊ ፣ መጽሐፍ ፣ ገለጦ ፣ ስለማይስተው ፣ ደብተራ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ሰምተዋል ። ክታብ ፣ ያላሰረ ፣ ልጅ ፣ ከስንት ፣ አንድ ፣ ነው ። ባላምባራስ ፣ እያገረገሩ ፣ ባይከለክሉ ፣ ኖሮ ፣ እርሳቸውም ፣ አንድ ፣ ልጃቸው ፣ እንዲያው ፣ የልክፍት ፣ መጠባበቂያ ፣ ስንኳ ፣ ቢኖራት ፣ ባልጠሉ ፣ ነበር ።

« አሄሄ ! እሙቴ ፣ እንዲያው ፣ ነገሩን ፣ እያወቁ ፣ የማያውቁ ፣ ይመስሉብኛል ! »

« ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይወደው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ እሰማለሁ ፡ » ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ጥቂት ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ቆሙ ።

«እነዚህ ፡ ከመልክአ ፡ ማርያም ፡ ያላለፉ ፡ ሰሞነኞች ፡ የሚያወሩትን ፡ አይስሙ ። ከነፍጠኝነቱም ፡ ከግብርናውም፡ ሳይሆኑ ፡ በመጽሐፉም ፡ ከነፍጠኛና ፡ ከገበሬ ፡ አይሻሉም ። መጠምጠማቸውን ፡ ብቻ ፡ አትዩ ። አምላክ ፡ እሥራኤል ፡ ጥበቡን ፡ ለአሮን ፡ ሲገልጥለት ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲረዳበት ፡ ነው ፡ »

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ከንፈራቸውን ፡ መጠጡና ፡ «እስቲ ፡ ወደቤት ፡ ገብተው ፡ አረፍ ፡ ይበሉ ፡» ሲሉ ፡ ጠየቁ ።

« ግዴልዎትም ። እየቆያችሁ ፡ እርስዎም ፡ ጌቶችም ፡ ሙያዬን ፡ ስታውቁት ፡ ቤቴ ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ። ይልቅስ ፡ አሁን ፡ የልጅዎን ፡ ዕድል ፡ እንጨነቅበት ። ኮከባቸው ፡ የሚገጣጠም ፡ ይመስልዎታል ፡ ? »

« እኔ ፡ ምናባቴን ፡ አውቃለሁ ፡ »

« እውነት ፡ አሉ ፡ እመቤቴ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ የማወቅ ፡ ጸጋ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ተሰጥቷል ። ዝናዬን ፡ ሳይሰሙ ፡ አልቀሩም ፡ ይሆናል ። የሰንቱን ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሠርቻለሁ ፡ »

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የሚመልሱት ፡ ጠፋቸው ። « መቼም ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ሁናብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባላም ባራስኳ ፡ ከሰሙ ፡ ወዮልኝ ፡ ነው ። የሚሆን ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ያድርጉ ፡» አሉ ፡ እንደ ፡ ማመንታት ፡ ዓይነት ።

« የልጁን ፡ ስም ፡ ያውቃሉ ? » ሲል ፡ ጠየቃቸው ።



« ኧረ ፡ አላውቀውም ፡ »

« የናቲቱንስ ፡ ? »

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ጣታቸውን ፡ ከከንፈራቸው ፡ ላይ ፡ አርገው ፡ አሰቡ ፡ « ውይ ! ረሳሁት ፡ መሰለኝ ። »

« ግዴለም ፡ እኔው ፡ ጠያይቄ ፡ እደርስበትና ፡ ሰሞኑን ፡ ጉዳዩን ፡ ሁሉ ፡ ጨርሼ ፡ እመጣለሁ ። ኧረገኝ ! በአእምሮዬ ፡ ብዙ ፡ ምሥጢር ፡ እየተመላለሰ ፡ አንዱን ፡ ቁም ነገር ፡ ረሳሁት ። የልጅዎና ፡ የርስዎ ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ ማነው ? »

« ውይ ! የኔው ፡ ደግሞ ፡ ያስፈልጋል ? » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እንደመሽኮርመም ፡ ቢጤ ፡ አንገታ ቸውን ፡ ደፋ ፡ አድርገው ፡ እንደመሳቅ ፡ ቃጣቸው ።

ደብተራው ፡ ለመሔድ ፡ ተነሣ ።

« ታዲያ ፡ እንዲያው ፡ ከቤት ፡ ሳይገቡ ፡ እንዲያው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሳይቀምሱ ፡ ሊሔዱ ፡ ነው ? » አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የሚናገሩት ፡ ጠፍቷቸው ።

«ስታውቁኝ ፡ ቤቴ ፡ ያሆናል ፡ ብዬ ፡ ቀድም ፡ ነግሬዎት ፡ የለም ? አሁንስ ፡ እቸኩላለሁኝ ። እንደናንተ ው ፡ ሳይመሽ ፡ የምጠይቃቸው ፡ ዘመዶች ፡ አሉኝ ፡ » ሲል ፡ ደብተራው ፡ መለሰ ።

« የተወቀጠ ፡ ቡና ፡ አለ ። ባንዳፍታ ፡ እደርሰዋለሁ ።» ደብተራው ፡ ለመሔድ ፡ እንደመቃጣት ፡ አለ ።

« ኧረ ፡ በሦስቱ ፡ ሥላሴ ! የሰው ፡ ቤትኮነው ፡ » ብለው ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ አከረሩ ።

« አዬ ፡ እመቤቴ ! በማይሆነው ፡ ያዙኝ ! እንግዲያውስ ፡ ቡናው ፡ ይቅርብኝና ፡ የሚጠጣ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ »

« ሞልቶ ፡ ተርፎ ፡ ምን ፡ ጠፍቶ ! » ሲሉ ፡ ወደጓዳ ፡ እየበረሩ ፡ ሄደው ፡ ለክፉ ፡ ቀን ፡ የተመረገውን ፡ ድፍድፍ ፡ ከፍተው ፡ በፋጋ ፡ በጥብጠው ፡ በኮልባ ፡ ዋንጫ ፡ ሞልተው ፡ ከመቅጃበት ፡ ይዘው ፡ ከተፍ ፡ አሉ ። ፉት ፡ ብለው፡ ቀምሰው ፡ ሰጡት ።

ሰውዬው ፡ በሰፌው ፡ ተጐነጨለት ።

« ጉሽ ፡ ነው ። ግን ፡ መቸም ፡ ጥም ፡ ያረካል ፡ » አሉ ። በመጨረሻም ፡ « ከሆነስ ፡ ከአቦ ፡ በፊት ፡ ብቅ ፡ ቢሉ ፡ አይከፋም ፡ ነበር ፡ » እያሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እንግዳቸውን ፡ እስከግቢው ፡ በር ፡ ሸኝተው ፡ ተመለሱ ።

ደብተራው ፡ ቀጠሮ ፡ ከሰጠ ፡ ሳምንት ፡ አለፈው ። ልደታ ፡ ገባች ። የአማጮቹ ፡ ቀጠሮም ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ቀረው ። የወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ስሜት ፡ ይቅበጠበጥ ፡ ጀመር ። ወትሮውንም ፡ ቢሆን ፡ ራሳቸው ፡ አላሰቡት ፡ ነበር ። ልባቸውን ፡ አነሳስቶ ፡ መጥፋቱ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይባላል ? ወስላታ ፡ ደብተራ ! ይኸኔ ፡ ለዚያች ፡ ቅራሪ ፡ ብሎ ፡ ይሆናል ! ሲሉ ፡ በሆዳቸው ፡ ተሳደቡ ። ግን ፡ አንድ ፡ ልባቸው ፡ ደግሞ ፡ አልቆረጠም ። ታዲያ ፡ ነገሩ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ዕጣቸው ፡ አጥፊና ፡ ጠፊ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅስ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ? « እኮን ፡ አሁን ፡ የነገ ፡ አቦ ፡ ልት ጨርሱ ፡ ነው ? እንደኔስ ፡ ሩቅ ፡ ያሉት ፡ ዘመዶችም ፡ ሰምተውት ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብንመክርበት ፡ አይከፋም ፡ » ሲሉ ፡ ባላቸውን ፡ አንድ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አስታወሱ ።

ባላምባራስም ፡ ሁለት ፡ ጊዜውን ፡ ታገሱና ፡ «አንቺ ፡ ሴትዮ ፡ ምን ፡ ነካሽ ! ጤናም ፡ አልያዘሽ ! የእኛ ፡ ጀምበር ፡



በጠለቀችበት ፡ የገበሬና ፡ የሸማኔ ፡ ቀን ፡ በወጣበት ፡ ልጄ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ጋብቻ ፡ እንደማታገኝ ፡ ሳውቀው ፡ ቁማ ፡ ትቅር ፡ ነው ፡ የምትይው ? » ሲሉ ፡ አፋቸውን ፡ አሲያዙ ፡ ቸው ።

የባታ ፡ ለት ፡ እንደዚያው ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ መንደሩ፡ ጭር ፡ ሲል ፡ ደብተራው ፡ ከተፍ ፡ አለላቸው ።

« ውይ ! መጡ ? እኔስ ፡ ቀረሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ » አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ።

« አሄሄ ! እመቤቴ ፡ እንኳን ፡ ለቁርጠኛዬ ፡ ለሌላውም ፡ ቃሌ ፡ ከታሠረ ፡ አይፈታም ። ታዲያ ፡ ይኸንኑም ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ተጉዤ ፡ ነው ፡ የደረስኩት ፡ » ደብተራው ፡ ከጉያው ፡ ውስጥ ፡ በጨርቅና ፡ በክር ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ አወጣ ። ከዚያም ፡ ባላምባራስ ፡ ከሚቀመጡበት ፡ የዋንዛ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠና ፡ በጥንቃቄ ፡ ይፈታ ፡ ጀመር ። «ይሀ ፡ ለሁሉም ፡ ነገር ፡ የሚሆን ፡ ልፋፌ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ። ማንም ፡ ሰሞነኛ ፡ የሚከትበው ፡ አይመስልዎት ! የዓረብ ፡ ልፋፌ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ! » በአሮጌ ፡ የመርዶፋ ፡ ጨርቅ ፡ የተሰፋውን ፡ ክታብ ፡ ለይቶ ፡ አሳያቸው ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ « አንዴ ፡ ይቆዩኝ ! » ብለው ፡ እየበረሩ ፡ ማድቤት ፡ ገብተው ፡ ከእልፍኝ ፡ እንዳትላወስ ፡ ልጃቸውን ፡ አዘው ፡ ጠላውን ፡ በኮልባ ፡ ቆሎውን ፡ በመሶብ ፡ ወርቅ ፡ ይዘው ፡ እየተንደረደሩ ፡ መጡ ። ከደብተራው ፡ አፍ ፡ ጠብ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ ይጠብቁ ፡ ገባ ።

« ይኸ ፡ ደግሞ ፡ » አለ ፡ ደብተራው ፡ ሁለተኛውን ፡ ክታብ ፡ አንስቶ ፡ « አምላከ ፡ እሥራኤል ፡ ለሰሎሞን ፡ የገ

ለጠለት ፡ ሰሎሞንም ፡ በስመ ፡ ሃሃኤል ፡ አጽናኤል ፡ ኤላኤል ፡ ላላኤል ፡ አምላኤል ፡ ምላኤል ፡ ሃሃሃሃሃኤል ፡ ሃረዋኤል ፡ ማማማኤል ፡ ማሚመ ፡ አደኤል ፡ ከትቦት ፡ ከጽላተ ፡ ሙሴ ፡ ጋር ፡ የመጣልን ፡ በአንተ ፡ ፍቅረ ፡ ሰብዕ፡ ነው ። መቾም ፡ ኮከባቸውኳ ፡ የርሱ ፡ ከጸሐይ ፡ መግቢያ ፡ በኩል ፡ የሚወጣው ፡ ሰንቡላ ፡ መሬት ፡ የርሷ ፡ ገውዝ ፡ ነፋስ ፡ ነው ። ይገጣጠማል ፡ » ደብተራው ፡ ከቆሎው ፡ ቅሞ ፡ ከጠላው ፡ ተጐነጨለት ። « ልጅዎ ፡ በሰው ፡ አገር፡ ትከብራለች ። ግን ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ጥቂት ፡ የደም ፡ ሕመም ፡ ያገኛታል ። እጀሰብ ፡ ይጸረራታል ፡ ይላል ፡ ኮከቧ ። ታዲያ ፡ ለደሙ ፡ የስንደዶ ፡ ተቀጥላ ፡ ለእጀሰቡ ፡ የቀረጥ ፡ ተቀጥላና ፡ የነፍስ ፡ ጡር ፡ ነብር ፡ ወተት ፡ ለማምጣት ፡ ዜጋመል ፡ ወርጄ ፡ ሰነበትኩ ፡ እልዎታለሁ ። »

« የነብር ፡ ወተት ፡ አሉኝ ? ውይ ! ውይ ! በተሰቀለው ! እንኳን ፡ እናትዎን ፡ አላረገኝ ። » ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ደረታቸውን ፡ በእጃቸው ፡ መቱ ።

« እንደሰውማ ፡ ቢሆን ፡ አዎ ! ግን ፡ ቀብቶ ፡ የስጠን፡ መጠበቂያስ ? ይህንን ፡ ሁለቱን ፡ በጥቁር ፡ ሐር ፡ አንዱን ፡ በቅናተ ፡ ዮሐንስ ፡ ይሥሩላት ፡» ብሎ ፡ ሰጣቸው ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እጃቸው ፡ ተንዘፈዘፈባቸው ። ሥውር ፡ ኃይሉ ፡ ነው ። ለአሮን ፡ ልጆች ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣኑ ፡ ነው ።

ሳቅም ፡ ልቅሶም ፡ እየቃጣቸው ፡ በሙዳይ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጠው ፡ ተመለሱ ።

« ታዲያ ፡ ምንድነው ፡ ውለታዎ ? » ሲሉ ፡ እጃቸውን ፡ ከደረታቸው ፡ ላይ ፡ እመሳቅለው ፡ ጠየቁ ።



« የኛ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ውለታ ፡ ይኖረዋል ፡ ብለው ? ዕውቀታችን ፡ በገንዘብ ፡ አይገዛ ። እምአእላፍ ፡ ጉልበት ፡ ቢጠራቀም ፡ የምንሠራውን ፡ አይሠራም ። ሕይወት ፡ በገንዘብ ፡ ይገኛል ፡ እመቤቴ ? ቢሆንም ፡ በደጁ ፡ ሰላም ፡ በአጸደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ የሚገኙትን ፡ ችግረኞች ፡የምንረዳው ፡ እንደናንተ ፡ ከመሳሰሉት ፡ መኳንንት ፡ ቤተሰብ ፡ በምናገኘው ፡ ነው ። »

« እሱማ ፡ ነው ። እኮ ፡ ታዲያ ፡ ዋጋውም ፡ ባይሆን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ልክፈልዎት ? » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እየተጨነቁ ፡ ጠየቁ ።

« መቾም ፡ ድካሜን ፡ ራስዎ ፡ አስበው ፡ ይገምቱት ። ዜጋመል ፡ በረሃ ፡ ከርሜ ፡ ነው ፡ የተመለስኩ ፡ » ሲል ፡ መለሰላቸው ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ወደጓዳቸው ፡ ገቡ ። መጀመርያ ፡ መድበው ፡ በአገልግል ፡ ያስቀመጡትኳ ፡ አምስት ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ ነበር ። ታዲያንስ ፡ ዜጋመል ፡ መውረዱን ፡ አላወቁም ። እንደገና ፡ ከትልቁ ፡ እንስራ ፡ ሥር ፡ ቆፍረው፡ አምስት ፡ ብር ፡ አወጡና ፡ አስር ፡ ብር ፡ አምጥተው ፡ ሰጡት ።

« በቀደምም ፡ ዛሬም ፡ ከቤት ፡ ሳይገቡ ፡ መሔድዎ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ? » ሲሉ ፡ ጠየቁ ።

« ግዴልዎትም ፡ የወደፊት ፡ ቤቱ ፡ ነው ። ለሠርጉ ፡ ያብቃን ? » ሲል ፡ መርቆ ፡ ተሰናበተ ።

« አሜን ! » አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ያቦ ፡ ለት ፡ « የት ፡ መሔድሽ ፡ ነው ? ተይ ፡ እንጅ ፡ አታስበርጅኝ ፡ » እያሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ክንፉ ፡ ሲያጉረመረሙ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ወፍ ፡ መንጫጫት ፡ ሲጀምር ፡ ከመኝታቸው ፡ ተነሱና ፡ አንድ ፡ እንሥራ ፡ ጠላ ፡ በጠበጡ ። በጥብጠው ፡ ያላሳደሩት ፡ የቆየ ፡ ድፍድፍ ፡ ስለሆነ ፡ ቃናውን ፡ እንዳይለውጥ ፡ በማለት ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ቅንጬ ፡ አብስለው ፡ ለእንፍርፍር ፡ የሚሆን ፡ ቂጣ ፡ ጋግረው ፡ ቡና ፡ ቆልተውና ፡ ወቅጠው ፡ አስቀመጡ ። ቤቱን ፡ በሙሬ ፡ ሙልጭ ፡ አድርገው ፡ ጠረጉና ፡ ተጠቅልለው ፡ የተቀመጡትን ፡ አጐዛና ፡ ጀንዲ ፡ አነጠፉበት ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የቤቱን ፡ መሰናዶ ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ትልቁን ፡ የልብስ ፡ አገልግል ፡ ከፍተው ፡ የክቱን ፡ ጥልፍ ፡ ቀሚስ ፡ አጠለቁ ። ካለወትሮዋቸውም ፡ ሽንሽናቸውን ፡ ለማሳመር ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ፈጁ ። ሹርባቸውን ፡ በአዲስ ፡ በተለወሰው ፡ ቅቤ ፡ አወዛዙና ፡ ቁንዳላውን ፡ በእንዝርት ፡ ዘንግ ፡ ቀና ፡ ቀና ፡ አደረጉት ።

« ረፍዷልኮ ፡ ባላምባራስ ፡ አትነሣም ፡ እንዴ ? » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የባላቸውን ፡ የክት ፡ ጋቢ ፡ ከአልጋው ፡ ሥር ፡ አስቀመጡላቸው ።

ባላምባራስ ፡ አይናቸውን ፡ አጨልገው ፡ አዩና ፡ « እንቺ ፡ የምትታጭ ፡ ሙሽራ ፡ አልመሰልሽም ፡ እልፉ ! » ሲሉ ፡ ቀለዱባቸው ።

«ጠላት ፡ ደስ ፡ አይበለው ። ወዳጅም ፡ አይከፋው ። ምንስ ፡ ቢሆን ፡ » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ንግግራቸ



ውን ፡ አንጠልጥለው ፡ ተውትና ፡ ከእልፍኝ ፡ ብቅ ፡ እንዳትል ፡ ልጃቸውን ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ሄዱ ።

ባላምባራስ ፡ ከዚያ ፡ ከሚወዱት ፡ የዋንዛ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ድርሳነ ፡ ሚካኤላቸውን ፡ ሲያነቡ ፡ ዓይኖቻቸው ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ይወርዳሉ ፡ እጃቸውም ፡ ስንት ፡ ሽህ ፡ ጊዜ ፡ ቃጣ ፡ የሳቡት ፡ ጣቶቻቸውም ፡ ብራናውን ፡ ያገላብጣሉ ፡ እንጅ ፡ እንደወትሮው ፡ ቃላቶቹ ፡ አይታዩዋቸውም ፡ ነበር ። ታሪኩም ፡ ሕሊናቸውን ፡ አልነካዉም ። ወትሮ ፡ ድርሳናቸውን ፡ ከያዙ ፡ መብረቅ ፡ ቢወርድ ፡ አይሰማቸውም ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ለቅጠል ፡ ኮሽታ ፡ ጆሮዋቸው ፡ ነቅቶ ፡ ነበር ። ዓይኖቻቸውም ፡ ወዲያው ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ አሻገሩ ፡ ይወረወሩ ፡ ነበር ።

« ነገሩ ፡ የሚከፋ ፡ አይደለም ። ኧረ ፡ ደህና ፡ ነው ፡ » አሉ ፡ ብቻቸውን ፡ ደጋግመው ። አዎ ! የቀኛዝማች ፡ አደፍርሰውን ፡ ዘር ፡ ሲያጠያይቁ ፡ ሲመራመሩና ፡ ሲያጣሩ ፡ ስንብተው ፡ ነበር ። ቅንጣት ፡ ያህል ፡ ሰባራ ፡ አጥንትና ፡ የሚያስነውር ፡ ሙያ ፡ አላገኙበትም ። ከእነወለተ ፡ እሥራኤል ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ የነጠረ ፡ ግንድ ፡ ነው ። ዘር ፡ ማንዝሩም ፡ የታወቀ ፡ ጀግና ፡ ነፍጠኛ ፡ ነው ። የቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ባለቤት ፡ አያት ፡ ብቻ ፡ የጨው ፡ ነጋዴ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ልጁም ፡ ደህና ፡ የደረሰ ፡ ጕረምሳ ፡ ነው ። «ምንም ፡ አይደለ ። ኧረ ፡ አይከፋም ! » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ለአራተኛ ፡ ጊዜ ።

ረፈድፈድ ፡ ሲል ፡ ሰዎቹን ፡ ሲመጡ ፡ ከሩቅ ፡ አዩዋቸው ። አሁን ፡ አራት ፡ ራሳቸውን ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ድርሳናቸውን ፡ ከአልጋቸው ፡ ራስጌ ፡ አስቀመጡና ፡ እን

ግዶቹ ፣ መምጣታቸውን ፣ ለባለቤታቸው ፣ አስጠንቅቀው ፣ እንደዋዛ ፣ በጓሮ ፣ እየተዘዋወሩ ፣ ጠበቋቸው ።

የመምሬን ፣ መስቀል ፣ ተሳልመው ፣ ቤት ፣ ከአስገቢቻውና ፣ ከተቀመጡ ፣ በኋላ ፣ « ታዲያስ ፣ አዝመራህ ፣ ደህና ፣ ተያይዝዋል ? » ሲሉ ፣ ቀኛዝማች ፣ ሰይፉ ፣ ጠየቁ ።

« ይመስገነው ፣ ለፈጣሪ ፣ » ሲሉ ፣ ባላምባራስ ፣ መለሱ ።

« ታዲያ ፣ አዲሳባ ፣ ምን ፣ ወሬ ፣ አለ ?» የቀኛዝማች ፣ ሰይፉ ፣ ለጠያየቅ ፣ ጉጉት ፣ ሳይሆን ፣ ጨዋታውን ፣ ለማቀጣጠል ፣ ያህል ፣ ነበር ።

« ያዲስ ፣ አባ ፣ ነገር ፣ ደግሞ ፣ ምኑ ፣ ተወርቶ ፣ ያልቃል ? ያለቅባትና ፣ ያለማገዶ ፣ የሚንቦገቦገው ፣ የሽቦ ፣ መብራት ፣ እንደሰይጣን ፣ የሚከንፈው ፣ መቶበላ ፣ የሚባለው ፣ ነገር ፣ የጋለሞታው ፣ ነገር ፤ አስረሽ ፣ ምችው ፣ ኧረ ፣ ጉድ ፣ ነው ፣ የሚታየው ! » ሲሉ ፣ በማዳነቅ ፣ ራሳቸውን ፣ ወዘወዙ ።

« የደጃማች ፣ አጥላባቸው ፣ ልጅ ፣ ያ ፣ የበከሩ ፣ ካዲሳባ ፣ ባሕር ፣ ማዶ ፣ ሄደ ፣ የሚባለው ፣ ውነት ፣ ነው ? » በማለት ፣ አቶ ፣ ደግፌ ፣ ጠየቁ ።

« እሱንስ ፣ አልሰማሁም ። ምኑ ፣ ቅጡና ፣ ሰውስ የት ፣ ተገናኝቶ ፣ »

« ኢየሩሳሌም ፣ ይሆናል ፣ የሄደው ፣ » አሉና ፣ መምሬ ወልዳረጋይ ፣ ጨዋታውን ፣ በመለወጥ ፣ « ከባላምባራስ ፣ ታዬ ፣ ጋር ፣ ትተዋወቁ ፣ የለ ?» በማለት ፣ አራተኛውን ሰው ፣ በመስቀላቸው ፣ ጫፍ ፣ አመለከቱ ።



« በዝና ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ » አሉ ፣ ባላምባራስ ፣

« አንዱ ፣ የሚሄት ፣ አድባር ፣ ይሉሃል ፣ እሱ ፣ ነው ። መቸም ፣ የመጣነው ፣ ለያው ፣ ለቀጠሮዋችን ፣ ነው ። »

የደረቡት ፣ የክት ፣ ጃኖ ፣ ተዘጋጅተው ፣ መጠበቃቸውን ፣ የማያሳውቅ ፣ ይመስል ፣ « አሆሆ ! ዛሬ ፣ ኖሯል ?» ሲሉ ፣ እንደማዘን ፣ ዓይነት ፣ ጢማቸውን ፣ ፈታተጉ ።

« ኋላስ ! አዬ ፣ ባላምባራስ ፣ ዝንጉ ፣ መሆን ፣ ጀመርክ ። » መምሬ ፣ ኮስተር ፣ ብለው ፣ ተመለከቷቸው ።

« መዘንጋትስ ፣ አልዘነጋሁትም ፣ ነበር ። ታዲያ ፣ ጊዜ ፣ አጠረና ፣ ከዘመድ ፣ ጋር ፣ አልተመካከርኩበት ፣ »

« አሄሄ ! ባላምባራስ ፣ አሁንስ ፣ ልታስከፋኝ ፣ ነው ። እኔስ ፣ የማማክር ፣ ዘመድ ፣ አይደለሁም ? የማይሆን ፣ ነገር ፣ ይዤ ፣ ካንተ ፣ ዘንድ ፣ እመጣለሁ ? የለም ። በካህን ፣ እግሬ ፣ ብመላለስ ፣ እግዚአብሔር ፣ አይወድልህም ። »

« እርሱማ ፣ ነው ፣ »

« እኮይ ! »

« ቢሆን ፣ መቸስ ፣ » ብለው ፣ ባላምባራስ ፣ ንግግራቸውን ፣ ሳይጨርሱ ፣ መምሬ ፣ ጭራቸውን ፣ እያወራጩ ፣ ተነሱና ፣ አቋረጧቸው ። ሶስቱም ፣ ሽማግሌዎች ፣ አብረው ፣ ተነሱ ።

« ኧረ ፣ በበዛይተ ፣ ዓለሚ ! አንድ ፣ በለንና ፣ ሸኘን ፣ ነው ፣ የምልህ ። ወላዲቴን ፣ እንዳልገዝትህ ፣ ! » ሲሉ ፣ መምሬ ፣ ተቆጡ ።

«አበስገበርኩ ! ምነዋ ፡ አባ !» ባላምባራስ ፡ አማ
ተቡ ። « ምንስ ፡ ቢሆን ፡ እርሱዎን ፡ አባቴን ፡ አሳዝና
ለሁ ! በሕልሜም ፡ አይድረስብኝ ። »

« በላ ፡ እሺ ፡ በለኝ ! » እርግጥ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ ዓይ
ነት ፡ ነበር ።

ባላምባራስ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አድርገው ፡ ጥቂት፡
ያሰቡና ፡ የተከዙ ፡ መሰሉ ። ለስለስ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ «መቼስ፡
ከቃልዎ ፡ አልወጣ ። እሺ ፡ » አሉ ።

« እንዲያ ፡ ነው ፡ እንጅ ! » ሲሉ ፡ መምሬ ፡ ጭራ
ቸውን ፡ በኃይል ፡ አወዛወዙት ። ከዚያም ፡ አቡነ ፡ ዘበሰ
ማያትና ፡ በሰላመ ፡ ገብርኤል ፡ አድርሰው ፡ ያሰብነውን ፡
ይፈጽምልን ፡ የዘራነውን ፡ ይባርክልን ፡ ያመረትነውን ፡
ያበርክትልን ፡ እሺ ፡ እንዳልከን ፡ እንዱ ፡ አምላክ ፡ እሺ ፡
ይበልህ ፡ ሲሉ ፡ አሳረጉና ፡ ሁሉም ፡ አሜን ! ብለው ፡ ተቀ
በሉ ።

« ይበሉ ፡ እንግዲህ ፡ የማሠሪያውን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡
ይስጡን ፡ » ሲሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ ሰይፌ ፡ ጠየቁ ።

« እኮ ፡ ቁጭ ፡ በሉ ! በቀደም ፡ ለታ ፡ እንዲሁ ፡
እንደሀዘን ፡ ቤት ፡ ገብታችሁ ፡ ወጥታችሁ ፡ ሄዳችሁ ፡ »
አሉ ፡ ባላምባራስ ።

ሽማግሌዎቹ ፡ ቂጣቸው ፡ ገና ፡ መሬት ፡ ሳይነካ ፡
ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ በቀዳዳ ፡ አጮልገው ፡ ሲጠባበቁ ፡
እንደቆዩ ፡ ሁሉ ፡ ሞሰቡን ፡ ግምጃ ፡ አልብሰው ፡ ከተፍ ፡
አሉ ።

« እንዲያው ፡ ለአፍ ፡ ማሟሻ ፡ ያህል ፡ ነው ፡ » አሉና
ክዳኑን ፡ ከፈቱት ። ቅንጬና ፡ ቋንጣ ፡ ጥብስ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡



ጉች ፡ ጉች ፡ ብሏል ። ከመካከል ፡ የግፍንፍል ፡ ፍትፍት ፡
ተቆልሏል ። « ይበሉ ፡ አባ ፡ ይባርኩት ፡ እንጅ !» ብለው ፡
ወደ ፡ ጓዳቸው ፡ ተመለሱ ። ጠላውን ፡ በማንቆርቆሪያ ፡
ዋንጫውን ፡ አስከክተው ፡ መጡና ፡ እየቀዱ ፡ ሰጡ ።

« ይኸውላችሁ ፡ አሽከሩ ፡ ሁሉ ፡ እየኰበለለ ፡ አለቀ »
አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ባለቤታቸው ፡ ጠላ ፡ ሲቀዱ ፡ የመዋ
ረድ ፡ ቅሬታ ፡ ተሰምቷቸዋል ።

« ፍካሬ ፡ የሱሱ ፡ ጨርሶት ፡ የለ ! ስምንተኛው ፡
ሺህ ፡ መቃረቡ ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ መምሬ ፡ መለሱላቸው ።
ቁርስ ፡ ተበልቶ ፡ ቡና ፡ ከተጠጣ ፡ በኋላ ፡ ለቃል ፡ ማሠሪ
ያው ፡ የነሐሴ ፡ በዓታ ፡ ተቃጥረው ፡ ባላምባራስ ፡ እንግዶ
ቹን ፡ ሸኝተው ፡ ሲመለሱ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ከደጃፉ ፡
ላይ ፡ ጠበቋቸው ።

« በይ ፡ እንግዲህ ፡ ሞጥረሽ ፡ መደገስ ፡ ነው ፡ » አሏ
ቸው ፡ ሚስታቸውን ።

« ክብሩ ፡ ይስፋ ፡ እንጅ ፡ ለዚህ ፡ ካበቃኝ ፡ ነው ! »
ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጣሪያው ፡ ላይ ፡
ቁልቁል ፡ የሚመለከታቸው ፡ ይመስል ፡ ወደላይ ፡ አንጋ
ጠጡ ።

የነሐሴ ፡ በዓታ ፡ ለት ፡ ቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡
ከፊተኞቹ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ ጨምረው ፡
ሰባት ፡ ራሳቸውን ፡ ሲመጡ ፡ ባላምባራስ ፡ ከንቱም ፡ አምስት ፡
ራሳቸውን ፡ ሆነው ፡ ተቀበሉዋቸው ። ገብተው ፡ የወንድ ፡
ወገን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡
ጥ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ። ማንም ፡ ሰው ፡ እንነሣ ፡ ብሎ ፡
ይናገር ፡ ሁሉም ፡ እንደገና ፡ ተነስተው ፡ ቆሙ ።

« ይበሏ ! » አሏቸው ፡ መምሬ ፡ ባላምባራስን ።

« ልጄን ፡ ሐመልማልን ፡ ለቀኛዝማች ፡ አደፍር ሰው ፡ ልጅ ፡ ለልጅ ፡ ጉበና ፡ ሰጥቻለሁ ። ለዚሁም ፡ ግራዝማች ፡ አሸብርና ፡ አቶ ፡ እንዳይላሉ ፡ እማኞቼ ፡ ናቸው ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ።

« የባላምባራስ ፡ ክንፉን ፡ ልጅ ፡ ሐመልማልን ፡ ለልጄ ፡ ለጉበና ፡ ተቀብያለሁ ። ለዚሁም ፡ ቀኛዝማች ፡ ሰይፈና ፡ አቶ ፡ ደግፌ ፡ እማኞቼ ፡ ናቸው ፡ » ሲሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ አጸፋውን ፡ መለሱ ። የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ መምሬ ፡ ወልዳረጋይ ፡ ሆኑ ። ቀኛዝማች ፡ አደፍር ሰው ፡ በሐር ፡ ማተብ ፡ የተንጠለጠለውን ፡ የብር ፡ ቀለበት ፡ አውጥተው ፡ ለባላምባራስ ፡ ሰጡ ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የቃል ፡ ማሠሪያውን ፡ የደገሱት ፡ በመጠኑ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ማድጋ ፡ ጠላ ፡ አንድ ፡ ስልቻ ፡ ማር ፡ ጠጅ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ከሶስት ፡ ዶሮ ፡ አላለፈም ። ድግሱን ፡ ለዋናው ፡ ቆጥበውታል ።

ሠርጉ ፡ ሐሙስ ፡ ቀን ፡ ለሚውለው ፡ ቃና ፡ ዘገሊላ ፡ ተቀጠረ ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ እንኳ ፡ ለድግሱ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ በፋሲካው ፡ ተጋቦት ፡ ቢሆን ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ባላምባራስ ፡ ግን ፡ ድርሳኑ ፡ ከእጃቸው ፡ የማይለየው ፡ ሚካኤል ፡ ከሐሙስ ፡ ጋር ፡ ተገጣጥሞ ፡ የሚውልበትን ፡ ቀን ፡ መረጡ ። ታዲያ ፡ ተገጣጥሞ ፡ የተገኘው ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ነበር ።

እንዳይደርስ ፡ የለም ፡ ጥር ፡ ደረሰ ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ግን ፡ በሥራ ፡ እቅላቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ቀኑንም ፡ ረስተውት ፡ ነበር ። ሰው ፡ ሲያነጋግራቸው ፡ አይናቸውን ፡ አፍጥጠው



እየተመለከቱ ፡ ድንገት ፡ እንደባነኑ ፡ ያህል ፡ «እእእ» ይላሉ ። ሌት ፡ ከቀን ፡ በዓይኑ ፡ ልቦናቸው ፡ የሚመላለሰው ፡ የጌሾው ፡ የብቅሉ ፡ የእንኩሮው ፡ የጥንስሱ ፡ ሥዕል ፡ ነው ። በአካልም ፡ ቢሆን ፡ ከባድ ፡ ድካም ፡ ደርሶባቸው ፡ ነበር ። ዕቃ ፡ ፍለጋ ፡ እስከወበሬና ፡ እስከገድም ፡ ድረስ ፡ ሄደዋል ። ሙግግ ፡ ብለው ፡ አጥንታቸው ፡ ወጣ ። አንድ ፡ ቀን ፡ « እልፉ ! ሰውነትሽ ፡ አለቀ ። ሕሊናሽም ፡ ቦዘ ። ሲያናግሩሽ ፡ አትሰሚም ! ራስሽን ፡ ጐዳሽኮ ! ቀስ ፡ በይ ፡ እንጂ ፡ » ሲሉ ፡ በፍቅር ፡ ተቆጥተዋቸዋል ። ግንስ ፡ ባላምባራስ ፡ ራሳቸውም ፡ ቢሆን ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ እንደዋዛ ፡ አልያዙትም ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ለአደሱ ፡ ለአፈርኮቻቸሩ ፡ የተጨነቁትን ፡ ያህል ፡ ባላምባራስም ፡ ሰንጋ ፡ ለመግዛት ፡ ጥገቶቻቸውን ፡ በስውር ፡ ሸጠዋል ። በኤፍራታ ፡ ሁለት ፡ ጋሻ ፡ የገባር ፡ መሬት ፡ ነበራቸው ። ሶስት ፡ መቶ ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ ተበድረው ፡ አሲዘውታል ። ያንን ፡ ደግ ፡ ዘመን ፡ በቅምጥልና ፡ አሳልፈው ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ለመጣች ፡ አንድ ፡ ልጃቸው ፡ ሠርግ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀርቶ ፡ ቢቀርሳ !

መቸም ፡ ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ አይጥፉ ፡ ወገን ፡ እያሳጣ ፡ እንጅ ፡ ከኤፍራታ ፡ የወራ ፡ ገብሬ ፡ ልጆች ፡ ከግድም ፡ የለታ ፡ ልጆች ፡ ከማማ ፡ ምድር ፡ የማማ ፡ ልጆች ፡ ከጌራ ፡ ምድር ፡ የጌራ ፡ ልጆች ፡ ለባላምባራስ ፡ ድግስ ፡ ላሎ ፡ ምድር ፡ መጥተው ፡ ሰፈሩ ። ወንዶች ፡ በዳስ ፡ ሥራ ፡ በዕቃ ፡ ፍለጋና ፡ መልከት ፤ ሴቶቹ ፡ በጓዳው ፡ ድግስ ፡ ሁሉም ፡ ሽር ፡ ጉድ ፡ ሲል ፤ የባላምባራስ ፡ ግቢ ፡ የወታደር ጦር ፡ ሠፈር ፡ መስሎ ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ጠጅ ፡ ተጣለ ። ሰባት ፡ ሠንጋ ፡ ታረደ ። ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ጠላውም ፡ ጠጁም ፡ ተዋጣላቸው ።

ከዳገቱ ፣ ከባላምባራስ ፣ ግቢ ፣ ሆኖ ፣ እድመኛው ፣ እየተቀጣጠለ ፣ ሲመጣ ፣ ከሩቅ ፣ ይታያል ። ባላምባራስ ፣ ወጣ ፣ እያሉ ፣ ቁልቁል ፣ ሲመለከቱ ፣ ፊታቸው ፣ በደስታ ፣ ይፈካ ፣ ነበር ። ከበሩ ፣ ውጭ ፣ አስተናባሪዎቹ ፣ እድምተኛ ውን ፣ በእጃቸው ፣ እየመሩ ፣ ያስገባሉ ። ከዳሱ ፣ በር ፣ ላይ ፣ ግቢ ፣ ተቀባዮች ፣ ወጡን ፣ እንጀራውን ፣ ጠላውን ፣ ወደ ጓዳ ፣ እየላኩ ፣ ብሩን ፣ በተነጠፈ ፣ ነጠላ ፣ ይደረድሩታል ። በጽሑፍ ፣ መመዝገብ ፣ የለም ። ግን ፣ ማን ፣ ምን ፣ እንዳ መጣ ፣ ተቀባዮቹ ፣ ከቶ ፣ አይስቱም ። በኋላ ፣ በዝርዝር ለባላምባራስ ፣ ይነግራሉ ። ሙግት ፣ ያስገባ ፣ ነበር ። ያንድ ደብር ፣ ዘመዶቻቸውም ፣ ሰንጋ ፣ እየነዱ ፣ መጥተዋል ።

ከውስጥ ፣ ዳሱ ፣ ሺህ ፣ ጊዜ ፣ እንደጐላ ፣ የንብ ፣ ቀፎ ያተማል ። ከጓሮ ፣ ዘፈን ፣ ይደለቃል ። ሶስት ፣ አራት ፣ አዝ ማሪዎች ፣ ቆመዋል ። አንደኛው ፣ ሰንጎ ፣ መገን ፣ ይላል ሌላው ፣ ከሚስቱ ፣ ጋር ፣ ይቀባበላል ። ሶስተኛው ፣ አዝ ማሪ ።

« ባላምባራስ ፣ ክንፉ ፣ ደስ ፣ ይበልህ ፣ ደስ ፣

ፈረስ ፣ ያስጋልባል ፣ የሠራኸው ፣ ዳስ ፣ » የሚለውን ግጥም ፣ እየደጋገመ ፣ ዘለሰኛ ፣ ይመታል ። በእርግጥም ዳሱ ፣ ፈረስ ፣ ያስጋልባል ። ግቢው ፣ በሞላ ፣ ዳስ ፣ ሆኖ ነበር ። በዚያ ፣ ላይ ፣ አግዳሙ ፣ ተጥሎ ፣ ቤቱ ፣ ባንድ ወገን ፣ ወንዱ ፣ ባንድ ፣ ወገን ፣ እንደዕድሜውና ፣ እንደ ብሩ ፣ ተቀምጧል ። ባላምባራስ ፣ ወደ ፣ ትልልቆቹ ፣ እን ውንት ፣ እየሄዱ ፣ ያጐነብሱና ፣ « ኧረ ፣ ባካችሁ ! ሰው የወለደውን ፣ ካልላሙለት ፣ የደገሰውን ፣ ካልበሉለት እያሉ ፣ ይለምናሉ ።

ዳሱ ፣ መሙላት ፣ ሲጀምር ፣ አንድ ፣ ጐረምሳ ፣ እያ ለኸለኸ ፣ ገብቶ ፣ ለባላምባራስ ፣ በጆሮዋቸው ፣ ሹክ ፣ አላ ቸው ። « የት ፣ ደርሰዋል ? » ሲሉ ፣ ጠየቁት ።

« ፈፉውን ፣ ሳይሻገሩ ፣ አይቀሩም » አላቸው ። የሠ ርገኛውን ፣ መዳረስ ፣ እንዲያስታውቅ ፣ የተላከ ፣ ነበር ። ለዘ ገዩ ፣ ዕድምተኞች ፣ ጠባብ ፣ መተላለፊያ ፣ ትቶ ፣ በሩ ፣ በአጣናና ፣ በጨፈቃ ፣ ተዘ ና ፣ በዱላና ፣ በትግል ፣ የታ ወቁ ፣ የደብሩ ፣ ጐረምሶች ፣ ዱላቸውን ፣ ይዘው ፣ ዘብ ፣ ቆሙ ።

የሠርገኛው ፣ ሆታ ፣ እየቀረበ ፣ ሲሄድ ፣ ከዳሱ ፣ ውስጥ ትርምሱና ፣ ጥድፊያው ፣ ይበልጥ ፣ እየተተራመሰ ፣ የሴት ፣ ጭፋሮና ፣ ዘፈን ፣ እየደመቀ ፣ ሄደ ። ሠርገኛው ፣ ደረሰና ፣ ከኋላው ፣ እንደተነዳ ፣ ከብት ፣ አንዱ ፣ ከፊቱ ፣ ያለውን ፣ እየገፋና ፣ እየተጫነ ፣ ከበሩ ፣ አጠገብ ፣ ተገጠገጠ ። ሙሽ ራው ፣ በጥቂት ፣ ሚዜዎች ፣ ታጅቦ ፣ ከበቅሎው ፣ ሳይወ ርድ ፣ ወደዳር ፣ ቆመ ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ሲሆን ፣ ጭፋሮው ፣ አላቋረጠም ።

ይበላሃል ! ይበላሃል ! ጅቦ !
ይበላሃል ! ይበላሃል ! ጅቦ !
ይበላሃል ፣ ይጐረምድሃል !
ይበላሃል ! ይበላሃል ፣ ጅቦ ! !

ጥቂቶቹ ፣ ከመሐል ፣ ሆነው ፣ ወደላይ ፣ እየዘለሉና ፣ ላቸውን ፣ እያጋጩ ፣ በመጨፈር ፣ ሲያቀነቅኑ ፣ ሌሎች ፣ ቀበሌዋቻቸው ፣ ጥቂት ፣ እንደቆዩ ፣ « ከፊት ፣ በለው ፣ ሩን ! ከፊት ፣ በለው ፣ በሩን ! » ሲል ፣ አንዱ ፣ ጮኸ ። ፊት ፣ በለው ! በሩን ፣ ከፊት ፣ በሩን ! ሲል ፣ ሁሉም ፣

ትንሚሚና ፡ ፊቱን ፡ ወደበራፉ ፡ መልሶ ፡ ጥሶ ፡ የሚገባ ፡ መሰለ ።

ከውስጥ ፡ በኩል ፡ የጐረምሳ ፡ ቡድን ፡ « ተው ፡ ተመለስ ፡ ትበላለህ ! ኋላ ፡ ውርድ ፡ ከራሴ ፡ ነው ! » የሚል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰማ ። ከኋላ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሠርገኛ ፡ አትለውም ! ጣሰውና ፡ ግባ ! እያለ ፡ ሲጋፋ ፡ ከፊት ፡ ያለው ፡ ጐረምሳ ፡ ዱላውን ፡ ቃጥቶ ፡ ፈራ ፡ ተባ ፡ ይላል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደሽመል ፡ ምከታ ፡ ጨዋታ ፡ የሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ዱላ ፡ ኳ ! ኳ ! ይጋጫል ። የሴት ፡ ወገን ፡ ቡድን ፡ «ተው ፡ ደም ፡ እንዳይፈስ ! » እያለ ፡ ይፎክራል ።

የወንድ ፡ ወገን ፡ ሠርገኛ ፡ ትንሽ ፡ ወደኋላ ፡ አፈገፈገና ፡ ክብ ፡ ሠርቶ ፡ ሆታውንና ፡ ጭፈራውን ፡ ቀጠለ ። ጥቂቶቹ ፡ ቀንደኛ ፡ አጃቢዎች ፡ ከወደጀርባ ፡ በኩል ፡ ክምችች ፡ ብለው ፡ ተመካከሩና ፡ በር ፡ አስከፋቹን ፡ መረጡ ። የተመረጠው ፡ ጐረምሳም ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ጥምጥሞት ፡ የነበረውን ፡ ነጠላ ፡ ፈትቶ ፡ አጣፍቶ ፡ ለበሰና ፡ ደበቅ ፡ ብሎ ፡ በመለየት ፡ ዕድምተኛ፡ መስሎ ፡ ኩምሽሽ ፡ እያለ ፡ መጣ ። ከፊቱ ፡ አስር ፡ ክንድ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ አዛውንት ፡ ገቡ ። ተከታትሎ ፡ ሊገባ ፡ ሲል ፡ « ተመለስ !» አለው ፡ የውስጠኛው ፡ ጐረምሳ ።

« ምነው ? »

« ምንድን ፡ ነህ ? »

«እኔ ፡ የተጠራሁ ፡ እድምተኛ ፡ ነኝ !» በር ፡ አስከፋቹ ፡ ጨዋነቱ ፡ የተደፈረ ፡ ለማስመሰል ፡ ፊቱን ፡ ኮስተር ፡ አደረገ ።

« ማን ፡ ልበል ? » ሲል ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ጐረምሳ ፡ በፌዝ ፡ ጠየቀ ።



« ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡ » አለ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የገቡትን ፡ አዛውንት ፡ በዓይኑ ፡ እያመለከተ።

« ከማን ፡ ጋር ? ከአብዬ ? » ብሎ ፡ ጐረምሳው ፡ ዱላውን ፡ ሲሰነዝርበት ፡ በር ፡ አስከፋቹ ፡ ለመመከት ፡ ከነጠላው ፡ ሥር ፡ የደበቀውን ፡ ዱላ ፡ ሲያወጣ ፡ ሠርገኛና ፡ በር ፡ ጠባቂ ፡ እንደገና ፡ ቁርቁስ ፡ ጀመሩ ። አንድ ፡ ሶስቱ ፡ ተፈነከቱ ። ከወንድ ፡ ወገን ፡ የነገር ፡ አባት ፡ ለመገላገል ፡ ሲቀርቡ ፤ ከውስጥ ፡ በሩ ፡ እንዲከፈት ፡ ታዘዘ ። ጨፈቃው ፡ ተነሣላቸው ። ግን ፡ አሁንም ፡ መንገዱ ፡ አልተለቀቀላቸውም ።

ሴቶች ፡ « አላስገባም ፡ ሠርገኛ ፡

ከውጭ ፡ ይተኛ !

በየት ፡ መጣ ፡ ዞሮ ፡ በየት ፡ መጣ ፡ ዞሮ ፡

የሚዜ ፡ ዝንጀሮ ፡ » እያሉ ፡ በመጨፈር ፡ ከመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ሠርገኛውን ፡ አገዱት ። ጐረምሳ ፡ አጃቢ ፡ ግን ፡ ኮረዳዋን ፡ እየጐነታተለና ፡ እየገፈተረ ፡ ጥሶ ፡ አለፈ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ሠርገኛ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ ተርታ ፡ ያዘ ። የነገር ፡ አባት ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሚዜዎች ፡ ቀደሙ ። ሙሽራው ፡ ከበቅሎው ፡ ወረደና ፡ በጥቂት ፡ ኦጃቢዎች ፡ ተጋርዶ ፡ ቆመ ። ሽማግሌዎቹና ፡ ሚዜዎቹ ፡ ከዳሱ ፡ ውጭ ፡ ጥግ ፡ ይዞ ፡ በተነጠፈ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ወደተቀመጡት ፡ የሴት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ቀረቡ ።

« ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ቆማችኋል ? » ሲል ፡ ከተቀመጡት ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ጠየቀ ።

የወንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ወደፊት ፡ ቀደሙና ፡ « ልጅ ፡ ታደርጉን ፡ ብለን ፡ » ሲሉ ፡ ጮኽ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

« እጃችሁ ፡ ከምን ? »

« ከሸማ ፡ ጥቅል ፡ ከወርቅ ፡ እንክብል ፡ »

« የልጃችን ፡ ማደሪያስ ? » ሲሉ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ፡ ጠየቁ ።

« ማደሪያ ? » የወንድ ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ፡ መልሰው ፡ ጠየቁ ። « ማደሪያማ ፡ ሞልቶ ፡ ተርፎ ! አስራ ፡ ሁለት ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፡ ሃምሳ ፡ ሰባት ፡ ጥገት ፡ መቶ ፡ አስራ ፡ ሶስት ፡ ወይፈንና ፡ ዘጠና ፡ አራት ፡ ጊደር ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ ጥጃ ፡ ስምንት ፡ ጋሻ ፡ የጤፍ ፡ መሬት ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ ጋሻ ፡ የጭሰኛ ፡ መሬት ፡ በወሎ ፡ አምስት ፡ የገባር ፡ መሬት ፡» ሽማግሌው ፡ ተግ ፡ አሉ ።

« አሄሄ ! ልጃችን ፡ ቤትም ፡ ዕቃም ፡ የላትም ? » የሴት ፡ ሽማግሌ ፡ እንደመቆጣት ፡ ቃጣቸው ።

« ሁለት ፡ ቤት ፡ ከእልፍኝ ፡ እስከጓዳው ። ቦስት ፡ አልጋ ፡ አስር ፡ እንስራ ፡ አምስት ፡ ጋን ። »

« አይበቃም ! »

« ሰባት ፡ ለት ፡ በምንት ፡ ጀንዲ ፤ አስራ ፡ ሰባት ፡ አጐዛ ፡ አስራ ፡ ሶስት ፡ ቢላዋ ፡ አስራ ፡ ዘጠኝ ፡ የቀንድ ፡ መለኪያ ፡ አስራ ፡ አንድ ፡ ኩላብ ፡ ዋንጫ ፡ »

« ጨምሩበት ! »

የወንዱ ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ፡ ጥቂት ፡ አሰቡ ፡ « ይህኒ ፡ የራስ ፡ አገር ፡ ያሳድር ፡ ነበር ። ሰላሣ ፡ ሁለት ፡ አህያ ፡ ስድስት ፡ ሰጋር ፡ በቅሎ ፡ ሶስት ፡ ባዝራ ፡ ሰባት ፡ ሰንጋ ፡ ፈረስ ፡ ከነኮረቻውና ፡ ከነጌጡ ፡ »



« አሁንም ፡ ቀርቷል ፡ » የሴት ፡ ሽማግሌ ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ጸጉራቸውን ፡ ፎከቱ ።

« እሽ ፡ እስቲ ፡ በሉ ፡ ግዴየለም ፡ » አሉ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ፡ « ጥሎሻችሁን ፡ ደግሞ ፡ እንይላችሁ ! » አጠያየቃቸው ፡ እንደሽሙጥ ፡ ቢጤ ፡ ነበር ።

ሶስተኛው ፡ ሚዜ ፡ በከረጢት ፡ ቋጥሮ ፡ ታቅፎት ፡ የነበረውን ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ በቁሙ ፡ እንዳለ ፡ ከተነጠፈው ፡ ለት ፡ ላይ ፡ ዘረገፈው ። ቹ ቹ ቹ ቹ ቹ ቹ ለቱን ፡ ሞላው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንገቱን ፡ አስግጎ ፡ ተመለከተ ። አይ ! ደህና ፡ ነው ። አላነሰም ። ብሩ ፡ የተዘረገፈበትን ፡ ለት ፡ አንዱ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ጐረምሳ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ከደንደን ፡ ሲያደርገው ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የተሸከሙት ፡ አጃቢዎች ፡ ቀረቡ ። በመጀመሪያ ፡ የሙሽራዋ ፡ ጥልፍ ፡ ቀሚስና ፡ ቀጭን ፡ ጥለት ፡ ኩታ ፡ ወጥቶ ፡ ተሰጠ ። ተረካቢው ፡ ከንፈሩን ፡ በፌዝ ፡ አጣመመ ።

ሌላው ፡ የራስ ፡ ሻሽ ፡ ወለባ ፡ አምባር ፡ ጉትቻ ፡ የብር ፡ መስቀል ፡ አሸን ፡ አልቦ ፡ የግር ፡ አልቦ ፡ አወጣና ፡ አስረከበ ።

«ይኸው ፡ ነው ፡ እንዳትሉ ! ዕድሜ ፡ የማያሳየው ፡ ጉድ ፡ የለም ። ልጃችን ፡ ርቃን ፡ ሥጋዋን ፡ ትሒድ ፡ አትሉም ? » ሲሉ ፡ ከተቀመጡት ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ አፈጮሌ ፡ አዛውንት ፡ አሾፉ ።

የወንድ ፡ ወገን ፡ ሥርገኞች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩና ፡ ቀንደኞቹ ፡ አንገታቸውን ፡ አቀርቅረው ፡ ተመካከሩ ። ከወደመሐል ፡ ሌላ ፡ ቀረጢት ፡ ተፈታና ፡ የናት ፡ ጥሎሽ ፡ ኩታና ፡ ቀሚስ ፡ ተሰጠ ።

« እሆ ! ሆ ! እናንተስ ፡ የማታፍሩ ፡ ጉደኞች ፡ ናችሁ ! » አሉ ፡ እኒያው ፡ አፈጮሌ ። ለወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ አምባር ፡ ጉትቻና ፡ አሸን ፡ አልቦ ፡ ተጨመረላቸው ።

« እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ማን ፡ የታል ? » ሲሉ ፡ ተቀማጭ ፡ አዛውንት ፡ ጠየቁ ። የወንድ ፡ ወገኖች ፡ በድንጋጤ ፡ ክው ፡ አሉ ። በገምቦ ፡ ከተመረገ ፡ በኋላ ፡ ተረስቶ ፡ ቀርቷል ። የሴት ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ አወካባቸው ።

« የለም ። ቀኛዝማች ፡ ደግም ፡ አላደረገ ። ብዙ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ቀርቷል ። የለም ! ሰው ፡ አቻውን ፡ ሲፈልግ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ። ለጐደለውም ፡ ለሁሉም ፡ ነገር ፡ ዋስ ፡ ጥሩ ፡ » አሉ ፡ አንዱ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ።

« ግራዝማች ፡ አየለ ፡ ይዋሱን ! » ሲሉ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ የነገር ፡ አባት ፡ ከተቀመጡት ፡ አዛውንት ፡ አንዱን ፡ ጠየቁ ።

« በጐደለው ፡ ሁሉ ፡ ዋስ ፡ ነኝ ፡ » ሲሉ ፡ ቆመው ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሙሽራው ፡ ከእነአጃቢው ፡ በአስተናባሪ ፡ ተጋብዞ ፡ ከዳሱ ፡ አናት ፡ በኩል ፡ በጨፈቃ ፡ ተገድግዶ ፡ በኩታ ፡ የተጋረደ ፡ የጫጉላ ፡ ቤቱ ፡ ተከልሎ ፡ ተሰጠው ። ከዚህያም ፡ የጫጉላ ፡ ቤቱ ፡ ሞሰብ ፡ በግምጃ ፡ ተሸፍኖ ፡ ቀደመና ፡ ተከታትሎ ፡ እየተጋዘ ፡ ማዕድ ፡ ቀረበ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የአሳላፊው ፡ ግርግር ፡ ዘፈኑ ፡ ጭፋሮው ፡ የአዝማሪው ፡ ዘለሰኛ ፡ እየደመቀ ፡ ሄደ ።

ሴቶች ባንድ ፡ በኩል ፤



« ኩራት ፡ ኩራት ፡ አይልሽም ፡ ወይ ?
የክንፉ ፡ አይደለሽምይ ፡
ኩራት ፡ አይልሽም ፡ ወይ ፤
የእልፍነሽ ፡ አይደለሽምይ ፤ »

የአያት ፡ የአጐት ፡ የወንድም ፡ የዘመድ ፡ የአክስት ፡ የዚያም ፡ የዚያም ፡ ስም ፡ እየተጠራ ፡ « ኩራት ፡ አይልሽም ፡ ወይ ፡ » እየተባባሉ ፡ እስክስታውን ፡ ያወርዱታል ።

ጐረምሶች ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ይጨፍራሉ ፡
ሎጋው ፡ ሽቦ ፡ ና !
ሎጋው ፡ ሽቦ !
ጉሮ ፡ ወሸባየ ፡ ጉሮ ፡ ወሸባ ፡

እንዲያ ፡ እንዲያ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ግዳይ !

አገጫቸውና ፡ አፍንጫቸው ፡ በጥላሸት ፡ የተለቀለቀ ፡ ሴቶች ፡ ድስቱንና ፡ ወጭቱን ፡ ይዘው ፡ በተርታ ፡ ሲገቡ ፡ በጥሎሽ ፡ ላይ ፡ የደረሰበትን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ሚዜና አጃቢ ፡ አሰፈሰፈ ። እንደጥሎሽ ፡ ተቀባዮቹ ፡ ከዚህም ፡ አፈጮሌውና ፡ ብልት ፡ አዋቂው ፡ ጣቱን ፡ እያሾለ ፡ ቀረበ ።

«ጉድ ፡ በሉ ! በሀገራችሁ ፡ ዶሮ ፡ ብልት ፡ የላትም ?» ሲል ፡ ራሱን ፡ ይዞ ፡ እንደመጮህ ፡ ይቃጣዋል ።

ግን ፡ ወጥ ፡ አቅራቢዎቹም ፡ የተመረጡ ፡ ስለነበሩ ፡ በነገር ፡ አልተሰናነፉም ። « በሀገርህ ፡ ዶሮ ፡ ብልተህ ፡ የምታውቅ ፡ ከሆነ ፡ ቆጥረህ ፡ ድረስበት ። ሽምብራ ፡ መቸርፈስ ፡ አይምሰልህ ! » የሚል ፡ መልስ ፡ ይሰጠዋል ።

« መላላጫው ፡ የታል ? »

« ኧረ ፡ ጉድ ፡ በይኝ ፡ አንቺዬ ፡ መላላጫ ፡ የማያውቀው ፡ መጣ ! ይህ ፡ ምንድን ፡ ነው ? »

« ሳምባቃፊው ፡ የታል ? »

«በሀገራችሁ ፡ ከጨዋ ፡ ፊት ፡ ይቀርባል ፡ እንዴ ? በኛ ፡ የአሽከር ፡ ምግብ ፡ ነው ፡ »

አንዱ ፡ ጕረምሳ ፡ እጁን ፡ ሰደድ ፡ አድርጎ ፡ ወጥ ፡ አውጭዋን ፡ ኮረዳ ፡ ለመቆንጠጥ ፡ ይሞክራል ።

« ወይድ ! የት ፡ መጣ ፡ ባለጌ ፡ ነው ! »

ወጥ ፡ የተነከረ ፡ እጅ ፡ ለጥፊ ፡ ይቃጣበታል ።

የወንድ ፡ ወገን ፡ ጠላውን ፡ ጠጁን ፡ ወጡን ፡ እንዲያው ፡ ማር ፡ ቅጠሉን ፡ እያጣጣለ ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡ መሸትሸት ፡ ሲል ፡ ለጭፋሮ ፡ ተነሣ ። መልሶ ፡ የራት ፡ ድግስ ፡ ቀረበ ።

ከራት ፡ በኋላ ፡ የወንድ ፡ ወገንና ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ውድድር ፡ ገጥሞ ፡ ሲጨፍርና ፡ ሲሸልል ፡ አንዱ ፡ ነገረኛ ፡ የደመኛ ፡ ስም ፡ በመጥራቱ ፡ የተፋፋመ ፡ አምባጓሮ ፡ ተነሣ ። ሰው ፡ አልተጐዳም ፡ እንጅ ፡ አንድ ፡ ሶስት ፡ ጥይት ፡ ተተኮሰ ። መምሬ ፡ ወልዳረጋይና ፡ ሌሎችም ፡ ሽማግሌዎች ፡ በመካከል ፡ ገብተው ፡ አምባጓሮውን ፡ አበረዱት ። ባላምባራስ ፡ ክንፉም ፡ ነገሩ ፡ ተባብሶ ፡ ደም ፡ እንዳይፈስ ፡ ጕረምሶቻችውን ፡ ገሰጹዋቸው ።

ጭፋሮውና ፡ ዘፈኑ ፡ በመፈራራትም ፡ በመጠንቀቅም ፡ ሁናቴ ፡ አነጋ ። የሚዜዎቹ ፡ አንዱ ፡ ሙክራ ፡ አሽከር ፡ በመምሰል ፡ እልፍኝ ፡ ገብተው ፡ ሙሽራይቷን ፡ ለማየት ፡



ነበር ። ግን ፡ ነጠላ ፡ ቀሚስ ፡ አድርገው ፡ በመልበስ ፡ ገረድ ፡ መስለውም ፡ አልሆንላቸውም ።

ጢት ፡ ከቁርስ ፡ በኋላ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሚዜዎች ፡ « እንግዲህ ፡ በላን ፡ ጠጣን ፡ ልጂቷ ፡ ትሰጠንና ፡ እሰናብቱን ፡ » ሲሉ ፡ ጠየቁ ።

« ምንድን ፡ ነው ፡ ጥድፊያው ? » የሚል ፡ የቁጣ ፡ ጥያቄ ፡ ቀረበላቸው ።

«መንገዳችን ፡ ሩቅ ፡ ነው ፡ »

« የሆነ ፡ እንደሆንስ ! ለዚህ ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፡ ጥሎሻችሁ ፡ ደግሞ ፡ ልጃችን ፡ በጢቱ ፡ የምትጐተትበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ! »

« ካላችሁስ ፡ ለዚህ ፡ ብጥብጥ ፡ ምግባችሁና ፡ ቅራሪ ፡ ጠላችሁ ፡ የምናረፍድበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። »

« እንዴት ! በመጣችሁበት ፡ መንገድ ፡ ሂዱ ። ሴት ፡ ልጅ ፡ የለንም ! » አሉ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ።

« እናንተው ፡ አግቧት ! » ሲል ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ሙሴ ፡ መለሰ ።

ንትርኩ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ተፈቀደላቸውና ፡ አሁንም ፡ ሙሽሪት ፡ ከእልፍኝ ፡ እስክትወጣ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ሆነ ።

ሙሽሪት ፡ ተሸፋፍና ፡ ሁለት ፡ ደንገጡር ፡ አስከትላ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ታጅባ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ ሌላ ፡ መጣሪያና ፡ ዕቃ ፡ የያዙ ፡ አሽከሮች ፡ በተርታ ፡ መጡ ። ባላምባራስ ፡ ክንፉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ሌሎችም ፡ የቅርብ ፡ ቤተ ፡

ዘመዶች ፡ ካንድ ፡ በኩል ፡ በተርታ ፡ ቈመዋል ። ከሌላ
በኩል ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ሙሽራውን ፡ ከቦ ፡ ተገጥግጧል ፡

ባላምባራስ ፡ አሽከራቸውን ፡ በዓይናቸው ፡ ሲጠቅሰ
ያንን ፡ የሚወዱትን ፡ መውዜር ፡ ይዞ ፡ ሲቀርብ ፡ ተቀበ
ሉና ፡ እጃቸውን ፡ ወደሙሽራው ፡ ዘረጉ ። በሙሽራው ፡
ፈንታ ፡ አንደኛው ፡ ሚዜ ፡ ተቀበለ ። ለሁለቱ ፡ ሚዜዎች ፡
ሚኒሽር ፡ ለሶስተኛው ፡ ሚዜ ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፡ ሸለሙ ።

ባላምባራስ ፡ «እርስዎም ፡ ከነርሱ ፡ በኩል ፡ ነዎት ፡
መሰል ፡ » አሉና ፡ ለመምሬ ፡ ወልዳረጋይ ፡ ያን ፡ ከእጃ
ቸው ፡ የማይለዩትን ፡ ድርሳነ ፡ ሚካኤል ፡ ዘረጉላቸው ።

« ኧረ ፡ በበዛይት ፡ ዓለሟ ፡ ምን ፡ አመጡብኝ ! ድር
ሳነ ፡ ሚካኤልምን ? » ሲሉ ፡ መምሬ ፡ አገረገሩ ።

« ይቀበሉኝ ፡ አልኩዎ ! » ሲሏቸው ፡ መምሬ ፡ ተቀ
በሉ ።

ሙሽሮቹ ፡ ከበቅሎዋቸው ፡ ወጥተው ፡ ሠርገኛው ፡
ሆ ! እያለ ፡ ጉዞ ፡ ሲጀምር ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ዕንባቸ
ውን ፡ በነጠላቸው ፡ እየጠራረጉ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገቡ ። ጥቂት ፡
ቆይቶ ፡ ባላምባራስ ፡ ዕንባቸውን ፡ ለመዋጥ ፡ ከንፈራቸ
ውን ፡ እንደመንከስ ፡ እያደረጉ ፡ ከሌሎች ፡ ቤት ፡ ዘመ
ዶች ፡ ጋር ፡ ወደዳሱ ፡ ገቡ ።

በወሩ ፡ ገደማ ፡ እሑድ ፡ ቀን ፡ መልስ ፡ ሆነ ። ሙሽራ ፡
አንድ ፡ ሰላሣ ፡ ራሱን ፡ መጣ ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ የድግሱን ፡ አቀራረብ ፡ ጥቂት ፡
ጊዜ ፡ ከተቆጣጠሩ ፡ በኋላ ፡ ምግቡም ፡ መጠጡም ፡ ጭ
ፈራውም ፡ ሲያያዝ ፡ ልጃቸው ፡ ወዳለችበት ፡ እልፍኝ ፡



ገቡ ። ሙሽራው ፡ ግን ፡ ከአጃቢዎቹ ፡ ጋር ፡ በዳሱ ፡ ው
ስጥ ፡ ጫጉላ ፡ ቤት ፡ ተጋርዶ ፡ ተሰጥቶታል ።

ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ልጃቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ አድርገው ፡
ጠየቋት ። ለማረጋገጥ ፡ ያህል ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ታሪኩን ፡
ከመንደር ፡ ሽውሽታ ፡ ከዚያም ፡ ደንገጡሯ ፡ ለመጠየቅ ፡
ስትመጣ ፡ ነግራቸው ፡ ነበር ። መልሱን ፡ የደገሱትም ፡
ባንድ ፡ በኩል ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ውርደት ፡ እንደማይደር
ስባቸው ፡ ተስፋና ፡ ጸሎት ፡ እያደረጉ ፡ በሌላ ፡ በኩልም ፡
ሆዳቸውን ፡ እያመማቸው ፡ ነው ። የልጃቸውን ፡ ታሪክ ፡
እንደሰሙ ፡ ሰውነታቸው ፡ እየተርበደበደ ፡ ወደዳሱ ፡ ሄ
ዱና ፡ ባላቸውን ፡ በጆሮዋቸው ፡ ሹክ ፡ ብለው ፡ በክንዳ
ቸው ፡ እየጐተቱ ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ አመጧቸው ።

« ምን ፡ ሆነሻል ? » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ክንዳቸውን ፡
እንደመንጠቅ ፡ እየከጀሉ ።

« ና ፡ እንጅ ፡ የልጅህን ፡ጉድ ፡ ስማ ፡ »

« የምን ፡ ጉድ ፡ » ከእልፍኝ ፡ ገቡ ።

« እንዲሁ ፡ ሾላ ፡ በድፍን ፡ ሆና ፡ መጥታልሃለች ! »
አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ በንዴት ፡ ከንፈራቸውን ፡
አሞድሙደው ።

« ምን ! » ሲሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ከቆሙበት ፡ ተወራጩ ።

« ምን ፡ ምን ፡ አለው ? የአገር ፡ መሳለቂያ ፡ መሆን ፡
ነው ፡ እንጅ ፡ » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ትከሻቸውን ፡
ነቅነቅ ፡ አደረጉ ።

« እኮ ፡ ምንድን ፡ ነው ? » ባላምባራስ ፡ ጣታቸውን ፡
አንገቷን ፡ ደፍታ ፡ በተቀመጠችው ፡ ልጃቸው ፡ ላይ ፡
ቀሰሩ ።

« እየነገርኩህ ፡ ! » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ቀበል አደረጉ ።

« አንቺ ፡ ዝም ፡ በይ ፡ ሴትዮ ! መዓትሽን ፡ እታውሪ ፡ እርሷው ፡ ትንገረኝ ፡ ነው ፡ የምለው ! » ባል ፡ መሆን ፡ አቅቷቸው ፡ ውርደቱን ፡ ያመጡት ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ ይመስል ፡ ባላምባራስ ፡ ዓይናቸውን ፡ አፈጠጡባቸው ።

« እኮ ፡ በይ ፡ ተናገሪ ! » ሲሉ ፡ ወደልጃቸው ፡ ቀረቡ ።

ሙሽሪት ፡ ጭንቅላቷን ፡ ከጉያዋ ፡ ውስጥ ፡ ለመደበቅ ፡ የምትሞክር ፡ ይመስል ፡ ይበልጥ ፡ አቀረቀረች ።

« ምኑን ፡ ትነግርሃለች ፡ እርሷ ! » አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ።

« የሆነውን ፡ ነዋ ! »

« ምን ፡ ሆነና » ሲሉ ፡ እናት ፡ እሸፉ ።

ባላምባራስ ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ገረፋዋቸው ።

ሙሽሪት ፡ የጫጉላው ፡ ሰሞን ፡ እንግልት ፡ ስቃይና ፡ ሰቀቀን ፡ በሐሳቧ ፡ ታያት ። ሚዜዎች ፡ እጅና ፡ እግሯን ፡ ሲይዟት ፡ ሰው ፡ ሲተናነቃት ፡ ከውጭ ፡ ጩኸትና ፡ ጭፈሮ ፡ ሲደባለቅ ፡ በፍርሃት ፡ አእምሮዋን ፡ ስትስት ፡ መልሳ ፡ ስትነቃ ፡ መልሰው ፡ ሲይዟት ፡ በበነጋው ፡ ደንገጡሯዋ ፡ መከራ ፡ ባታፅናናት ፡ ኖሮ ፡ በጠፍ ፡ ጨረቃ ፡ ለመጥፋት ፡ የከጀለችበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

« አንድ ፡ ቀን ፡ » አለች ፡ ሙሽሪት ፡ አንገቷን ፡ ቀና ፡ ሳታደርግ ፡ « እናቲቱ ፡ ከርሱ ፡ ጓደኞች ፡ ጋር ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ቆዩና ፡ ልጁ ፡ አንድ ፡ አዚም ፡ ዞሮበት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ በጤናው ፡ እንዲህ ፡ አይሆንም ፡ አሉና ፡ ፀጉሬን ፡ በጣታቸው ፡ እያበጠሩ ፡ ደባብሰው ፡ ጉያዬን ፡ ሲፈትሹ ፡ ያንን ፡ አገኙና ፡ »

« ምኑን ፡ ያንን ? » ሲሉ ፡ ባላምባራስ ፡ አቋረጧት ።

« ያሠርኩትን ፡ ክታብ ፡ »

« የምን ፡ ክታብ ! » ባላምባራስ ፡ ከንዴታቸው ፡ ጋር ፡ እንደመገረም ፡ አሉ ።

« ኧረ ፡ እንዲያው ፡ ለራስ ፡ መጠበቂያ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልፋፈ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ፡ መለሱ ።

« በቤቱም ፡ የማላውቀው ፡ጉድ ፡ ሞልቷል ! እሺ ፡ ቀጥይ ፡ ግዴለም ፡ ! »

« ከዚያም ፡ እናቲቱ ፡ አሽቀንጥረው ፡ ጣሉትና ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ መጥተው ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ቤቱንና ፡ ዙሪያውን ፡ ጠበል ፡ ረጩበት ። ክታቡ ፡ በወደቀበት ፡ ሥፍራም ፡ እንጨትና ፡ ጭራሮ ፡ አቀጣጥለው ፡ አነደዱበት ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ - - - »

ባላምባራስ ፡ ታሪኳን ፡ እስክትጨርስ ፡ አልጠበቁም። የአፍንጫቸው ፡ ቅጠል ፡ እጥፍ ፡ ዘርጋ ፡ እያለ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ በከባዱ ፡ ተነፈሱና ፡ አንዳችም ፡ ቃል ፡ ሳይናገሩ ፡ ወደዳሱ ፡ ተመለሱ ።

ለነገሩ ፡ ባላምባራስም ፡ ወይዘሮ ፡ እልፍነሽ ም ፡ እንግዶቻቸውን ፡ ሲጋብዙ ፡ አምሽተዋል ። ግን ፡ ፊታቸው ፡ ያሳጣ ፡ ነበር ። ሚዜዎቹም ፡ እንደሠርጉ ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡

ልብ ፡ ተዝናንተውና ፡ ተመክተው ፡ አልጨፈሩም ። ነጠላ፡ አደግድጎ ፡ መወዛወዙ ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ ለወግ ፡ ያህል ፡ ነበር ። አየሩ ፡ ቀዝቅዝዋል ። ሰውም ፡ ቀዝቅዞ ፡ አደረ ።

ጧት ፡ ከቁርስ ፡ በኋላ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሚዜዎች ፡ እንደተለመደው ፡ አሰናብቱን ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። እንደተለመደውም ፡ ሙሽራው ፡ ግን ፡ ከአማቾቹ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋር ፡ በበለጠ ፡ ለመተዋወቅ ፡ ይሰነብት ፡ ነበር ።

« ይሂዱ ፤ ሂዱ ፡ እንጅ ፡ ይረፍድባችኋል ፡ ወዳጆቼ ። እርሱም ፡ ይሂድ ። አውቀነዋል ። ተዋውቀናል ። ልጃችን ፡ ግን ፡ ከዚሁ ፡ ትቆያለች ፡ » አሉ ፡ ባላምባራስ ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ንዴትና ፡ ጸጸት ፡ በጉልህ ፡ እየተነበበ ። አውቀነዋል ፡ ሲሉ ፡ ፌዛቸው ፡ እንደጦር ፡ የሚዋጋ ፡ ነበር ።

እንደተለመደው ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አለልመኑም ። አልተከራከሩም ። አላንገራገሩም ። ምናልባትም ፡ ካለጠመንጃ ፡ አፈሙዝ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ የማይለውጠው ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፡ መሆኑን ፡ አውቀዋል ።

እንደ ፡ አለፈው ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራው ፡ ከበቅሎ ፡ እስኪወጣ ፡ ባላምባራስ ፡ ቆመው ፡ አልሸኙትም ፡ ነበር ። የሚናገሩትን ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ገቡ ። ግን ፡ አላስችላቸው ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ወጥተው ፡ ሠርገኞቹ ፡ ዳገቱን ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ተመለከቱ ።

—ልጇስ ፡ ባል ፡ አታጣም ። ድርሳኔም ፡ ደህና ፡ ባለቤት አግኝቷል ። አይቆጨኝም ። ከሴት ፡ እጅ ፡ የገባው ፡ መውዜሬ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በማሰብ ፡ ባላምባራስ ፡ ራሳቸውን ፡ ነቀነቁ ።



# ቾማ ።

አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ልጃቸው ፡ ቴሲ ፡ ለዓቅመ ፡ አዳም ፡ መቃረቡን ፡ የተገነዘቡት ፡ ከአምናው ፡ መስቀል ፡ አንስቶ ፡ ነበር ። ሴቶች ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ወንዶች ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሆነው ፡ ላላ ፡ ሽቦ ፡ ላላ ፡ እያሉ ፡ ሲጨፍሩ ፡ አዛውንት ፡ ከዳር ፡ ሆነው ፡ ሲመለከቱ ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፤ ቴሲ ፡ ባፈረጠመ ፡ ጡንጫው ፡ ላይ ፡ ላቡ ፡ እየተንቆረቆረ ፡ ሲወርድ ፡ አይተው ፡ ለስሜት ፡ መብቃቱን ፡ ተረዱ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሥራዬን ፡ ብለው ፡ በጥብቅ ፡ ባይዙትም ፡ ለልጃቸው ፡ ሚስት ፡ ማቅረብ ፡ የሚችል ፡ ቤተሰብ ፡ ከማሰብና ፡ ከማማረጥ ፡ አልቦዘኑም ፡ ነበር ።

ቴሲ ፡ ነሐሴ ፡ ቢመጣ ፡ ገና ፡ አስራ ፡ ሰባት ፡ ዓመቱ ፡ ነው ። ከጥጃ ፡ ማገድ ፡ አልፎ ፡ ከከብት ፡ ጥበቃ ፡ ወጥቶ ፡ የእንሰት ፡ ጭፍጨፋውን ፡ አሳይቶ ፡ እርፍ ፡ መያዝ ፡ የጀመረው ፡ አምና ፡ ነበር ። ዘንድሮ ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ በሬ ፡ ጠምዶ ፡ ራሱ ፡ ሲያርስ ፡ ውሎ ፡ ይመለሳል ። አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ይህ ፡ ሲገርማቸው ፡ ከእርሻ ፡ እንደዋለ ፡ በዚያው ፡ አደን ፡ ሂዶ ፡ ሚዳቋ ፡ ገድሎ ፡ ልብሱ ፡ በደም ፡ እንዳይበላሽ ፡ ፈቀቅ ፡ አድርጎ ፡ በአጠና ፡ አንጠልጥሎ ፡ ሲመጣ ፡ አጋዝ፡ ቦርጋ ፡ ከቤታቸው ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ጋያቸውን ፡ ይስቡ ፡ ነበር ። ኩራት ፡ በተመላበት ፡ ፈገግታ ፡ ከግር ፡ እስከራሱ ፡ ተመለከቱትና ፡ መልሰው ፡ በሐሳብ ፡ የአውራ ፡ ጣታቸውን ፡ ጥፍር ፡ ይቸረችሩ ፡ ጀመር ።

ሚስታቸው ፡ ለራት ፡ ቆጮ ፡ ወደሚጋግሩበት ፡ ጓዳ ፡ ገቡና ፡ « ልጅሽ ፡ የሠራውን ፡ አየሽ ? » አላቸው ።

ክብት ፡ አጥፍቶ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፡ የተመለሰ ፡ መስሏቸው ፡ አጀት ፡ ኬርወጅ ፡ ደንገጥ ፡ አሉና ፡ « ምን ፡ ሠራ ? » ሲሉ ፡ ጠየቁ ።

« አደን ፡ ጥሎልሻል ። እንዲህማ ፡ ከሆነ ፡ ሳይተላለፈው ፡ ቀረ ፡ ብለሽ ፡ ነው ። አሆ ! ሆ ! ኧረ ፡ ከጐረቤት ፡ ጣጣ ፡ እንዳያመጣብን ! ከመጭው ፡ መስቀል ፡ አያሳልፈንም ። ደግሞ ፡ ዛሬ ፡ ጉብሉ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂዶ ፡ እየጠፋ ፡ አስቸግሯል ። ምን ፡ ፋይዳ ፡ እንደሚያገኙበት ፡ አይገባኝም ። ከአሁኑ ፡ ታጥቀሽ ፡ ብትነሽ ፡ ይሻላል ። ወደወልቂጤም ፡ ወደ ፡ እንድብርም ፡ ወራርደሽ ፡ ምናምኑን ፡ ብታመጭ ፡ አይከፋም ። » አሉ ፡ ቦርጋ ፡ ጢማቸውን ፡ እያሻሹ ።

« ኤ ! ኤ ! ልጅቷን ፡ አግኝተሃል ? » ኬርወጅ ፡ በመደነቅ ፡ አንገታቸውን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ዘንበል ፡ አድርገው ፡ ጠየቁ ።

« በሐሳቤ ፡ ባወጣ ፡ ባወርድ ፡ እስከአሁን ፡ እኔ ፡ የማውቀው ፡ አላገኘሁም ። ከጌቶ ፡ ቦራሲዩ ፡ ወገን ፡ አንድ ሸርጋ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ የደረሰች ፡ ልጅ ፡ አለችው ፡ ሲባል ፡ ሰምቸ ፡ ነበር ። በጣም ፡ አላስደሰተኝም ፡ » አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ አይናቸውን ፡ እንደመከደን ፡ አድርገው ፡ የሰባት ፡ ቤት ፡ ጉራጌን ፡ ዘር ፡ ማንዘር ፡ ሐረግ ፡ በሐሳባቸው ፡ ለማንበብ ፡ ሞከሩ ። ራሳቸውን ፡ አወዛወዙና ፡ « እስቲ ፡ ነገ ፡ ከሸንጎ ፡ ላይ ፡ ሽማግሎችን ፡ አደራ ፡ ብዬ ፡ እጠይቃለሁ ፡ እንጅ ፡ » ብለው ፡ ወደጋያቸው ፡ ተመለሱ ።

በበነጋው ፡ ከሸንጎ ፡ በኋላ ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ልጅ ፡ በመገረዝ ፡ በመላው ፡ ሰባት ፡ ጉራጌ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ብዙ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚያውቀውን ፡ ግርማን ፡ ይዘው ፡ ሶስቱን ፡



የቸሃ ፡ ቀንደኛ ፡ አዛውንቶች ፡ ለምነው ፡ ከግራር ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀመጡ ። ገራዥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ያለውን ፡ ቤተ ሰብ ፡ ሁሉ ፡ ሲቆጥር ፡ አዛውንቱ ፡ ሐረጉንና ፡ ግንዱን ፡ ሙያውን ፡ ንብረቱንና ፡ ጀብዱዉን ፡ ሲያማርጡ ፡ በተሲዓት ፡ የጀመሩ ፡ ጀንበር ፡ እስከትዘቀዘቅ ፡ አመሹ ። በመጨረሻም ፡ ከምሑር ፡ ቤት ፡ ከአድማጠረ ፡ ነገድ ፡ በዳሞ ፡ ጋማሊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተስማሙ ።

* * *

አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ገደማ ፡ ገማሊ ፡ ከሸንጎ ፡ አርፍዶና ፡ ማዶ ፡ ከጀረትማ ፡ ሠፈር ፡ ዘመድ ፡ ጥየቃ ፡ ውሎ ፡ እንደገባ ፡ ከቤቱ ፡ ተዛንብ ፡ አጐዛ ፡ አስነጥፎ ፡ በአሽከር ፡ እግሩን ፡ ይታጠባል ። ከጋቢው ፡ በታች፡ ግራ ፡ እጁን ፡ እየሰደደ ፡ ወገቡን ፡ ያሻሻል ። ደክሞት ፡ ነበር ። ክብት ፡ መግባት ፡ ጀምሯል ። ሁለቱ ፡ እንግዶች ፡ ውሻውን ፡ በዱላቸው ፡ እየተከላከሉ ፡ ከግቢው ፡ ሲገቡ ፡ ሁለተኛውን ፡ እግሩን ፡ ተለቃልቆ ፡ ሳይጨርስ ፡ ተነስቶ ፡ ተቀበላቸው ።

በየተራ ፡ ጉንጭ ፡ ለጉንጭ ፡ ተሳሳሙና ፡ « እንደምን ሰነበትክ ፡ እንደምን ፡ ሰንብታችኋል ። አገር ፡ ደህና ። ከብት ፡ ደህና ። እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ። ሁሉም ፡ ደህና ፡ » ተባባሉ ።

«በል ፡ እግርህን ፡ ታጥበህ ፡ ጨርስ ፡ ዳሞ ፡ ጋማሊ ፡» አሉ ፡ አንደኛው ፡ አዛውንት ። በችኮላ ፡ ተለቃለቀና ፡ ተያይዘው ፡ ወደቤት ፡ ገቡ ። ጋማሊ ፡ ከባላባትነቱ ፡ በቀር ፡ ደህና ፡ ሀብታም ፡ ነበርና ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ባለሶስት ፡ ተዋረድ ፡ ቤት ፡ አሠርቷል ። የወቅሩ ፡ ጌጥ ፡ ለጉድ ፡ ነው ። ግድግዳው ፡ ከጥርብ ፡ እንጨት ፡ ነው ። ልስላሜው ፡

ጥጥ ፡ የሚያስዳምጥ ፡ ይመስላል ። አንድ ፡ እልፍኝ ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ሶስት ፡ ክፍል ፡ አለው ። አሮጌው ፡ ቤት ፡ የጥጆች ፡ ጋጥ ፡ የአሽከሮች ፡ ቤትና ፡ ማድቤት ፡ ሆኗል ።

እንግዶቹ ፡ የቤቱን ፡ አሠራርና ፡ በየግድግዳውና ፡ በየምሰሶው ፡ የተንጠለጠለውን ፡ መሣሪያና ፡ ጌጣጌጥ ፡ እያደነቁለት ፡ ከመደብ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጡ ፡ «ኧረ ፡ እንዲያው ፡ ዛሬ ፡ አገራችንን ፡ በምን ፡ አወቃችሁት ? አሁንማ ፡ መገናኘቱም ፡ ፈጽሞ ፡ ቀረ ። ጐይታና ፡ ግርማ ፡ እርስዎንማ ፡ ካየሁ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ! ኧረ ፡ እንዲያው ፡ ተራራቅን ፡ ባካችሁ ? » አለ ፡ ዳሞ ፡ ጋሚሊ ።

« ምን ፡ መራራቅ ፡ ብቻ ! እንዳይሆን ፡ ሆነን ፡ ተለያየን ፡ እንጅ ! » ሲሉ ፡ ጐይታና ፡ ግርማ ፡ በቅሬታ ፡ ራሳቸውን ፡ እያወዛወዙ ፡ መለሱ ።

« አይ ! ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሞገመነና ፡ አድማጠረ ፡ እንኳ ፡ አይለያይም ። መቸም ፡ ዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ለየራሱ ፡ ሲኳትን ፡ እንዲያው ፡ መቀራረቡ ፡ ተረሳና ፡ እንጅ ፡ አባቶቻችንማ ፡ በየዕለቱ ፡ በማዕድ ፡ ይገናኙ ፡ ነበር ፡ » ሲሉ ፡ ሁለተኛው ፡ እንግዳ ፡ ተተኩ ።

«አሁንስ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ይከለክላል ?» አለ ፡ ጋሚሊ ።
« ምንም ። እንዲያው ፡ ምንም ! »

አሽከር ፡ ጠላ ፡ አቅርቦ ፡ እየቀዳ ፡ ሰጠ ። « ቡናውን ፡ ቶሎ ፡ አፍሉ ፡ » ሲል ፡ ጋሚሊ ፡ አዘዘ ።

« የለም ! መሽቶብናል ፡ እንሄዳለን ፡ » አሉ ፡ ጐይታና ፡ ግርማ ።



« አሁን ፡ ልትሔዱ ፡ ነው ? »
« ኋላስ ? »

« አንድዬን ፡ አድራችሁ ፡ ነው ፡ የምትሔዱት ! በስንት ፡ ዘመናችሁ ፡ መጥታችሁ ፡ ደግሞ ፡ » ጋሚሊ ፡ እንደመከፋት ፡ አለ ።

« ማደር ፡ ቀርቶ ፡ ብንሰነብትስ ፡ አንጠላ ፡ ነበር ፡ »
« በሞቴ ፡ እደሩ ! »
« የማይሆነውን ! ቤቶቻችን ፡ አላወቁም ። ይጨነቃሉ »
« ታዲያ ፡ በጊዜ ፡ ምሽት ፡ ምን ፡ አመጣችሁ ? »

« ሰው ፡ እግረ ፡ መንገዱ ፡ ሲያመቸው ፡ ዘመድ ፡ አይጠቅም ፡ አሉህ ? » አሉ ፡ ጐይታና ፡ ግርማ ።

« ባልጠየቅ ፡ በቀረብኝ ። ለዚህ ፡ ለዚህስ ፡ ባልመጣችሁብኝ ፡ » አለ ፡ ጋሚሊ ።

« ቤትህን ፡ ደህና ፡ ሠርተሃል ። ለመሆኑ ፡ ቤተሰብህ ፡ ደህና ፡ አፍርቷል ፡ » ሲሉ ፡ ጐይታደና ፡ እንደዋዛ ፡ ጠየቁ ።

« ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ይበቁኛል ። »

« ወንድ ፡ ሴት ? » አሉና ፡ ሁለተኛው ፡ እንግዳ ፡ ሁለተኛውን ፡ ጥያቄ ፡ ደቀኑ ።

« የበኸሬ ፡ ሴት ፡ ናት ። ቀጥሎ ፡ ሁለት ፡ ወንዶች ። የመጨረሻዋ ፡ ደግሞ ፡ ስትገቡ ፡ ከውጭ ፡ ያያችኋት ፡ መሆኗ ፡ ነው ። »

« እ ኸ ኸ ኸ ! አድርሰሃላ ! »
« አዎ ! »

« ታዲያ ፡ ምን ፡ አስበሃል ? መቸም ፡ ምግመኑና ፡ አድማጠረ ፡ አይለያይም ? » አሉ ፡ ጐይታና ፡ግርማ ፡ በማዳነቅ ።

ጋማሊ ፡ መልስ ፡ አልሰጣቸውም ።

« ጠይቀን ፡ እንጅ ? » ሲሉ ፡ ግርማ ፡ አፈጠጡበት ።
« ምን ፡ ብዬ ? » ጋማሊ ፡ ግራ ፡ የገባው ፡ መስሎ ፡ ጠየቀ ።

« ምን ፡ አመጣችሁ ፡ ብለህ ? »

« እሺ ፡ ምን ፡ አመጣችሁ ? »

« ምን ፡ አመጣችሁ ፡ ማለት ፡ ደግ » ጐይታና ፡ ግርማ ፡ ጢማቸውን ፡ እንደመጐተት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እንደማዘንበል ፡ አድርገው ፡ መለሱ ። « እኛ ፡ የመጣነው ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ለመተማሥርም ፡ ለማስተሳሰርም ፡ ነው ፡ » አሉ ።

« ለማን ፡ ነው ? » ጋማሊ ፡ ሁለቱን ፡ እንግዶች ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ተመለከታቸው ።

« ለአታቲው ፡ ቀንደኛ ፡ ለታወቀው ፡ አባሹረም ፡ ለአጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ልጅ ፡» ሲሉ ፡ ሁለተኛው ፡ ሽማግሌ ፡ መለሱ ።

« መሔዳችሁ ፡ ካልቀረ ፡ እኮ ፡ በሉ ፡ ጠጡት ፡ » ሲል ፡ ጋማሊ ፡ መልሱን ፡ እንዳልሰማ ፡ ያህል ፡ ዋንጫውን ፡ እያነሣ ፡ ጋበዛቸው ።

« ይህ ፡ ጠላ ፡ ያልተጠጣ ፡ ምን ፡ ይጠጣል ! » ግርማ ፡ ለማጣጣም ፡ ከንፈራቸውን ፡ መጠጡ ።



« ጠጥተን ፡ በጊዜ ፡ እንድንሄድ ፡ የመጣንበትን ፡ ንገረና ፡ »

« አሁን ፡ መልስም ፡ የለኝ ፡ »
« መቸ ፡ እንመጣ ? »
« እኮ ፡ ጠጡት ? »
« መሽቷል ፡ ሸኘን ፡ ጋማሊ ፡ »

ጋማሊ ፡ ጸጉሩን ፡ አካከከ ፡ « በወዲያኛው ፡ ወር ፡ ገደማ ፡ ብቅ ፡ በሉ ፡ መቸማ ፡ »

ሽማግሌዎቹ ፡ በወዲያኛው ፡ ወር ፡ ሲመጡ ፡ ምክት፡ ታርዶ ፡ አረቄ ፡ ጠጅ ፡ ጠላ ፡ ቡና ፡ ቀርቦ ፡ በሚገባ ፡ ከተጋበዙ ፡ በኋላ ፡ የወር ፡ ቀጠሮ ፡ ተሰጡ ። በወሩ ፡ መጡ ። ተጋብዘው ፡ ተሸኙ ።

« ተው ! ዳሞ ፡ ጋማሊ ፡ ዓመት ፡ እስከዓመት ፡ ስታቅማማ ፡ ልጅህ ፡ ቆማ ፡ ትቀራለች ! አሁን ፡ ማይሙት ፡ አጋዝ ፡ በርጋ ፡ አቻህ ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ ነው ? » አሉ ፡ አንደኛው ፡ ሽማግሌ ፡ እንደዘበት ።

« እሄሄ ! የኔ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ ቆማ ፡ የምትቀረው ! ከሞገመን ፡ ከቋምንት ፡ ከገብርያጥር ፡ ከሸራር ፡ ከነጌራ ፡ ከብራሲዮ ፡ ከድብረገርራ ፡ ከእንቴዘራ ፡ ከአድማጠረ ፡ ከይሳ ፡ ከደንገዠ ፡ ከምድረ ፡ ሰባት ፡ ቤት ፡ ጉራጌ ፡ ለአድማጠሩ ፡ ወኸርታረግ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ ከታጣማ ፡ ቁማ ትቅር ! » ሲል ፡ ጋማሊ ፡ መለሰላቸው ።

« ኧረ ፡ ስቀልድህ ፡ ነው ፡ ! » አሉ ፡ ሽማግሌው ።
« እኔ ፡ ደግሞ ፡ በልጄ ፡ አልቀልድማ ! » ግን ፡ እነጋገሩ ፡ የመከፋት ፡ አልነበረም ።

በሶስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ የፊተኞቹ ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ አራት ፡ ቀንደኛ ፡ አዛውንት ፡ ጨምረው ፡ መጡ ።

« ዛሬስ ፡ በዋዛ ፡ እንላቀቅም ፡ አሉ ፡ » ከመጀመርያው ፡ አንስቶ ፡ ሲመላለሱ ፡ የከረሙት ፡ አንደኛው ፡ ሽማግሌ ።

ዳሞ ፡ ጋማሊ ፡ እንግዶቹን ፡ በእጁ ፡ እያመላከተ ፡ አስቀመጠና ፡ ከድኳ ፡ ላይ ፡ ቆርጠጥ ፡ አለ ። በመምሕሩ ፡ ፊት ፡ ጥናቱ ፡ የጠፋበት ፡ ተማሪ ፡ ይመስል ፡ ጸጉሩን ፡ አከከ ።

ስለ ፡ አዝመራውም ፡ ስለከብቱም ፡ ስለ ፡ ንግዱም ፡ ስለሸንጎውም ፡ አጤ ፡ ምኒልክ ፡ ፊንፊኔ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ስለቆረቆሩት ፡ ከተማም ፡ ስለጭሰኝነቱና ፡ ስለባላባትነቱ ፡ ጥቂት ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ቆይተው ፡ ከቡናው ፡ በፊት ፡ ቁርሱ ፡ የቆሎ ፡ ቂጣና ፡ ቆሎው ፡ ሲቀርብ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ባንድነት ፡ ተነሱ ።

« ዛሬስ ፡ አትልፋ ! ዳሞ ፡ ጋማሊ ፡ ካልጨረስክልን ፡ እህል ፡ ውሃ ፡ ከቤትህ ፡ ላንቀምስ ፡ በመስቀል ፡ በድንግላይ ፡ መነኩሴ ፡ ተገዝተን ፡ ነው ፡ የመጣነው ፡ » አሉ ፡ ተቀዳሚው ፡ ሽማግሌ ።

ጋማሊ ፡ ጋቢውን ፡ እንደማጣፋት ፡ አለና ፡ ክንዱን ፡ አወራጨ ፡ « ሳሊለን ፡ ቅድስት ! ሳሊለን ፡ ቅድስት ! » ለማማተብ ፡ ያህል ፡ መዳፉን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ አማታው ። « እኔ ፡ ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ያገር ፡ አዛውንት ፡ ያገር ፡ ቀንደኞች ፡ ግንባር ፡ የማላከብር ፡ ደፋር ፡ ነኝ ? » በማዘን ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ።



« በላ ! ሽበታችን ፡ ካስፈራህ ፡ ዕድሜያችን ፡ ከከበደህ ፡ የላመ ፡ ጉልበታችን ፡ የደከመ ፡ ክንዳችን ፡ ካሳዘነህ ፡ ትልቅነታችንን ፡ ካከበርክ ፡ በላ ! » አሉ ፡ ጸጉራቸው ፡ ንድፍ ፡ የመሰለው ፡ አዲስ ፡ መጥ ፡ ሽማግሌ ። ግንዳቸው ከእነሞር ፡ ፌረር ፡ ቢሆንም ፡ በመላው ፡ ሰባት ፡ ቤት ፡ ጉራጌ ፡ በጀግንነታቸውም ፡ ባይሆን ፡ በሸንጎ ፡ ነገራቸው ፡ ከዚያም ፡ በሽበታቸውና ፡ በጢማቸው ፡ በምድረ ፡ ሰባት ፡ ቤት ፡ ጉራጌ ፡ የታወቁ ፡ አዛውንት ፡ ናቸው ።

ጋማሊ ፡ ለቅጽበት ፡ ዓይኑን ፡ ከደን ፡ አድርጎ ፡ አሰበ ። የበክር ፡ ልጁ ፡ ታየችው ። ምድረ ፡ የሰባት ፡ ቤት ፡ ጉራጌን ፡ በዓይነ ፡ ሕሊናው ፡ አዳረሰው ። አራት ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ የአጋዝ ፡ ቦርጋን ፡ ወደላይ ፡ የዘር ፡ ግንዱን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ሙያውንና ፡ ጉብዝናውን ፡ ወደታች ፡ ከብቱን ፡ ንብረቱን ፡ ርስቱን ፡ አስመርምሯል ። የተሻለ ፡ ጠያቂ ፡ ቢኖር ፡ ተጣድፎ ፡ እንዲመጣም ፡ ያንን ፡ የመንደር ፡ አዝማሪ ፡ ጠቁሞ ፡ በሸንጎውም ፡ በድግሱም ፡ «የዳሞ ፡ ጋማሊ ፡ ሴት ፡ ልጅኮ ፡ ልትታጭ ፡ ነው ። አዬ ፡ ሚስት ፡ ተገኘች ! ሚስት ፡ ማለት ፡ አመለጠች ! » እያሰኘ ፡ አስወርቷል ። ታዲያ ፡ የመጣ ፡ የለም ። ሊሰጣት ፡ ወስኖ ፡ ነበር ። «ጌቶቼ ፡ መኳንንቶቼ ፡ አጣደፋችሁኝኮ ፡ » አለ ፡ በአክብሮት ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ እንዳደረገ ።

« አጣደፋችሁኝ ? ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ? አህያ ፡ ቀንድ ፡ እስከታበቅል ፡ ጠብቁ ፡ እንደሆን ፡ እንጃ ! » ሲሉ እንደመገሰጽ ፡ ኮስተር ፡ አድርገው ፡ ተናገሩ ።

« ኧረ ፡ አልወጣኝም ! » ጋማሊ ፡ አሁንም ፡ ጸጉሩን ፡ አከከ ።

« በል ፣ እኛም ፣ ግዝታችን ፣ ተፈትቶ ፣ እህል ፣ ውሃውን ፣ እንቅመስበት ፡ »

ጋማሊ ፡ አሁንም ፡ እንደመተከዝ ፡ አለ ። « ካገሬ ፡ ሽማግሌ ፡ ቃል ፡ ብወጣ ፡ ፈጣሪ ፡ ከገነት ፡ ቤቱ ፡ ያውጣኝና ፡ በአገሬ ፡ በትውልዴ ፡ አከብራችሁ ፡ ፈልጋችሁኝ ፡ እንደመጣችሁ ፡ አከብሬ ፡ ፈልጌ ፡ እቀበላችኋለሁ ። ከፈቃዳችሁ ፡ አያውጣኝ ። ጥያቄያችሁን ፡ እምቢ ፡ ብዬ ፡ ክፉ ፡ ፊታችሁን ፡ አያሳየኝ ፡ » ሲል ፡ መለሰ ።

« የአውራ ፡ ልጅ ፡ ነህና ፡ አውራ ፡ ያድርግህ ! »
« አባቶችህ ፡ ደገኛ ፡ ነበሩና ፡ ልጅ ፡ ልጆች ፡ ይጡሩህ»
« የወላድ ፡ መካን ፡ አያድርግህ ! »
« የሽማግሌ ፡ ውርደት ፡ አይጣልብህ ! »

ሁሉም ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ መረቁት ። ተራ ፡ በተራም ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ ጋር ፡ ጉንጭ ፡ ለጉንጭ ፡ ተሳሳመ ። ከዚያ በኋላ ፡ ምግቡንና ፡ መጠጡን ፡ ተጋበዙ ።

ጋማሊ ፡ የጠረጠረው ፡ አልቀረለትም ። በድንገት ፡ እንደ ፡ አቡዬ ፡ ጠበል ፡ የልጁ ፡ ፈላጊ ፡ በዛ ። ከጉመር ፡ ከእዣ ፡ ከፌረር ፡ ከቆንጫጫ ፡ ጠያቂዎች ፡ እየመጡ ፡ አስቸገሩት ። የነጠረ ፡ ባላባት ፡ የታወቀ ፡ አዛውንት ፡ ልጅ ፡ የተንቀባረረ ፡ ጌታ ፡ የልጁን ፡ እጅ ፡ ጠየቀ ። ጋማሊ ፡ እንደ ፡ መቆጨትም ፡ እንደመናደድም ፡ አለ ። እስከዛሬ ፡ የት ፡ ነበሩ ? ታዲያ ፡ መቸም ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ አያጥፈውም ። የለም ። ከአገር ፡ ሽማግሌ ፡ አፍ ፡ ከመግባት ፡ ከቶ ፡ ያድነው ። ደግሞም ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ መልካም ፡ ጋብቻ ፡ ነው ።

የቸጉ ፡ ቀን ፡ ሳምንት ፡ ሲቀረው ፡ ጋማሊ ፡ አንድ ብር ፡ ወርዶ ፡ ሐረር ፡ እየተመላለሱ ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ ሸቀ



ጥ ፡ በማምጣት ፡ ከታወቁት ፡ ሲራራ ፡ ነጋዴ ፡ ለራሱ ፡ እጀ ፡ ጠባብና ፡ ሱሪ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ መሐሙዲ ፡ ለሚስቱ ፡ ቀሚስ ፡ አስር ፡ ክንድ ፡ ረዳ ፡ መንገሻ ፡ ገዝቶ ፡ ተመለሰ ። የመንደሩ ፡ ጠላፊ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ሰፍቶ ፡ በአምስት ፡ ቀን ፡ የሁለቱንም ፡ ልብስ ፡ አደረሰው ።

የቸጉ ፡ ዕለት ፡ ጋማሊ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተነስቶ ፡ ግቢውን ፡ እየተዘዋወረ ፡ ጐበኘ ። ንጹሕ ፡ ነው ። እያሳፍርም ። ከጓዳም ፡ ጠላው ፡ ዳግም ፡ አረቄው ፡ ክትፎው ፡ ቆጮው ፡ ድግሱ ፡ ደህና ፡ ተሟልቷል ። እንደትናንት ፡ ማምሻውን ፡ አንድ ፡ ያማረ ፡ ወይፈኑንና ፡ አንድ ፡ ሙክት አሳርዶ ፡ ነበር ። ግን ፡ ልጅ ፡ ሲድር ፡ የመጀመርያ ፡ ጊዜው ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳብ ፡ ይዞት ፡ ነበር ። ከዳገቱ ፡ ላይ ፡ ሆኘ ፡ አዝመራውን ፡ ቁልቁል ፡ ተመለከተ ። መጨረሻውን ፡ ያሳምረው ፡ እንጅ ፡ ቡቃያው ፡ ግሩም ፡ ይዝዋል ። የእንሰቱ ፡ ተክል ፡ ውሃ ፡ ጠብ ፡ የማያስደርግ ፡ ችምችም ፡ አረንጓዴ ፡ ጫካ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ሁሉንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢባርክለት ፡ ከርሞ ፡ መስቀል ፡ ቅልጥ ፡ አድርጎ ፡ ይሠርጋል ። ወይፈን ፡ ቢታረድ ፡ ወይፈን ፡ ይተካል ።

በተሲአት ፡ ላይ ፡ እንግዶቹ ፡ አንድ ፡ አስር ፡ ያህል ፡ ሆነው ፡ ሲመጡ ፡ ጋማሊ ፡ በአዲሱ ፡ መሐሙዲ ፡ እጀ ፡ ጠባብና ፡ ሱሪው ፡ ላይ ፡ ጥለቱ ፡ ስንዝር ፡ የሆነ ፡ ጃኖ ፡ ደርቦ ፡ ተቀበላቸው ።

አንቱ ፡ የአከሰቱ ፡ ባልና ፡ የደብሩ ፡ አዛውንት ፡ በር ፡ አትራጋ ፡ አብረውት ፡ ነበሩ ። ከእንግዶቹ ፡ መካከል ፡ ጋማሊ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ የማያውቃቸው ፡ አንድ ፡ ካህን ፡ ነበሩ ። የልጁ ፡ አባት ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ በአለባበሱ ፡ ከሌሎች ፡ ደመቅ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። ወርዶፋ ፡ ተፈሪ ፡

ሱሪ ፡ ወልደየስ ፡ እጀጠባብ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አረንጓዴ ፡ ጥለት ፡ የቤት ፡ ፈትል ፡ አጣፍቶበታል ።

እንግዶቹ ፡ ተቀምጠው ፡ ጠላ ፡ ቀርቦ ፡ አሳላፊ ፡ እጁን ፡ አጣፍቶ ፡ እንደቆመ ፡ ጋማሊ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ በመመለስ ፡ አንገቱን ፡ አስግጎ ፡ « ከብት ፡ ደህና ? ሰው ፡ ደህና ? አገርስ ፡ ደህና ? » ሲል ፡ ጨዋታውን ፡ ከፈተ ።

« ከብቱም ፡ ሰውም ፡ አገሩም ፡ ደህና ። እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ። ምናለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ይኸው ፡ መቸም ፡ ሊያቀራርበን ፡ ነው ። »

« በሉ ፡ ቅመሱት ፡ እንጂ ፡ » ጋማሊ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ እንግዶቹን ፡ በዓይኑ ፡ እየቃኘ ፡ ጋበዘና ፡ ወደ ፡ ቦርጋ ፡ እንደገና ፡ ዞሮ ፡ « ልጅህ ፡ ደህና ፡ ነው ? » ሲል ፡ ጠየቀው ።

ቦርጋ ፡ በአወንታ ፡ መለሰለት ።

« ስሙ ፡ ማን ፡ ይባላል ? »

« ቴሊ ፡ »

« ኧረግ ! የኔ ፡ ቅድመ ፡ አያትም ፡ ቴሊ ፡ ነበር ፡ ስማቸው ። » ጋማሊ ፡ ፈገግ ፡ አለ ። « ሙያውስ ? » ጋማሊ ፡ በሚገባ ፡ መጠየቅ ፡ የፈለገው ፡ ይህንን ፡ ነበር ። ማን ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ እንግዳን ፡ በጥያቄ ፡ ውጥር ፡ አድኅር ፡ መያዝ ፡ ነውር ፡ ነውና ፡ ጥያቄውን ፡ እንደዋዛ ፡ ሰነዘረው ።

« አዬ ፡ ዳሞ ፡ ጋማሊ ! እኔ ፡ ብነግርዎት ፡ አባቱ ፡ ነኝና ፡ ሌላ ፡ ያስመሰልብኛል ። ስለሙያውስ ፡ ሌሎች ፡



ቢመሰክሩለት ፡ ይሻል ፡ ነበር ። ፈረስ ፡ ሲጋልብ ፡ ጦር ፡ ሲወረውር ፡ ሲያድን ፡ ሲያርስ ፡ ኧረ ፡ እንዲያው ፡ ይተውኝ ! እሱ ፡ ባወቀ ፡ ከሰው ፡ ዓይን ፡ ይጠብቅልኝ ፡ እንጂ ! »

« ፊቱን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እንዳያዞር ፡ ብቻ ፡ ይጠብቁት ፡ » ጋማሊ ፡ በጉዳዩ ፡ እንዳሰበበት ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀ ።

« እንግዲህማ ፡ አብረን ፡ እንጠብቃለን ፡ እንጂ ፡ » ሲል ፡ ቦርጋ ፡ መለሰ ። በመግባባት ፡ ተሳሳቁ ። በመካከሉ ፡ ሌሎች ፡ ጣልቃ ፡ ገቡና ፡ ጨዋታው ፡ ተዘበራረቀ ። አንዱ ፡ ስለአዝመራ ፡ ያወራል ። ካህኑ ፡ ስለአባ ፡ ገሪማ ፡ ገድል ፡ ይተርካሉ ። ሶስተኛው ፡ የጋብቻውን ፡ አቻነት ፡ ያደንቃሉ ። ከመጀመርያው ፡ አንስቶ ፡ እየተመላለሱ ፡ ነገሩን ፡ ከጫፍ ፡ ያደረሱት ፡ ሽማግሌ ፡ ግራ ፡ እጃቸውን ፡ ብድግ ፡ አደረጉና ፡ «ጨዋታው ፡ በኋላ ፡ ይሆናል ። አሁን ፡ ዋናውን ፡ ጉዳያችንን ፡ እንፈጽም ፡ » አሉ ። ሁሉም ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

« በል ፡ ጋማሊ ፡ » ሲሉ ፡ ጠየቁት ። ጋማሊ ፡ ተነስቶ ፡ ቆመ ። ሌሎችም ፡ ተነሱ ።

« ዝምድናህን ፡ ፈልገን ፡ መጥተናል ፡ »

« ዘመድ ፡ አያሳጣ ፡ እንጂ ፡ ዝምድናችሁ ፡ ዝምድናዬ ፡ ነው ፡ » ጋማሊ ፡ ጥቂት ፡ አሰበ ። « የበኽር ፡ ልጄ ፡ ኬርወኜን ፡ ለአጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ልጅ ፡ ለቲሊ ፡ ቦርጋ ፡ ወድጄ ፡ ፈቅጄ ፡ በቸግ ፡ ሰጥቻለሁ ፡ » ሲል ፡ መለሰ ።

ቦርጋ ፡ ወዲያው ፡ ቀበል ፡ አደረገና ፡ « እኔም ፡ ቦርጋ ፡ የዳሞ ፡ ጋማሊን ፡ ልጅ ፡ አጀት ፡ ኬርወኜን ፡ ለልጄ ፡ ለቴሊ ፡ ቦርጋ ፡ ሚስት ፡ እንድትሆነው ፡ ወድጄ ፡ ፈቅጄ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ተቀብያለሁ ፡ » አለ ።

« የወንድ ፡ የቸግ ፡ አባት ፡ ማነው ፡ » ሲሉ ፡ የጋማሊ ፡ አኅት ፡ ጠየቁ ።

« በርደፈረ ፡ ሸርጋ ፡ ናቸው ፡ »

« በርደፈረ ፡ ሸርጋ ፡ የወንድ ፡ የቸግ፡አባት ፡ ነዎት ?» የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ቀረበላቸው ።

« አዎን ፡ ነኝ ፡ » አሉ ፡ ሳያመነቱ ፡

« ለልጂ ፡ ለኬርወኜ ፡ ለጥርሷ ፡ ለዓይኖችዋ ፡ ለእግርዋ ፡ ለእጅዋ ፡ ለመላ ፡ አከላቷ ፡ ኃላፊ ፡ ነዎ ፡ በርደፈረ ፡ ሸርጋ ? » ሲል ፡ ጋማሊ ፡ ጠየቃቸው ።

« ክፉ ፡ እንዳያገኛት ፡ ደግ ፡ እንዲመኛት ፡ አዎ ፡ ኃላፊ ፡ ነኝ ፡ » ብለው ፡ መለሱ ።

« የሴት ፡ የቸግ ፡ አባትስ ፡ ማነው ? »

« በርከፈተ ፡ አትራጋ ፡ ናቸው ።

« ልጃችን ፡ ክፉ ፡ እንዳያገኘው ፡ የሴት ፡ የቸግ ፡ አባት ፡ ነዎ ? »

« ነኝ ፡ »

የወንድ ፡ የቸግ ፡ አባትና ፡ አጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ከዳሞ ፡ ጋማሊና ፡ ከሴት ፡ ቸግ ፡ አባት ፡ ከበርከፈተ ፡ አትራጋ ፡ ጋር ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ትከሻና ፡ ግምባር ፡ ተሳሳሙ ።

ግብዣውና ፡ ጨዋታው ፡ ጸሐይ ፡ ዘቅዘቅ ፡ እስከትል፡ ቆይቶ ፡ ሁሉም ፡ ሞቅና ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሲሰነባበቱ ፡ ጋማሊና ፡ ቦርጋ ፡ እንደገና ፡ ተሳሳሙ ።



## ሦርጉ ፡ ለመስቀል ፡ ተቀጠረ ።

ሦርጉ ፡ በመስከረም ፡ ሊሆን ፡ ኬርወኜ ፡ ፍልሰታ ፡ ከተፈሰገች ፡ ማግሥት ፡ አንስቶ ፡ በየዘመዶቿ ፡ ቤት ፡ እየተጠራች ፡ ስትጋበዝ ፡ ከረመች ። ከልጃገረድ ፡ ጓደኞችዋ ፡ ጋር ፡ ትሆንና ፡ ከአክስቷ ፡ ቤት ፡ ቀጥሎ ፡ ከአኅቷ ፡ ከአያቷ ፡ ( የእናቷ ፡ ወላጅ ) ከክርስትና ፡ እናቷ ፡ ከቸግ ፡ አባቷ ፡ ከአጐቶችዋና ፡ ከአክስቶችዋ ፡ ቤተሰቦች ፡ ቤት ፡ አራትና ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ስትቀለብ ፡ ትሰነብታለች። በየተጠራችበት ፡ መጠነኛ ፡ ድግስ ፡ አለ ። ቢያንስ ፡ ሙክት ፡ ይታረዳል ። በመጀመርያው ፡ ቀን ፡ በርከትከት ፡ ያለ ፡ ተጋባዥ ፡ ይጠራል ። ከዚያ ፡በ ኋላ ፡ ግን ፡ እርሷና ፡ ጓደኞችዋ ፡ ለብቻ ፡ ይያዛሉ ። ከትፎው ፡ ቆጮው ፡ ጮፍጮው ፡ ሰማሞዣቱ ፡ የጐመን ፡ ክትፎው ፡ ፍንታፍንቾው ፡ እንደ ፡ አራስ ፡ ይቀርብላቸዋል ። መስከረም ፡ ሲጠባ ፡ ኬርወኜ ፡ በቆየው ፡ ደም ፡ ግባቷና ፡ ውብቷ ፡ ላይ ፡ እንደትኩስ ፡ ብርቱካን ፡ አወለወለች ። ለመቀንጠፍ ፡ የደረሰች ፡ የምታስጐመጅ ፡ ፍሬ ፡ ሆነች ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ጓደኛዋ ፡ « እንግዲህኮ ፡ ጥለሽን ፡ ልትሄጅ ፡ ነው ፡ ? » አለቻት ።

« የት ? » አለች ፡ ኬርወኜ ፡ በመደናገር ፡ እንደመበርገግ ፡ እየቃጣት ። ግን ፡ ስታስመስል ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ መጠርጠሯ ፡ አልቀረም ፡ ነበር ።

« ባል ፡ ልታገቢ ፡ ነው ! » ስትል ፡ ጓደኛዋ ፡ መለሰች።

« ሂጅ ! አፍር ፡ ብይ ! ብል ፡ ይብላሽ ፡ እቴ ፡ » አለች በመሽኮርመምና ፡ በማፈር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ በንግግር ፡ አላነሱትም ። በሐሳብ ፡ ግን ፡ ይተዋወቁ ፡ ነበር ።

ቴሊም ፡ የነገረው ፡ አልነበረም ። ግን ፡ ነጋሪ ፡ አላስ
ፈለገውም ። አባቱ ፡ በግቢው ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡
ማሠራት ፡ ሲጀምር ፡ አወቀ ። በየግቢው ፡ ድንገት ፡ አዲስ፡
ቤት ፡ ሲሠራ ፡ በዚያ ፡ ግቢ ፡ ወዲያው ፡ ሠርግ ፡ ተደግሶ ፡
የሚያውቃቸው ፡ ጐልማሶች ፡ ሚስት ፡ ሲያገቡ ፡ ብዙ ፡
ጊዜ ፡ ተመልክቷል ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ቴሊ ፡ የልብ ፡ ጓደኛውን ፡ አማከረ
ውና ፡ ሁለቱ ፡ ወደ ፡ ምሑር ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ኬርወኄ ፡
ፍልሰታ ፡ አስቀድሳ ፡ ወደቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ ከጋሚሊ ፡
ግቢ ፡ አጠገብ ፡ ጠብቀው ፡ አዩዋት ።

« ውብ ፡ ናት ፡ » አለው ፡ ጓደኛው ።

« ሚስቴ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ » ሲል ፡
ቴሊ ፡ እንደማፈር ፡ ብሎ ፡ ጥፍሩን ፡ ቆረጠመ ።

የመስቀል ፡ ለታ ፡ ሙሽሪት ፡ ኬርወኄ ፡ ለብሳ ፡ ተሸ
ልማ ፡ አጊጣ ፡ በእልፍኝ ፡ እናቷንና ፡ ወንድሞችዋን ፡
ስማ ፡ ወጣች ። በወላድነቷ ፡ በመንደሩ ፡ የታወቀች ፡ ባዝ
ራ ፡ ፈረስ ፡ ቀርቦላት ፡ ተቀመጠችባትና ፡ የግቢውን ፡
በር ፡ እንዳለፈች ፡ መልሰው ፡ አወረዱዋት ። ኮርቻው ፡
በጌጥ ፡ ወደተንቆጠቆጠ ፡ ሰጋር ፡ በቅሎ ፡ አዛወሩዋት ።
ይዛው ፡ የምትሔደው ፡ የቤትና ፡ የጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ከቄጠማ ፡
በጌጥ ፡ የተሠራው ፡ የኬሻ ፡ መኝታ ፡ ከእንጨት ፡ ተጠ
ርቦ ፡ በዛጐል ፡ የተሸለመው ፡ ቅራስ ፡ ከቀርከሃ ፡ በጌጥ ፡
ቀለማት ፡ የተሠራው ፡ ሞሶብ ፡ ከዘንባባ ፡ የተሰፋው ፡
ጉንዶ ፡ ( የጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ማስቀመጫ ፡ ) በሁለት ፡ ትልልቅ ፡
ከረጢት ፡ ተቀርቅቦ ፡ በሁለተኛ ፡ በቅሎ ፡ ተጫነ ። ሙሽ
ሪት ፡ ኬርወኄ ፡ በሶስት ፡ የመንደር ፡ ባልቴቶችና ፡ በአ
ስር ፡ ልጃ ፡ ገረዶች ፡ ታጅባ ፡ ወደ ፡ ባሏ ፡ ቤት ፡ ጉዞዋን ፡
ቀጠለች ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ኬርወኄ ፡ በእልፍኝ ፡
ውስጥ ፡ ተጠብቃ ፡ የእጅዋ ፡ ጥፍር ፡ እስከ ፡ ሥሩ ፡ ድረስ ፡
እየተመደመደ ፡ በቅቤ ፡ ስትታሽ ፡ ሰንብታለች ። እድም
ተኛው ፡ ከደመራው ፡ አንስቶ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲጋበዝ ፡
ጭፈራውም ፡ ሲቀልጥ ፡ አድሮ ፡ ውሏል ። ኬርወኄ ፡ ተወ
ልዳ ፡ ያደገችበትን ፡ ግቢ ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
ዞር ፡ ብላ ፡ በኀዘን ፡ ዓይን ፡ ስትመለከት ፡ በዳሱ ፡ ውስጥ ፡
ሁካታውና ፡ ጭፋሮው ፡ ያተም ፡ ነበር ።

« አይዞሽ! » አሉ ፡ አንደኛዋ ፡ ባልቴት ፡ እያንዳንድ
ዋን ፡ ፊደል ፡ ለየብቻ ፡ ከምላሳቸው ፡ አውጥተው ፡ እየ
ጣሉ ፡ « ተመልሰሽ ፡ ትመጫለሽ ። አዲሱ ፡ ቤትሽንም ፡
ትለምጅዋለሽ ። » ኬርወኄ ፡ መልስ ፡ አልሰጠችም ።

ሶስቱ ፡ ባልቴቶች ፡ በዘፈን ፡ በአሽሙርና ፡ በነገር ፡
ባገር ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ አዋቂነታቸው ፡ የተመረጡ ፡
ናቸው ። ያገር ፡ ቤቱን ፡ መንደር ፡ መግቢያና ፡ መውጫ ፡
አሳምረው ፡ ያውቁታል ።

የመንደሩን ፡ ቁልቁለት ፡ ጨርሰው ፡ ሰፊውን ፡ ሜዳ፡
እንደተያያዙት ፡ የአራቱ ፡ ሰዓት ፡ ጐዳና ፡ እንዲገፋላቸው፡
ዘፈን ፡ ጀመሩ ።

ከበሮው ፡ ድልቅ ፡ ድልቅ ፡ ሲል ፡ እየተቀባበሉ ፡
ያቀነቅናሉ ።

ደስ ፡ ይበልህ ፡ ሙሽራ ፡
አግኝተሃል ፡ የሰው ፡ አውራ ፡
ላላ ፡ ሸቦ ፡ ላላ ፡ ሸቦ ፡
የምሑር ፡ ዘር ፡ አድማጠረ ፡

የከበረ ፣ የነጠረ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣ ላላ ፣ ሸቦ
ከቸሃም ፣ ተፈለገ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
ከጉመርም ፣ ተጠየቀ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
ከእግም ፣ ሰው ፣ ተላከ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
ከጌቶም ፣ ሁሉ ፣ ታዬ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
ከእነሞር ፣ ተመረጠ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
ከአክሊለ ፣ ተጐበኘ ፣
ላላ ፣ ሸቦ ፣
እንዳንችም ፣ አልተገኘ ።

ሚዳውን ፣ ጨርሰው ፣ ከአፋፉ ፣ ላይ ፣ ሆነው ፣ በአሻገር ፣ የሞገመነ ፣ ሠፈር ፣ የሚታይበትን ፣ ጉብታ ፣ ሲያዙ ፣ የመስከረም ፣ ድንገተኛ ፣ ዝናም ፣ ያወርደው ፣ ጀመር ። ሙሽሪት ፣ ኬርወጌ ፣ የሰሌን ፣ ባለጌጥ ፣ ጥላዋን ፣ ዝቅ ፣ አድርጋ ፣ ይዛ ፣ በቅሎዋን ፣ እያሰገረች ፣ አጃቢዎች ፣ ከበሮውንና ፣ ሌላውንም ፣ ዕቃ ፣ አንግተው ፣ ኩታቸውን ፣ ጠቅልለው ፣ ቀሚሳቸውን ፣ ከፍ ፣ አድርገው ፣ ይዘው ፣ እየተሯሯጡ ፣ ዳገቱን ፣ ለመዝለቅ ፣ ሞከሩ ። ግን ፣ ዝናሙ ፣ ስለበረታባቸው ፣ ከአጋማሽ ፣ ላይ ፣ ከአንድ ፣ የወይራ ፣ ዛፍ ፣ ስር ፣ ተጠለሉ ። ጭፋሮው ፣ ቀርቶ ፣ ልብሳቸውን ፣ አራገቡና ፣ እእችክ ፣ እችክ ፣ እያሉ ፣ እስኪያባራ ፣ ድረስ፣ ቆሙ ። ጥቂት ፣ እንደቆዩና ፣ ዶፉ ፣ ጋብ ፣ ሰማዩ ፣ ገለጥ ፣



ነጐድጓዱ ፣ በረድ ፣ ማለት ፣ ሲጀምር ፣ ከየት ፣ በኩል ፣ እንደመጣ ፣ ያላዩት ፣ ጐልማሳ ፣ ድንገት ፣ ከአጠገባቸው ፣ ተገኘ ።

እንደመደናገጥ ፣ አሉና ፣ ሁሉም ፣ አፍጥጠው ፣ ተመለከቱት ። እርሱ ፣ ግን ፣ በማሾፍ ፣ አኳኋን ፣ ዓይኑን ፣ ጭለቅ ፣ አድርጎ ፣ « ሙሽሪት ? » አለ ።

« ኧረ ፣ ሞት ፣ ይሞሽርህ ፣ እቴ ! » አሉት ፣ አንደኛዋ፣ ባልቴት ።

« አጠፋሁ ፣ እንዴ ? ሙሽርነት ፣ ተመቸወዲህ ፣ የሚያሳፍር ፣ ሆነ ፣ »

« ኡኡ ፣ እትዬ ! ለዛው ፣ ጠብ ፣ የሚል ፣ ኧረ ፣ ከየት ፣ መጣልኝ ! አንተ ፣ ብሎ ፣ የሙሽራ ፣ ወግ ፣ አዋቂ ! » ባልቴቷ ፣ በበኩላቸው ፣ ከንፈራቸውን ፣ አጣመው ፣ አዩት ።

« ባልዳርም ፣ ሲዳሩ ፣ አይቻለሁ ። ሙሽራው ፣ ከየት ፣ ነው ? » ሲል ፣ በፌዝ ፣ ፈገግታ ፣ ጠየቀ ።

« ምን ፣ ዶለህ ! » አሉ ፣ ረገጥ ፣ አድርገው ፣

« ምነዋ ! ለመጥራት ፣ የሚያሳፍር ፣ ነው ፣ እንዴ ? » ባልቴቷን ፣ አፎልቆ ፣ ተመለከተ ።

« ኧረ ፣ አንድ ፣ በሉልኝ ፣ ይህንን ፣ ሰው ! » ጣታቸውን ፣ አሾሉበት ።

« እንዲያውም ፣ እንደመሰለኝ ፣ ወደሞገመነ ፣ ሠፈር ፣ ነው ፣ » አለ ፣ አሁንም ፣ የፌዝ ፣ ፈገግታውን ፣ ሳይለውጥ ።

መልስ ፣ አልሰጡትም ።

« ታዲያ ፣ ወንዙ ፣ ያሻግራል ፣ ብላችሁ ፣ ነው ? » ሲል ፣ ጠየቀ ።

« ውይ ! ሞልቶ ፡ ይሆን ? »ባልቴቲቱ ፡ ንትርካቸውን ፡
ረስተው ፡ በማሰብ ፡ አገጫቸውን ፡ ያዙ ።

« የት ፡ ይቀራል ። እኔ ፡ የተሻገርኩት ፡ ለጥቂት ፡
ፈረሰኛው ፡ ሲደርስ ፡ ነው ፡ »

ባልቴቶቹ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ታያዩ ። ልጃገረዶ
ቹም ፡ በሐሳብ ፡ ፈዘዙ ። አሁን ፡ ዝናቡ ፡ አባርቶ ፡ ነበር ።

እንደገና ፡ መንገዳቸውን ፡ እንደቀጠሉ ፡ ሰውዬው ፡
እንደዋዛ ፡ አብሮ ፡ እየተጓዘ ፡ « መቼስ ፡ ለክፉም ፡ ለደ
ጉም ፡ እስከወንዙ ፡ ማዶ ፡ ልሸኛችሁ ፡ እንጅ ፡ » አለ ።
አልተቃወሙትም ።

ጥቂት ፡ እንደሄዱ ፡ አሁንም ፡ ከየት ፡ በኩል ፡ እንደ
መጣ ፡ ያላዩት ፡ ሁለተኛ ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቦ ፡ ከጉ
ዞው ፡ ተቀላቀለ ። ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ የሚተዋወቁ ፡ አልመሰ
ሉም ። ከሙሽራዋ ፡ በቅሎ ፡ አጠገብ ፡ ያዘግሙ ፡ የነበሩት ፡
ባልቴት ፡ ጭፍሮውን ፡ ለመቀስቀስ ፡ እጃቸውን ፡ ዘርግ
ተው ፡ ዞር ፡ ሲሉ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ሆነው ፡
በዓይኖቻቸው ፡ ሲጠቃቀሱና ፡ በከንፈሮቻቸው ፡ ሲነጋገሩ ፡
ያዙዋቸው ። ግን ፡ ያላዩ ፡ መሰሉና ፡ ጥቂት ፡ እንደሄዱ ፡
ቀስ ፡ ብለው ፡ ለአንደኛዋ ፡ ባልቴት ፡ ሹክ ፡ አሉ ። ሁለተኛ
ይቱ ፡ እንደዚሁ ፡ በቀስታ ፡ ለሶስተኛዋ ፡ አስተላለፉ ።
ሶስተኛዋ ፡ የሙሽራይቱን ፡ በቅሎ ፡ ተደግፈው ፡ ሙሽራ
ይቱን ፡ የሚያጫውቱ ፡ መስለው ፡ ቀረቡ ። ጭፍሮው ፡
ተጀመረ ። ወዲያው ፡ አንዴ ፡ « መጭ ! » ብለው ፡ በቅ
ሎዋን ፡ ሲያስነሱ ፡ ሙሽሪት ፡ በዚያው ፡ በሁለት ፡ እግ
ሯ ፡ እየኰለኰለች ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ የሆነውን ፡ ገና ፡ ሳያ
ውቁ ፡ ዳገቱን ፡ ዘልቃ ፡ በቁልቁለቱ ፡ ጠፋች ። እንደጠረ



ጠሩትም ፡ ሶስተኛ ፡ ሰው ፡ መጣ ። የሆነውን ፡ ሲያውቁ ፡
ሶስቱም ፡ በይፋ ፡ ተነጋገሩና ፡ ጠብ ፡ መጫር ፡ አማራቸ
ው ። ባልቴቶቹ ፡ « በሉዋ ፡ ደብድቡን ! » ብለው ፡ ሲያ
ፈጡባቸው ፡ ጊዜ ፡ መልሰው ፡ ተውት ።

ዳገቱን ፡ ወጥተው ፡ ቁልቁል ፡ ሲመለከቱ ፡ አሁንም ፡
ሁለት ፡ ወንዶች ፡ አዩ ። ሙሽሪት ፡ ግን ፡ የውሃ ፡ ሽታ ፡
ሆናለች ። የመንገዱን ፡ አግጣጫ ፡ ስንኳ ፡ ነግረዋት ፡
ነበር ።

« እነማን ፡ ይሆኑ ፡ ከቶ ? » ሲሉ ፡ አንደኛዋ ፡ ባል
ቴት ፡ ጠየቁ ።

« እኔ ፡ ምናባቴን ፡ አውቄ ። ሲንቀረፈፉ ፡ ኖሩና ፡ አሁን-
አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ የለመኑት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ አሉ ፡ »
ሲሉ ፡ ሁለተኛዋ ፡ መለሱላቸው ። አጃቢዎች ፡ ባዶ ፡ እጃ
ቸውን ፡ ወደ ፡ ሞገመነ ፡ ገሰገሱ ።

ለመድረስ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡
ሲቀራቸው ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ጐረምሶች ፡ ከመንገድ ፡
ላይ ፡ ጠብቀው ፡ ተቀበሏቸውና ፡ ኬወርጌ ፡ አለመምጣቷ ፡
ሲታወቅ ፡ ባልቴቶችም ፡ ልጃገረዶቹም ፡ ዋይታውን ፡
ገቡበት - ልጃችን ፡ እህታችን ፡ ውሃ ፡ በላት ! ወዬው ፡
እኛ ፡ ውሃ ፡ እንሁንልሽ ! እሱው ፡ ሞሽሮ ፡ እንደፈጠረሽ ፡
ለሙሽርነቱ ፡ ጠራሽ ! ወዬው ! ወዬው ፡ ኬወርጌ ! ጐረ
ምሶቹ ፡ ቶከራ ፡ ቃጣቸው ። ግማሹ ፡ ወደ ፡ አድማጠረ ፡
በአስቸኳይ ፡ ሰው ፡ ተልኮ ፡ ለወላጆቿ ፡ ያስታውቅ ፡ አለ ።
ግማሹ ፡ ወደሚጠረጥሩት ፡ ሠፈር ፡ እንዝመት ፡ አለ ።
ሽምግልገል ፡ ያሉት ፡ ደግሞ ፡ በመጀመርያ ፡ ወንዙንም ፡
ጫካውንም ፡ አካባቢውንም ፡ እንፈልግ ፡ አሉ ።

ወንዙን ፡ ከላይ ፡ እስከ፡ ታች ፡ አዳረሱት ። የሚመስላቸውንም ፡ ቦታ ፡ ዋናተኛ ፡ እየጠለቀ ፡ አየ ። ተከፋፍለው ፡ ግማሹ ፡ ጫካውን ፡ እየጣሰ ፡ ሲገባ ፡ ሌላው ፡ በየጉብታው ፡ እየወጣ ፡ ዙሪያውን ፡ ሲቃኝ ፡ ጀምበር ፡ ጠልቃ ፡ ምሽቱ ፡ ለዓይን ፡ ያዘ ።

ጥቂቶቹ ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። በሕይወት ፡ ካለች ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቃት ። በቀን ፡ ብርሃን ፡ ትገኛለች ። በሕይወት ፡ ከሌለችም ፡ ነፍሷን ፡ ይማረው ! አሁን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ?

አብዛኛው ፡ ወደሠፈር ፡ ለመመለስ ፡ ሲዘጋጅ—እስቲ በችቦ ፡ እንሞክር ። ችቦውን ፡ ለምልክት ፡ ስናወዛውዝ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ በፍርሃት ፡ ተደብቃ ፡ እንደሆን ፡ ትወጣለች ። ወድቃም ፡ እንደሆነ ፡ እንዳለንላት ፡ በማወቅ ፡ ትጽናናለች ። ወይም ፡ ምልክት ፡ ልትሰጠን ፡ ትችል ፡ ይሆናል—ሲል ፡ አንዱ ፡ ድንገተኛ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ ።

ከመንደር ፡ ችቦ ፡ አቀጣጥለው ፡ በየጉብታው ፡ እየቆሙ ፡ ያወዛውዙ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሞከሩ ። በመጨረሻም ፡ ከአንድ ፡ ረባዳ ፡ መሬት ፡ አንድ ፡ ስልምልም ፡ የሚል ፡ ብልጭታ ፡ ታዬ ። ቀጥሎም ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ እልም፡ ቡግ ፡ እያለ ፡ ተወዛወዘ ። ሁሉም ፡ ባንዴ ፡ እየተሯሯጡ ፡ ወደዚያው ፡ ሥፍራ ፡ ሄዱ ።

አንዲት ፡ የጭሰኛ ፡ ጐጆ ፡ ናት ። እርጅናና ፡ ቁስቁልና ፡ ያጠቃው ፡ ሰውዬ ፡ መድረሳቸውን ፡ ሲመለከት ፡ ችቦውን ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ቃጠሎውን ፡ እየሞቀ ፡ ጠበቃቸው ።

ከጐጆው ፡ ውስጥ ፡ ኬርወጌ ፡ በዚያ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ምሽት ፡ የሚያስጐመጅ ፡ የግራር ፡ እሳት ፡ ተቀጣጥሎላት



በእጐዛ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ስትሞቅ ፡ አገኙዋት ። ኬርወጌ ፡ በቅሎዋ ፡ ፈርጥጣ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ካወረደቻት ፡ በኋላ ፡ እንደምንም ፡ በልጓም ፡ አብርዳ ፡ ከኮርቻው ፡ ከተፈናጠረች ፡ በኋላ ፡ እያዘገመች ፡ ከዚህ ፡ ጭሰኛ ፡ ቤት ፡ ተጠግታ ፡ ነበር ።

ለሙሽራይቱና ፡ ለአጃቢዎቹ ፡ ከጐረቤት ፡ አንድ ፡ እልፍኝ ፡ ተዘጋጅቶላቸው ፡ ነበር ። ገብተው ፡ ጥቂት ፡ እንዳረፉ ፡ ወዲያው ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ቀረበ ። ዝናምና፡ ብርድ ፡ ላቆራመደው ፡ ሰውነታቸው ፡ እሳት ፡ ተነደደ ። ከሚላላኩት ፡ የጐረቤት ፡ ልጆች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ በመካከላቸው ፡ ስላልነበር ፡ ሙሽራይቱም ፡ አጃቢዎቹም ፡ ሳይተፋፈሩና ፡ ሳይሽኰረመሙ ፡ የደረሰባቸውን ፡ እያወጉ ፡ እየጐራረሱና ፡ እየተገባበዙ ፡ ተዝናንተው ፡ ቆዩ ። እንዲያውም ፡ ሠርገኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ወደ ፡ መርሳቱ ፡ ተቃርበው ፡ ነበር ።

ወደ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ላይ ፡ ከውጭ ፡ ጉረምሶች ፡ እየጨፈሩ ፡ መምጣታቸውን ፡ ሲሰሙ ፡ ተበራገጉና ፡ ከበሮዋቸውን ፡ ከጣሉበት ፡ አንስተው ፡ ሙሽራይቱን ፡ ከእልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ ጋርደው ፡ ከአንድ ፡ በኩል ፡ ተሰብስበው ፡ ተቀመጡ ። ጐረምሶቹ ፡ ገቡና ፡ ከአንድበኩል ፡ ተከማችተው ፡ ቆሙ ። የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ከበሮ ፡ ድልቅ ፡ ድልቅ ፡ ማለት ፡ ጀመረ ። ተመልካቹ ፡ አጫፋሪ ፡ ዳኛ ፡ ታዛቢ ፡ እየተጋፋ ፡ ቤቱን ፡ እስከገደቡ ፡ ሞላው ። ከመካከል ፡ ለመተያያና ፡ የእስክስታ ፡ መውረጃ ፡ ቦታ ፡ ተከልሎ ፡ ሲተው ፡ መቀመጫ ፡ ቀርቶ ፡ መቆሚያ ፡ ታጣ ። ወዲያውም ፡ የዘፈኑ ፡ ውድድር ፡ በቤት ፡ ወገን ፡ ተከፈተ ።

ባልቴቶቹ ፡ በጆሮዋ ፡ እያንጋገሩዋት ፡ እንዲት ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፡ ልጃገረድ ፡ ስታቀነቅን ፡ ሌሎች ፡ እያጨበጨቡ ፡ ይቀበሉዋታል ። ከበሮው ፡ ያጅባል ።

ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
እድማጠረ ፡ የሰብ ፡ መጭ ፡ ያአቦጂ ፡
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ።
ከዘር ፡ ጥሩ ፡ አድማጠረ ፡
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
እንደቅቤ ፡ የነጠረ ፡ ዮሆ ፤

አቀንቃኝዋ ፡ ስትጨርስ ፡ ጭብጨባው ፡ ደምቆ ፡ ከበሮው ፡ ድርብ ፡ እየተመታ ፡ አንድዋ ፡ ልጃገረድና ፡ አንዱ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ጕረምሳ ፡ እስክስታ ፡ ይገጥማሉ ፡ እም ! እም ! እም ! እስክስታ ፡ ወራጆቹ ፡ ክንዳቸው ፡ እስኪዝል ፡ ወገባቸው ፡ እስኪበጠስ ፡ ቅልጥማቸው ፡ እስኪሰማው ፡ አንገታቸው ፡ እስኪሰበር ፡ ትንፋሻቸው ፡ እያጠረ ፡ ሂዶ ፡ ላባቸው ፡ በግንባራቸው ፡ መንቆርቆር ፡ እስኪጀምር ፡ ድረስ ፡ ተዋጥተው ፡ ጫን ፡ ጫን ፡ እየተነፈሱ ፡ ሲቀመጡ ፡ የወንድ ፡ አቀንቃኝ ፡ ተተካ ።

ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
የሰው ፡ አባት ፡ አንድ ፡ አዳም ፡ ነው ፡
የወንዝ ፡ አባት ፡ አንድ ፡ አዋሽ ፡ ነው ።
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
ዘር ፡ ቢፈለግ ፡ ከነሥሩ ፡
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
ሞገመነ ፡ ብለው ፡ ይጥሩ ።
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡



የቦርጋ ፡ ፈረስ ፡ ድብረቶ ፡
ማን ፡ ያቆመዋል ፡ ከቶ ።
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
ሙሽሪት ፡ ክብር ፡ ይሰማሽ ፡
ለትልቅ ፡ ቤት ፡ በተመረጥሽ ።
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፤
ቤቶቹ ፡ ደግሞ ፡ መልሱን ፡ ሰጡ ።
አዝመራው ፡ የለመለመ ፡
ቤቱ ፡ የተሸለመ ፡
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፤
በረቱ ፡ የጠበበ ፡
ጕተራው ፡ የደለበ ፤
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ፡
የፈረሱ ፡ ስም ፡ ቴላምሶ ፡
ሳይገል ፡ ሳይጥል ፡
መች ፡ ይመጣል ፡ ተመልሶ ፡
ዮሆ ፡ ዮሆ ፡ ሲያን ፡ ዮሆ ።

ግዳይ ፡ እየተቆጠረ ፡ የፈረስ ፡ ስም ፡ እየተሞገሰ ፤ እየተቀደሰ ፡ ሀብት ፡ ሙያ ፡ እየተዘረዘረ ፡ ተመልካችና ፡ አጫፋሪ ፡ የእያንዳንዱን ፡ ወገን ፡ ግጥም ፡ በማበላለጥ ፡ እያዳነቀ ፡ ውድድሩ ፡ እስከንጋቱ ፡ አስራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ሲቀልጥ ፡ አደረ ። በእስክስታ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ ሲያይል ፡ በግጥም ፡ ደግሞ ፡ ባልቴቶቹ ፡ አልተቻሉም ፡ ነበር ።

ዋናው ፡ ሚዜ ፡ የሙሽራይቱን ፡ ቡልኮ ፡ ኩታና ፡ ቀሚስ ፡ በባሕር ፡ ማዶ ፡ ግምጃ ፡ ሸፍኖ ፡ ግልገል ፡ ሚዜው ፡ ተከትሎት ፡ ሲገቡ ፡ ጭፋሮውና ፡ ዘፈኑ ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

ለዋናው ፡ ባልቴት ፡ ቀረበላቸው ። ባልቴቷ ፡ እያገላበጡ ፡ አዩና ፡ « በአገራችሁ ፡ እንዝርት ፡ የለም ፡ ወይ ! ባገራችሁ ፡ ደጋኑ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብሯል ፡ ወይ ! » ሲሉ ፡ አሽሟጠጡና ፡ ተቀበሉ ። ከዚያም ፡ ሚዜዎች ፡ ሙሽራይቱን ፡ ተሸከሙና ፡ ሁሉም ፡ ባንድነት ፡ እየጨፈሩ ፡ ወደሙሽራው ፡ እልፍኝ ፡ ገባች ። ሙሽራው ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ አልነበረም ። ያመጣችው ፡ መኝታ ፡ ያመጣችው ፡ መጋረጃ ፡ ተዘጋጅቶላት ፡ ሁሉም ፡ ወጡ ። ከመጋረጃው ፡ ውጭ ፡ እሳት ፡ ለማንደድና ፡ ለመላላክ ፡ አንዲት ፡ የዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ቀረች ።

በበነጋው ፡ ጧት ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ላይ ፡ አጅበው ፡ የመጡት ፡ ሴቶች ፡ ከአደሩበት ፡ ማረፊያ ፡ ተጠርተው ፡ ወደሙሽራይቱ ፡ እልፍኝ ፡ ገቡ ። ሚዜዎችና ፡ ሌሎች ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አጫፋሪዎችም ፡ ከበሮ ፡ ይዘው ፡ ገቡ ። ከዘፈኑ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ቁርስ ፡ ቀረበ ። የቆሎ ፡ ገንፎ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ጮፍቆ ፡ በቢላ ፡ የሚቆረስ ፡ የመሰለ ፡ እርጎ ፡ በተለይ ፡ የተበጠበጠ ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ምርጡ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ « በሞቴ ! » የሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ነው ። በጭፈሮ ፡ ዝሎ ፡ ላደረ ፡ አካል ፡ በድካም ፡ ለተብላላ ፡ ሆድ ፡ ጥሩ ፡ ቁርስ ፡ የሠርጉ ፡ ዋና ፡ ማሠረጊያ ፡ ነው ። የሙሽራው ፡ እናትም ፡ በየመሶቡ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ጋብዘው ፡ ሙሽራይቱን ፡ አባበሉ ። ረፈድፈድ ፡ ሲል ፡ ዘፈንና ፡ ጭፈሮ ፡ ተጀመረ ። አሁን ፡ ግን ፡ ውድድር ፡ አልነበረም ። የወንድ ፡ ወገን ፡ የሴት ፡ አጃቢ ፡ ተባብረው ፡ ሲያቀንቅኑና ፡ ሲቀባበሉ ፡ እስክስታም ፡ ሲወርዱ ፡ እንደቆዩ ፡ የሙሽራው ፡ እናት ፡ በአዲስ ፡ የባሕር ፡ ሽቶ ፡ የተለወሰ ፡ ቅቤ ፡ በጌጥ ፡ በተሸለመ ፡ ዕቃ ፡ በደንገጡር ፡ አሲዘው ፡ ገቡ ። ዘፈኑ ፡ እርጭ ፡ አለ ። እማት ፡ የቅቤ ፡ ዕቃውን ፡



ከፍተው ፡ መዓዛው ፡ የሚያውደውን ፡ ልውስ ፡ ቅቤ ፡ በአምስት ፡ ጣታቸው ፡ እየዛቁ ፡ ባልቴቶችንና ፡ ልጃገረዶችንም ፡ በሙሉ ፡ ከጸጉራቸው ፡ ተርፎ ፡ ግንባራቸው ፡ ሁሉ ፡ እስኪጭረቀረቅ ፡ ድረስ ፡ ቀቡዋቸው ። አሁንም ፡ ዘፈኑ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ተሟሟቀ ፡ በግምጃ ፡ የተሸፈነ ፡ ዕቃ ፡ የያዙት ፡ ጐረምሶች ፡ የሙሽራውን ፡ አባት ፡ ተከትለው ፡ ገቡ ። እማች ፡ ዕቃውን ፡ በግምጃው ፡ እንደተጠቀለለ ፡ ለዋናው ፡ ሚዜ ፡ አስረከቡትና ፡ ወጡ ። ዋናው ፡ ሚዜ ፡ ዕቃውን ፡ እየነጣጠለ ፡ ለዋናዋ ፡ ባልቴት ፡ አስረከበ ። ለሙሽሪት ፡ አባት ፡ አንድ ፡ ወፍራም ፡ ብልኮና ፡ ለአንድ ፡ ሱሪ ፡ የሚበቃ ፡ መሐሙዲ ፡ ጨርቅ ፤ ለሙሽሪት ፡ እናት ፡ አንድ ፡ ቀጭን ፡ ኩታ ፡ ጥንድ ፡ የብር ፡ ጉትቻና ፡ ሃያ ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ ነበር ።

አጃቢዎቹ ፡ ከበሉ ፡ ከጠጡ ፡ የመጨረሻውንም ፡ እስክስታ ፡ ካሳዩ ፡ በኋላ ፡ ከረፋዱ ፡ በአምስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ላይ ፡ ተሰናብተው ፡ «የሞገመኑ ፡ ግንድ ፡ ይለምልም ፡ የቦርጋ ፡ ዘር ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ እንደባሕር ፡ አሸዋ ፡ እንደዱር ፡ አራዊት ፡ ይብዛ ፡ » በማለት ፡ በዘፈን ፡ እየመረቁ ፡ ወደ ፡ ሠፈራቸው ፡ ተመለሱ ።

በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ በአጋዝ ፡ ቦርጋ ፡ ዋና ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ሙክትና ፡ አምስት ፡ ዶሮ ፡ የታረደበት ፡ መጠነኛ ፡ ግብዣ ፡ ተደገሰና ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ ከተበላና ፡ ከተጠጣ ፡ በኋላ ፡ ቴሊ ፡ ከአባቱ ፡ ምርቃት ፡ ተቀበለ ። « ሽንትህ ፡ የተመረቀ ፡ ከብትህ ፡ የተባረከ ፡ አዝመራህ ፡ የለገሠ ፡ ይሁን ፡ » ሲሉት ፡ ተጐንብሶ ፡ ሳመና ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ የማንንም ፡ ዓይን ፡ ለማየት ፡ አፍሮ ፡ አንገቱን ፡ እንዳቀረቀረ ፡ ወደሙሽራይቱ ፡ እልፍኝ ፡ ተፈተለከ ።

እምስቱን ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ቴሊ ፡ በዘፈንም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራይቱን ፡ ለማየት ፡ ሞክሮ ፡ አልሆነለትም ፡ ነበር ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ነበረች ። ከመጋረጃ ፡ ወጥታ ፡ ሳለች ፡ ድንገት ፡ ኮቴ ፡ የሰማች ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያው ፡ ትሠወር ፡ ነበር ። እሳት ፡ በማንደድ ፡ ቡና ፡ በማፍላት ፡ ከውስጥ ፡ ወደውጭ ፡ ከውጭ ወደ ፡ ውስጥ ፡ በመላላክ ፡ የሰነበተች ፡ እንዷት ፡ የዘጠኝ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። እንደዚሁም ፡ ሁለቱ ፡ ሚዜዎች ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ መጋረጃው ፡ ሳይገቡ ፡ በእልፍኙ ፡ ሆነው ፡ ሙሽራይቱ ፡ የሚያስፈልጋት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ቴሊ ፡ ገርበብ ፡ ያለውን ፡ በር ፡ ከፍቶ ፡ ሲገባ ፡ቤቱ ፡ በሚያስደነግጥ ፡ ጸጥታ ፡ ተቀበለው ። ከመጋረጃው ፡ ማዶ ፡ ሙሽሪት ፡ ትንፋሽዋን ፡ ስንኳ ፡ አፍና ፡ ተሸሽጋለች ። ልጂቱና ፡ ሚዜዎቹ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ አቀራርበው ፡ ሄደዋል ። እሣቱ ፡ ደከምከም ፡ ብሎ ፡ የክፍሉ ፡ ጨለማ ፡ ለዓይን ፡ ይይዝ ፡ ነበር ። ቴሊ ፡ ከምድጃው ፡ አጠገብ ፡ ቆመና ፡ እንጨቱን ፡ በእግሩ ፡ እየገፋ ፡ ቆሰቆሰው ። ተንጣጣና ፡ እንደገና ፡ ቦግ ፡ ብሎ ፡ መንደድ ፡ ጀመረ ። ዱካ ፡ አቀረበና ፡ ተቀመጠ ። ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ። ጨዋታ ፡ አማረው ። መጋረጃውን ፡ ገልጦ ፡ ሚስቱን ፡ ለማየትም ፡ ከጀለ ። ግን ፡ ዓይኑን ፡ ገልጦም ፡ ሆነ ፡ ከድኖ ፡ በዚያ ፡ ደብዛዛ ፡ የእሣት ፡ ብርሃን ፡ መካከል ፡ የሚታዩት ፡ ከውጭ ፡ ጀሮዋቸውን ፡ ከግድግዳው ፡ ጋር ፡ አጣብቀው ፡ ኮሽታ ፡ የሚያዳምጡት ፡ የመንደር ፡ ጐረምሶች ፡ ናቸው ። ዓይነ ፡ ሕሊናው ፡ ግድግዳውን ፡ አልፎ ፡ እርሱም ፡ በሌሎች ፡ ሠርግ ፡ ጊዜ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ እንዳደረገው ፡ ግማሹ ፡ ተንበርክኮ ፡ ግማሹ ፡ በግር ፡ ጣቱ ፡



ተቆራጦ ፡ ቆሞ ፡ ግማሹ ፡ ተጋድሞ ፡ ግማሹ ፡ ተቀምጦ ፡ ምድረ ፡ የመንደር ፡ ጐረምሳ ፡ ትንሽ ፡ ቀዳዳ ፡ ያገኘ ፡ በዚያች ፡ በኩል ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ያላገኘ ፡ ጀሮውን ፡ አቁሞ ፡ ሲመለከተው ፡ አየ ። ድንገት ፡ ቢያስነጥስ ፡ ድንገት ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ካፉ ፡ ብትወጣ ፡ ከበድ ፡ አድርጎ ፡ ስንኳ ፡ ቢተነፍስ ፡ ጢት ፡ የቡና ፡ መጠጫ ፡ እንደሚሆን ፡ ያውቀዋል ። ሲያስበው ፡ ሰውነቱን ፡ ሰቅጥጥ ፡ አለው ። ይህ ፡ ፌዝ ፡ ባይኖር ፡ ሚስት ፡ ማግባትስ ፡ መልካም ፡ ነበር፡ አለ ፡ በሆዱ ። ሳይንቀሳቀስ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ቆየ ። ጀርባውንም ፡ ደከመው ። ቀስ ፡ ብሎ ፡ እሳቱን ፡ አጥፍቶ ፡ ከፍሉ ፡ በጨለማ ፡ ሲዋጥ ፡ ኮቴው ፡ እንዳይሰማ ፡ በጣቶቹ ፡ እየተረገጠ ፡ በዳበሳ ፡ መጋረጃውን ፡ ገልጦ፡ገባ ።

ቀን ፡ ቀን ፡ የትም ፡ እየዋለ ፡ ማታ ፡ ገብቶ ፡ ከእሣቱ ፡ ዳር ፡ እየተቀመጠ ፡ ከዚያም ፡ እሣቱን ፡ አጥፍቶ ፡ በዳበሳ ፡ ወደሙሽራይቱ ፡ መጋረጃ ፡ እየደረሰ ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በላይ ፡ ኮቴውንም ፡ ትንፋሹንም ፡ ሳያሰማ ፡ ሰነበተ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የመንደሩ ፡ ጐረምሶች ፡ ከቤቱ ፡ ተዛንብ ፡ እያደሩ ፡ አድፍጠው ፡ ሲያዳምጡ ፡ ሰነበቱ ።

ዝምታ ፡ መታፈን ፡ ነው ። ጸጥታና ፡ ጨለማም ፡ አራት ፡ ዓይን ፡ እንዳለው ፡ ጭራቅ ፡ ያስፈራል ። አንድ ፡ ቀን ፡ ቴሊ ፡ አንድ ፡ ሶስት ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ ጠጥቶ ፡ ሰውነቱ ፡ በስሜት ፡ ተወጥሮ ፡ ወደ ፡ እልፍኙ ፡ ሲገባ ፡ ነገር ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ረሳው ። ባይረሳውም ፡ ታክቶት ፡ ሰልችቶት ፡ አቅቶት ፡ ነበር ። ሚስቱን ፡ ወደ ፡ ቷል ። ሰውነቱ ፡ እየተቅበጠበጠ ፡ ጣራ ፡ እስኪሰነጠቅ ፡ መዝፈንም ፡ መሬት ፡ እስኪበሳ ፡ መጨፈርም ፡ እስኖው ። እንዳጋጣሚ ፡ እሣቱ ፡ ደህና ፡ እየተንቀለቀለ ፡ ይነድ ፡ ነበር ።

በቀጥታ ፣ ተፈናጥሮ ፣ መጋረጃውን ፣ ገልጦ ፣ « አንቺዬ ፣ ብቅ ፣ ብዬ ፣ እባክሽ ፣ ፊትሽን ፣ ለማየት ፣ ርቦኛል ፣ » አለ። መልስ ፣ አልሰጠችውም ።

ከውጭ ፣ ምድረ ፣ ጐረምሳ ፣ ኩታውን ፣ እየጠቀለለ፣ አፉን ፣ ወተፈ ።

« እኮ ፣ ነይ ፣ ልይሽ ! » አለ ፣ በድጋሚ ። ሙሽሪት ፣ አልተነቃነቀችም ። በክንዱ ፣ ሊጐትታት ፣ ሞከረ ። ግን ፣ አልሆነም ። አልጋውን ፣ ሙጭጭ ፣ አድርጋ ፣ ይዛ ፣ እልፍኙን ፣ የምታተራምሰው ፣ ሲሆን ፣ ጊዜ ፣ መጋረጃው ፣ እንደተገለጠ ፣ እሳቱ ፣ እንደነደደ ፣ በዚያው ፣ ቀረ ።

በበነጋው ፣ ጧት ፣ ከወላጆቹ ፣ አዳራሽ ፣ ቡና ፣ ተፈልቶ ፣ ቁርስ ፣ ቀርቦ ፣ ዘመድ ፣ አዝማድ ፣ የመንደር ፣ ሽማግሌ ፣ ጐረምሳ ፣ ተሰብስቦ ፣ እንዳለ ፣ ቴሲ ፣ ምንም ፣ ነገር ፣ እንዳልሆነ ፣ ሁሉ ፣ ብልኮውን ፣ አጣፍቶ ፣ ዘው ፣ ሲል ፣ እንደ፡ ሳቅ ፣ ፈነዳበት ። « አንቺዬ ! ናፍቀሽኝ ፡ ጐምጅቼ ፣ ነበር !! » ሲሉ ፣ ጐረምሶች ፣ እንደዘፈን ፣ ባንድ፣ ቃል ፣ አስተጋቡ ።

ቴሲ ፣ አንድ ፣ እግሩ ፣ የበሩን ፣ መድረክ ፣ እንዳለፈ ፣ ወዲያው ፣ ፊቱን ፣ መልሶ ፣ አንገቱን ፣ አቀርቅሮ ፣ በቁልቁለቱ ፣ ወደሜካው ፣ ተፈተለከ ።

እንደመሮጥ ፣ እየቃጣው ፣ ሰውነቱ ፣ በሃፍረት ፣ ሲንቀጠቀጥ ፣ ባንድ ፣ በኩል ፣ ግን ፣ እፎይታ ፣ ተሰማው ። እንግዲህ ፣ አይታፈንም ። እንግዲህ ፣ ጐረምሶቹ ፣ ከቤቱ ፣ ዙሪያ ፣ አድፍጠው ፣ አያድሩም ። ጉዱን ፣ ተወጣው ። ከእንግዲህ ፣ ሰላም ፣ ነው ።



# ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልዎ ።

በሩ ፣ ተንኳኩቶ ፣ ሲከፈት ፣ ኀሩይ ፣ ከእንቅልፉ ፣ ብንን ፣ አለና ፣ ዓይኑን ፣ አርገበገበ ። የክፍሉ ፣ መብራት ፣ በርቶ ፣ ነበር ። ወይም ፣ ረስቶት ፣ ተኝቶ ፣ ሲበራ ፣ አድሯል ።

« አትነሣም ፣ እንዴ ! » አለ ፣ ቢተው ፣ ከአልጋው ፣ አጠገብ ፣ ቆሞ ።

ኀሩይ ፣ አፉን ፣ እያዛጋ ፣ ሰዓቱን ፣ ተመለከተ ። ለአስር ፣ ሰዓት ፣ ሩብ ፣ ጉዳይ ፣ ይላል ። « በውድቅት ፣ ሌሊት፣ ምንድን ፣ ነውኮ ፣ የምትረብሸው ፣ » ሲል ፣ አንሶላውን ፣ ተከናነበ ።

« አፋ ! » ቢተው ፣ ብርድ ፣ ልብሱንና ፣ አንሶላውን ፣ ከላዩ ፣ ላይ ፣ ገፈፈበት ። « ደግሞ ፣ አታፍርም ፣ ተኝተህ ፣ ስንኳ ፣ ስታድር ? ነገምኮ ፣ እንዲሁ ፣ ታደርግ ፣ ይሆናል ። መጥኔ ፣ ፈረደባት ። ብቻ ፣ እኛን ፣ እንዳታዋርደን ፣ » አለ ፣ በቀልድ ፣ ቁጣ ።

« ዛሬስ ፣ ሆነ ፣ ነገ ፣ እንቅልፍ ፣ የማያስተኛ ፣ ምን ፣ ምክንያት ፣ አለ ? » ሲል ፣ እያጉመተመተ ፣ ከአልጋው ፣ ወርዶ ፣ እንደ ፣ ዓይነ ፣ ሥውር ፣ ነጠላ ፣ ጫማውን ፣ በእጁ ፣ እየደባበሰ ፣ ፈለገ ።

ቢተው ፣ በመገረም ፣ ራሱን ፣ ነቀነቀ ። ኸረ ፣ እርሙን! ሰው ፣ አይሆንም ። ከአካባቢው ፣ ወግ ፣ ጋር ፣ ፈጽሞ ፣ የማይገጥመው ፣ ግዴለሽ ፣ ጠባዩ ፣ በሠርጉ ፣ ቀን ፣ ስንኳ ፣ ተኝቶ ፣ ለማርፈድ ፣ ይፈልጋል ። ቢተው ፣ የራስ ፣ ሚዜው፣ ነው ።

ኀሩይ ፡ ጺሙን ፡ ላጭቶ ፡ ፊቱን ፡ ታጥቦ ፡ ልብሱን ፡
እስኪለብስ ፡ ድረስ ፡ ሌሎቹ ፡ ሚዜዎችና ፡ አጃቢዎች ፡
መጡ ። ከዚያም ፡ ከመኝታ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡
ከሽንት ፡ ቤት ፡ ወደሳሎን ፡ ሲሄድ ፡ ዙሪያውን ፡ ከበው ፡
እያዋከቡና ፡ እያሽበለበሉ ፡ አንዱ ፡ ክራባቱን ፡ ሲያስተ
ካክልለት ፡ ሌላው ፡ ኮቱን ፡ እንደመጠራረግ ፡ ሲል ፡ ሶስ
ተኛው ፡ የጫማውን ፡ ማሠሪያ ፡ ሲቋጥርለት ፡ የጸጉሩን ፡
አበጣጠር ፡ የሱሪውን ፡ አተጣጠቅ ፡ የመሐረሙን ፡ አቀ
ማመጥ ፡ ሲመረምሩ ፡ ራሱ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ የማያውቅ ፡
ሕጻን ፡ አስመሰሉት ።

« አፋ ! አቦ ፡ ተውኝ ! » ሲል ፡ እጁን ፡ አራገበ ፡

« የምንሰደበውኮ ፡ እኛ ጭምር ፡ ነን » አለ ፡ ቢተው ፡

እንደሚኒስትር ፡ ሹፌር ፡ የአውቶሞቢሉን ፡ በር ፡
ቀድመው ፡ ከፍተው ፡ አስገቡት ። ማርቸዲስ ፡ ሲሳፈር ፡
የመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ ባይሆንም ፡ ከግራ ፡ ቀኙ ፡ በባል
ደረባ ፡ ታጅቦ ፡ በሹፌር ፡ ሲፈስስ ፡ የፌዝ ፡ ኩራት ፡ ተሰ
ማው ። ከወንዝ ፡ ዳር ፡ ከአሸዋ ፡ ክምር ፡ ቤተ ፡ መንግ
ሥት ፡ ተሠርቶ ፡ መኳንንትና ፡ መሳፍንት ፡ ተሰይመው ፡
ሹምሽረት ፡ የሚደረግበት ፡ የልጆች ፡ ወይም ፡ የልጅነት ፡
ጨዋታ ፡ መሰለው ።

« የነገርንህን ፡ በሙሉ ፡ ታስታውሰው ፡ የለ ? » ሲል
ቢተው ፡ ጠየቀ ። ኀሩይ ፡ በአዎንታ ፡ ራሱን ፡ አወዛወዘ ።

« በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ሲጋራ ፡ ፈጽሞ ፡
አይጨስም ፡ »

« እሺ ፡ »



« ደግሞ ፡ » አለ ፡ የእግሩ ፡ ሚዜ ፡ አባተ ፡ « ኬኩ ፡
ሲቆረስ ፡ ቢላዋውን ፡ የምትይዘው ፡ ርሷ ፡ ስትሆን ፡ አንተ ፡
እጅዋን ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ይዘህ ፡ ትረዳታለህ »

« ገብቶኛል ፡ »

« አቀማመጡን ፡ እንዳትረሳ ። አንተ ፡ ሁልጊዜ ፡
ከግራ ፡ በኩል ፡ ነው ፡ የምትሆነው ፡ » ሲል ፡ ቢተው ፡
ለአስራ ፡ አንደኛ ፡ ጊዜ ፡ አስታወሰው ። ኀሩይ ፡ አይረሳም።

« ዋናው ፡ ነገር ፡ » ሲል ፡ ሁለተኛው ፡ ቀጠለ ፡ « ዋ
ናው ፡ ነገር ፡ » ነገሩን ፡ ለማጠንከር ፡ በጨለማው ፡
ጣቱን ፡ ቀሰረ ፡ « አለመቅለብለብ ፡ ነው ። ረጋ ፡ ማለት ፡
አለብህ ። እንደወጉ ፡ እርሷንም ፡ ሆነ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቿን ፡ ከአ
ሁን ፡ በፊት ፡ የምታውቃት ፡ መምሰል ፡ የለብህም ። እጅ ፡
ነትንሣ ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ ፈገግታ ፡ ሳታሳይ ፡ በቁጠባ ፡
ነው ። ሲጋራህን ፡ ከአሁኑ ፡ ጨርስ ፡ » ከፓኬቱ ፡ አው
ጥቶ ፡ ሰጠው ።

ኀሩይ ፡ ሲጋራውን ፡ አቀጣጠለና ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።
ከስድስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያፈቀራትን ፡ በክፉና ፡ በደግ ፡
አብራው ፡ የኖረችውን ፡ ቀጸላን ፡ እንዴት ፡ የማያውቃት ፡
ሊመስል ፡ ይችላል ? እንደ ፡ ቤቱ ፡ በወጣበትና ፡ በገባበት ፡
ቤተሰብ ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡ ባይተዋር ፡ ይመስላል ? ቧ
ልት ፡ ነው !

ኀሩይና ፡ ቀጸላ ፡ የተዋወቁት ፡ በጐሬ ፡ ከተማ ፡ ትም
ህርት ፡ ቤት ፡ እርሱ ፡ አስረኛ ፡ ክፍል ፡ ደርሶ ፡ እርሷ ፡
ስድስተኛ ፡ ሳለች ፡ ነው ። የሁለቱም ፡ ቤተሰቦች ፡ የጐሬ ፡
ከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ ናቸው ። በትንሽ ፡ ከተማ ፡ ሁሉም ፡

ሁሉን ፣ ስለሚያውቅ ፣ የሁለቱ ፣ ቤተሰቦች ፣ በቅርብ ፣ ይ
ዋወቃሉ ።

ሁለቱ ፣ ወጣቶች ፣ እንደዋዛ ፣ የጀመሩት ፣ ዕው
ያና ፣ ወዳጅነት ፣ እየጠነከረና ፣ እየጠለቀ ፣ ሄደ ። የጥናትያ
ሆነ ፣ የዕረፍት ፣ ጊዜያቸውን ፣ አብረው ፣ ሲያሳልፉ ፣ ሊ
ጣጠሉ ፣ የማይችሉ ፣ አንዱ ፣ ለሌላው ፣ የተፈጠረ ፣ መሀ
ናቸው ፣ ይሰማቸው ፣ ጀመር ። በመካከላቸው ፣ የነበረው
የሚያቅበጠብጥ ፣ ፍቅር ፣ አይደለም ። የመዝናናት ፣ የመ
ስማማት ፣ የመተሳሰብ ፣ ዓይነት ፣ ነው ።

ስለ ፣ ኑሮዋቸው ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ያሰቡት ፣ ጎሩይ
ኮሌጅ ፣ ለመግባት ፣ በተነሣ ፣ ጊዜ ፣ ነበር ። ለዘለዓለሙ
እንዳይተጣጡ ፣ ስጉና ፣ የምሽት ፣ ጀንበር ፣ ለምስክርነት ፣
ቆማ ፣ ወፎች ፣ ሲያቀነቅኑ ፣ ዛፎች ፣ እስክስታ ፣ ወርደ
ውላቸው ፣ በዋርካ ፣ ዛፍ ፣ ጥላ ፣ ሥር ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣
ፈጸሙ ። በዕንባ ፣ ተለያይተው ፣ ሲጻጻፉ ፣ ከርመው ፣ ለዕ
ረፍት ፣ ሲመለስ ፣ ለአባቱ ፣ ነግሮ ፣ ሽማግሌ ፣ ተላከ ።
ግን ፣ በአዛውንቶች ፣ ግምት ፣ ልጅ ፣ ያቦካው ፣ ለራት ፣
አይበቃም ፣ ይባላልና ፣ የእነርሱን ፣ መፋቀር ፣ የእነር
ሱን ፣ መስማማት ፣ ወላጆቹ ፣ ዋጋ ፣ አልሰጡትም ። የጎ
ሩይ ፣ አባትኳ ፣ በመጀመርያ ፣ እንዲያው ፣ ያው ፣ ያገር ፣
ወንዝ ፣ ትዝታ ፣ ተቀስቀሶባቸው ፣ ቅር ፣ ተሰኙ ፣ እንጅ ፣
አምርረው ፣ አልነበረም ።

« ልጄ ! ለዚህም ፣ ደረስክ ? እንደአባት ፣ ወልጄ ፣
አፈር ፣ በበላሁትና ፣ እኔ ፣ ሳላስበው ፣ አንተ ፣ ለራስህ ፣
ማሰብ ፣ ጀመርክ ? መቸም ፣ ለነገሩማ ፣ መማርህ ፣ ለዚሁ ፣
አይደል ! » ጸጉራቸውን ፣ አከኩ ። « እንዲያው ፣ ግን ፣
ለነገሩ ፣ ወንዝህን ፣ ሳታየው ፣ ወገንክን ፣ ሳትተዋወቅ ፣



በሰው ፣ አገር ፣ እንድትቀር ፣ ያደረግሁህ ፣ እኔው ፣ ነኝ ።
ለመሆኑ ፣ ደህና ፣ ልጅ ፣ ናት ? » ብለውት ፣ ነበር ። የእጅ ፣
ውዝዋዜ ፣ የፊት ፣ ገለጣ ፣ ባጀበው ፣ የቃላት ፣ ብዛት ፣
አረጋገጠላቸው ። አንድ ፣ ልጃቸው ፣ ነውና ፣ ኮሌጅ ፣ የተ
ማረ ፣ አዋቂ ፣ ነውና ፣ « ከሆነችህማ ፣ ቤተሰቦችኳ ፣ አይ
ከፉም ፣ » ሲሉ ፣ መረቁት ።

የቀጸላ ፣ አባት ፣ ፊታውራሪ ፣ ታደገ ፣ ግን ፣ በቀላሉ ፣
አልተበገሩም ። የጎሩይ ፣ አያት ፣ ለደጃዝማች ፣ ጉልቻ ፣
አድረው ፣ ወደ ፣ ጉሬ ፣ ከመምጣታቸው ፣ በፊት ፣ በትው
ውልድ ፣ አገራቸው ፣ በኤልያስ ፣ ሽማኔ ፣ ነበሩ ፣ እየተባለ ፣
ይወራል ። ታዲያ ፣ በነጠረ ፣ ዘራቸው ፣ ሽማኔ ፣ ቀርቶ ፣
ገበሬ ፣ በሌለበት ፣ የነፍጠኛ ፣ ሐረጋቸው ፣ የሚመኩት ፣
የቀጸላ ፣ አባት ፣ ፊታውራሪ ፣ ታደገ ፣ ሽማግሌዎቹን ፣ ፊት
ነስተው ፣ መለሱዋቸው ። ቁማ ፣ የቀረች ፣ ሴት ፣ ልጅ ፣
ብትሆንም ፣ ወግ ፣ ስለሆነ ፣ መግደርደሩ ፣ አይቀርምና ፣ ሽማ
ግሎቹ ፣ ድጋሚ ፣ ሄዱ ። ፊታውራሪ ፣ ግን ፣ የባሰውን ፣
ተኮፍሰው ፣ የባሰውን ፣ ተሶርፈው ፣ አሽሙር ፣ ነገር ፣ ጣል
ጣል ፣ አድርገው ፣ በእምቢታ ፣ መለሱዋቸው ። የጎሩይ ፣
አባት ፣ የፊታውራሪን ፣ ንቀት ፤ ተደፈርኩ ፣ የማለትም ፣
ቁጣ ፣ ሽማግሎቹ ፣ አለሰልሰው ፣ ያመጡትንም ፣ መልስ ፣
ሲሰሙ ፣ በበኩላቸው ፣ አካኪዘራፍ ፣ አሉ ። በልጃቸው ፣
ጠባይ ፣ ይተማመኑበታል ። በዕውቀትም ፣ ረገድ ፣ ከጉሬ ፣
ነዋሪዎች ፣ መካከል ፣ በንጉሥ ፣ ተመርጦ ፣ ወደ ፣ አዲስ ፣
አበባ ፣ ለመምጣት ፣ የመጀመሪያው ፣ ነው ። ማን ፣ ከማን ፣
ያንሳልና ፣ ነው ! ክብራቸው ፣ ተነክቷል ። የሕግ ፣ ዘመን ፣
ሆነና ፣ ጊዜ ፣ ያነሳው ፣ ሁሉ ፣ መኳንንት ፣ ተባለና ፣ ክንዳ
ቸውን ፣ ሳይንተራሱት ፣ ተዋረዱ ። ምንም ፣ ሠርቶ ፣ አዳሪ ፣
ቢሆኑ ፣ ጦር ፣ መወርወር ፣ ጋሻ ፣ መመከት ፣ ጠመንጃ ፣

ማንጣጠር ፣ ባላቃታቸው ፣ ነበር ። ተፋልመው ፣ ይወጣላ ቸው ፣ ነበር ።

ግን ፣ መቸም ፣ የወለደ ፣ አንጀት ፣ ጨክኖ ፣ አይጨ ክንምና ፣ ጎሩይ ፣ በምድረ ፣ ዓለም ፣ እንደርሱ ፣ አዋቂ ፣ የሌለ ፣ መስሎ ፣ የሚታያቸውን ፣ አባቱን ፣ ሲያባብል ፣ ሲሰብክና ፣ ሲያግባባ ፣ ቀጸላ ፣ « ዲቃላ ፣ አስታቅፋችኋ ለሁ ፣ ወይም ፣ ራሴን ፣ እገድላለሁ ፣ » እያለች ፣ ቤተሰቦ ችዋን ፣ ስታስፈራራ ፣ ከረመችና ፣ መስከረም ፣ ሲጠባ ፣ የሁለቱም ፣ ቤተ ፣ ሰቦች ፣ ጊዜ ፣ በወለደው ፣ የልጆች ፣ ፈቃድ ፣ ተረቱ ። የቤት ፣ ቤተሰብ ፣ ክብራቸውንና ፣ ደረጃ ቸውን ፣ ለልጃቸው ፣ ሕይወት ፣ ሠው ። የወንድ ፣ ቤተሰብ፣ ለልጃቸው ፣ ፈቃድ ፣ ሲሉ ፣ ውርደታቸውን ፣ ረሱ ። በሁ ለቱ ፣ ወጣቶች ፣ መካከል ፣ ጉዳዩ ፣ ከበሰለ ፣ በኋላ ፣ ጎሩይ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ ሊመጣ ፣ አስር ፣ ቀን ፣ ብቻ ፣ ሲቀረው ፣ ሽማግሌዎች ፣ እንደገና ፣ ተልከው ፣ ስምምነት ፣ ተደረገ ። በሶስተኛው ፣ የኮሌጅ ፣ ዓመት ፣ አሁንም ፣ በስንት ፣ መከራ አስፈቅዶ ፣ ለመጀመርያ ፣ ጊዜ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ መጥታ ፣ ከርሱ ፣ ጋር ፣ ከረመች ። በዚህም ፣ የተፈጠረው ፣ ሐሜት ፣ የጐሬን ፣ ሕዝብ ፣ ቀጥ ፣ አድርጎ፣ አባጀው ። ድንግልናዋን፣ አስረክባ ፣ ተመለሰች ፣ ተባለ ። ከሌላ ፣ አርግዛ ፣ ስለ ፣ ነበር፣ ተላላው ፣ ልጅ ፣ ተሞኝቶ ፣ በሐኪም ፣ ለማስወጣት ፣ ነው ፣ ተባለ ። ወልዳ ፣ ጥላ ፣ መጣች ፣ ያሉም ፣ ነበሩ ። ንጽ ሕናቸውን ፣ የሚያውቁት ፣ ግን ፣ ሁለቱ ፣ ብቻ ፣ ነበሩ ። እርግጥ ፣ ስሜታቸው ፣ የተፈተነበት ፤ ሰውነታቸው ፣ የጋ ለበት ፣ አከላታቸው ፣ የተቅበጠበጠበት ፣ ጊዜ ፣ ነበር ። ግን ፣ ፓርላማውን ፣ ፒያሳውን ፣ ማርካቶውን ፣ አራዳው ፣ ጊዮርጊስን ፣ ቅድስት ፣ ሥላሴን ፣ ኮሌጁን ፣ ሲያሳያት ፣ ሲኒማ ፣ ቤት ፣ ሲወስዳት ፣ ቤተ ፣ መጻሕፍት ፣ ሲያስጐበ



ኛት ፣ ብዙው ፣ ጊዜ ፣ ሳይታወቃቸው ፣ ያልፍ ፣ ነበር ። ሁለ ቱም ፣ በትምህርት ፣ ቤት ፣ ዘመናቸው ፣ እንደዚህ ፣ የእ ረፍት ፣ ጊዜ ፣ በደስታ ፣ ያሳለፉት ፣ አልነበረም ። ሁለቱ ም ፣ ፈተናቸውን ፣ ተወጥተው ፣ ጎሩይ ፣ ቀጸላን ፣ እንደ ፣ እህት ፣ ጠብቆ ፣ መልሷታል ።

እርሱ ፣ ተመርቆ ፣ ሲወጣ ፣ እርሷ ፣ አስራ ፣ ሁለተኛ ፣ ክፍልን ፣ ጨርሳ ፣ የኮሌጁን ፣ መግቢያ ፣ ፈተና ፣ ስትወ ድቅ ፣ የሁለቱም ፣ ቤተሰቦች ፣ ወደ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ መጥ ተው ፣ ሠርጉ ፣ ተደገሰ ። የማይደርስ ፣ መስሏቸው ፣ ይህ ንን ፣ ዕለት ፣ ሁለቱም ፣ በናፍቆት ፣ ተቻኩለውበት ፣ ነበር። ዳሱ ፣ መተከል ፣ ሲጀምር ፣ ውጣ ፣ ውረዱ ፣ ግርግሩ ፣ ጣጣው ፣ ምንጣጣው ፣ ጎሩይን ፣ ይሰለቸው ፣ ጀመር ። የሠ ርጉ ፣ መባቻ ፣ ሌሊት ፣ ዕንቅልፍ ፣ አድብኖት ፣ ያደረውም ፣ ከድካም ፣ የተነሣ ፣ ነው ።

ሚዜዎቹ ፣ እርሱን ፣ እንደመከሩት ፣ ሁሉ ፣ ቀጸላ ንም ፣ ከወትሮው ፣ ተለውጣ ፣ አገኛት ። ማጋጌጥ ፣ ለማታ ዘውትረው ፣ ቀጸላ ፣ በወፍራሙ ፣ የተለሰነው ፣ የከንፈር ፣ ቀለም ፣ በልግስና ፣ የተነሰነሰው ፣ የፊት ፣ ዱቄት ፣ ቅባቱ ፣ ኩሉ ፣ ክሬሙ ፣ አልተስማማትም ። ጀማሪ ፣ የለቀለቀው ሥዕል ፣ አስመስሏታል ። « እግዜር ፣ ይይላችሁ ፣ እንጅ ፣ እንዲህ ፣ ትጫወቱባታላችሁ ፣ የኔን ፣ ቆንጂዬ !»ሲል ፣ በፌ ዝ ፣ ለመቆጣት ፣ ከጀለው ። ወደማድቤቱ ፣ ጐራ ፣ ብሎ ፣ «እማማ! ታዲያ ፣ ወጡንም ፣ ጠላውንም ፣ እንቅመሰውና ፣ አቃቂር ፣ እናውጣለት ፣ » ሲል ፣ ከቅርብ ፣ ጊዜ ፣ ወዲህ ፣ በጣም ፣ እየተላመዳቸው ፣ የሄደውን ፣ እናቷን ፣ ሊቃለድ ፣ አማረው ። ግን ፣ ሁሉም ፣ ኮስተር ፣ ብሏል ። ወጥ ፣ ሲሠራ፣ ያነጋ ፣ ቤተ ፣ ዘመድ ፣ እልልታውን ፣ እያቀለጠ ፣ ሲቀበላ

ቸውና ፡ ሲሸኛቸው ፡ እናትና ፡ አባት ፡ ግን ፡ ከመግቢያው ፡
ላይ ፡ እጃቸውን ፡ በኋሊት ፡ አቆላለፍው ፡ ቆመው ፡ እያዩ ፡
የማያዩዋቸው ፡ መሰሉ ። ይህ ፡ ሲያስገርመው ፡ « የኛ ፡
ሙሽራ ፡ የኛ ፡ ሙሽራ ፡ ኩሪባቸው ፡ በእንግሊዝ ፡ አናግሪ
ያቸው ፡ » የሚለው ፡ ዘፈን ፡ በሳቅ ፡ አፍኖት ፡ ነበር ።
ለእሱ ፡ ያስገረመውን ፡ ሌሎቹ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ አላ
ገኙትም ። እሱ ፡ ሰምቶት ፡ ስለማያውቅ ፡ በሳቅ ፡ የሚያ
ፍን ፡ የሆነበት ፡ « የሙሽሪት ፡ በእንግሊዝ ፡ መነጋገር ፡»
ዘፈን ፡ ለሌሎች ፡ በወጥ ፡ ላይ ፡ ጨው ፡ ከመጨመር ፡ የተለየ ፡
አስደናቂ ፡ አልሆነባቸውም ። ከሁሉም ፡ ይባስ ፡ ወደቤተ
ክርስቲያን ፡ ሲሄድ ፡ ጎሩይ ፡ ሊያጫውታት ፡ ቢሞክር ፡
እየተቅለሰለሰች ፡ አላነጋገረችውም ። ፈገግታዋም ፡ የጠ
ወለገ ፡ ነበር ።

በእርሱ ፡ ቤት ፡ እንደጅብ ፡ በውድቅት ፡ ሌሊት ፡
የጓደበ ፡ ቢመስለው ፡ ሌሎች ፡ ሙሽሮች ፡ ከነርሱ ፡ ቀድ
መው ፡ አገኘ ። ሙሽሮቹ ፡ ከመቅደሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ቅድስቱን ፡ አልፈው ፡ ከመቅደሱ ፡ ምኩራብ ፡ ላይ ፡ በተ
ርታ ፡ ተደርድረዋል ። አጃቢና ፡ሚዜ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡
ተገጥግጦ ፡ ቆሟል ። ካህናቱ ፡ ማኅሌት ፡ ጨርሰው ፡ ግማ
ሹ ፡ ተቀምጧል ። ግማሹ ፡ ጸሎተ ፡ ነግሁን ፡ ያደርሳል ፡
ንጽሕናው ፡ እምብዛም ፡ የማያስደስት ፡ አልባሳት ፡ ተደ
ርበው ፡ ከሌሎች ፡ ሙሽሮች ፡ ጐን ፡ ተቀመጡ ። ሥርዓተ ፡
ተክሊሉ ፡ ወዲያው ፡ አልተጀመረም ፡ ነበርና ፡ በደረቅ ፡
ሌሊት ፡ መጥተው ፡ መጠበቃቸው ፡ በልጅነቱ ፡ የፈጸመ
ውን ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ አስታወሰው ። ገና ፡ አራተኛ ፡
ክፍል ፡ ሳለ ፡ ለሚያዝያ ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ሰልፍ ፡ ትምሕርት ፡
ቤታቸው ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አባቱ ፡ ጫማና ፡ ልብስ ፡ ገዙና ፡
ሰጡት ። ልብሱ ፡ እምብዛም ፡ አላጓጓውም ። ጫማ ፡ ሲያ



ደርግ ፡ ግን ፡ የመጀመርያ ፡ ጊዜው ፡ ነበር ። ይህ ፡ የሆነው ፡
በዋዜማው ፡ ምሽት ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ እስኪነጋ ፡ ቸኩሎ ፡
ነግቶ ፡ የማይደርስበት ፡ መስሎት ፡ ጫማውን ፡ ሰክቶ ፡ አድሮ
ነበር ። « ይህም ፡ ዶሮ ፡ ሲጮህ ፡ መጥቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ማን
ጋት ፡ ከዚያ ፡ ጫማ ፡ ሰክቶ ፡ ከማደሩ ፡ የተለየ ፡ አይደ
ለም ፡ » አለ ፡ በሆዱ ።

ደብዘዝ ፡ ያለው ፡ ውጋገን ፡ በመስኮቱና ፡ በጣሪያው ፡
መስታወት ፡ መስረፅ ፡ ሲጀምር ፡ ካህኑ ፡ ጥና ፡ ይዘው ፡
መጽሐፍ ፡ በክንዳቸው ፡ ሸጉጠው ፡ አንድ ፡ መስቀል ፡
ሌላው ፡ ጧፍ ፡ በያዙ ፡ ሁለት ፡ዲያቆናት ፡ ታጅበው ፡
ገቡ ። ከዚያም ፡ በስመአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ አማትበው ፡ ባረኩና ፡ በግምጃ ፡ የተደ
ጐሰውን ፡ መጽሐፈ ፡ ተክሊል ፡ ከአትሮንሱ ፡ ላይ ፡ ገለጡ ።
ሁለት ፡ ሶስት ፡ ገጽ ፡ እንደደገሙ ፡ አንድ ፡ የትምህርት ፡
ቤት ፡ ደብተር ፡ ተዘርግቶ ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ እየተጠ
የቀ ፡ ይመዘገብ ፡ ጀመር ። ቀጸላ ፡ ተናገረች ። ጎሩይ ፡ ግን ፡
ረስቶታል ። እነቢተው ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ ጥያቄ ፡ መኖ
ሩን ፡ አላስጠኑትም ። ወላጆቹን ፡ በጠየቀ ፡ ነበር ። ለጊዜው ፡
ደንገጥ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ አገጩን ፡ አሻሽቶ ፡ አፉ ፡ እንዳመ
ጣለት ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ አለ ። ካህኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
በለሆሳስ ፡ ጸሎት ፡ ሲደግሙ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ጮኸው ፡ በግ
ዕዝ ፡ ሲያነቡ ፡ በአማርኛ ፡ ሲያነበንቡ ፡ ከዚያም ፡ ድንገት ፡
ዜማውን ፡ ሲያንቆረቁሩት ፡ ዲያቆናቱ ፡ ሲቀበሏቸው ፡
መስቀል ፡ የያዘው ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ዲያቆን ፡ በዜማው ፡
እየመራ ፡ ካህኑ ፡ እያጠኑ ፡ መቅደሱን ፡ ዞረው ፡ ሲመለሱ ፡
ሆነ ፡ ብሎ ፡ ለሚያዳምጠውና ፡ ለሚከታተለው ፡ ሥርዓተ ፡
ተክሊሉ ፡ የሚስለች ፡ አልነበረም ። እንዲያውም ፡ አንድ ፡
ዓይነት ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ውበት ፡ ነበረበት ። ጎሩይ ፡ ግን ፡

አስቀድሞ ፡ ሐሳቡን ፡ የተጫነው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ መሬዘም ፡ ነበርና ፡ ሳያዳምጠው ፡ ሳይከታተለው ፡ ሰለቸው ፡ በሥርዓቱ ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ በዚያ ፡ እንደሌለ ፡ ጆሮውንና ፡ ዓይኑን ፡ ደፍኖ ፡ በሐሳቡ ፡ የሚመላለሰው ፡ « ይህ ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል ? ነገር ፡ ቢበዛ ፡ በአሀያ ፡ አይጫንም ! » የሚል ፡ ነገር ፡ ነበር ። እንደ ፡ ማንቀላፋትም ፡ ቃጣው ።

በጎሩይ ፡ ስሜት ፡ በሰዓት ፡ ሳይሆን ፡ በዘመናት ፡ ከሚለካ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ቀለበቶቻቸው ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ተደርሶባቸው ፡ ከክብደቱ ፡ የተነሣ ፡ አንገት ፡ የሚሰብር ፡ አክሊል ፡ ተደፍቶላቸው ፡ ሁለቱም ፡ ከካህኑ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

« በኢትዮጵያ ፡ ተዋኅዶ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ባልሽ ፡ እንዲሆን ፡ ትፈቅጃለሽን ? » ስትባል ፡ ተጠየቀች ።

« እፈቅዳለሁ ። » ስትል ፡ መለሰች ።

« በኢትዮጵያ ፡ ተዋኅዶ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ሚስትህ ፡ እንድትሆን ፡ ትፈቅዳለህን ? »

« እፈቅዳለሁ ፡ » አለ ፡ ጎሩይ ፡ ሳያመነታ ።

« እረጀች ፡ ደከመች ፡ ብለህ ፡ ብታጣ ፡ ብትነጣ ፡ ላትተዋት ፡ » ብለው ፡ ውግዘቱን ፡ በመቀጠል ፡ « ዓይኗ ፡ ቢፈስ ፡ ክንድዋ ፡ ቢሰበር ፡ » ሲሉ ፡ ጎሩይ ፡ ስቅጥጥ ፡ አለው ።

« ምነዋ ፡ አባ ! ምነው ፡ ያሟርታሉ ፡ አባ ! እንዴ ! ለመመረቅ ፡ እንጅ ፡ እርግማን ፡ ለመስማትኮ ፡ አልመጣንም ፡ » ሲል ፡ በሆዱ ፡ ገሰጻቸው ።



ከዚያም ፡ እጃቸውን ፡ ደራርበው ፡ ሞት ፡ እስኪለያያቸው ፡ በሥጋም ፡ ሆነ ፡ በመንፈስ ፡ ላይለያዩ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ ገቡ ። ቀለበቱን ፡ ሰካላት ። ቀለበቱን ፡ ሰካችለት ።

« በቃ ፡ አይደል ? » ሲል ፡ ጎሩይ ፡ በሹክሹክታ ፡ ቢተውን ፡ ጠየቀው ። የሲጋራው ፡ ሱስ ፡ ተነሣበት ። ከመኪና ፡ ገብቶ ፡ እስኪለኩስ ፡ ተጣደፈ ።

« እ ሄ ! ሄ ! ገና ፡ ቅዳሴ ፡ መች ፡ ገቡና ! አስቀድሰን ፡ ነው ፡ የምንወጣው ፡ » ሲል ፡ አረዳው ። ሆን ፡ ብለው ፡ ያስከፉት ፡ ይመስል ፡ ጎሩይ ፡ ከንፈሩን ፡ ጣለ ። የሲጋራው ፡ ሱስ ፡ ሲያፋዘው ፡ በተጕናጸፈው ፡ መንጦላዕት ፡ ሙቀት ፡ ያች ፡ የምታንሰፈስፈው ፡ የጧት ፡ እንቅልፉ ፡ ታዳፋው ፡ ጀመር ። ሲታገል ፡ ስትጥለው ፡ ፊቱን ፡ በመዳፉ ፡ እየጠረገ ፡ ሲከላከል ፡ ስትሸፍነው ፡ ግማሽ ፡ ቅዳሴ ፡ ያህል ፡ ቀና ፡ ደፋ ፡ ሲል ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተሸነፈና ፡ የሕሊና ፡ ጸሎት ፡ የሚያደርስ ፡ ይመስል ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ይለጥጠው ፡ ገባ ። ለደጉ ፡ ሲተኛ ፡ አያንኮራፋም ።

ልዝብ ፡ ባለ ፡ ቁንጥጫ ፡ ከእንቅልፍ ፡ ዓለሙ ፡ ሲመለስ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ ሆነበት ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በሕዝብ ፡ ጥቂ ፡ ብሎ ፡ ሞልቷል ። ጸሎቱ ፡ ጨዋታው ፡ ያተማል ። ከአንዱ ፡ የመቅደስ ፡ በር ፡ በኩል ፡ ሴቶች ፡ ለጠበል ፡ ይሻማሉ ። አንዱ ፡ በሌላው ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ተንጠላጥሎ ፡ አንዱ ፡ ሌሎችን ፡ ገፍቶና ፡ ሰርስሮ ፡ ለማለፍ ፡ ሲታገል ፡ አንድዋን ፡ ብርጭቆ ፡ ሃያና ፡ ሰላሣ ፡ እጅ ፡ በአንዴ ፡ ሲናጠቃት ፡ ጎሩይን ፡ እንስራ ፡ የሚሰበርበትን ፡ ሴቶች ፡ ጸጉር ፡ የሚናጩበትን ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ወረፋ ፡ አስታወሰው ። ረፈድ ፡ ብሎ ፡ የጧቷ ፡ ጮራ ፡ በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ ገብታ ፡ ነበር ። ደህና ፡ እንቅልፉን ፡ ጨርሶ ፡

ነበርና ፡ ነቃ ፡ አለ ። ከዚያም ፡ እንደገና ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ተደርሶ ፡ መስቀል ፡ ተሳልመው ፡ ወጡ ።

« ይባርክላችሁ ። ዘራችሁን ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት እንደባሕር ፡ አሸዋ ፡ ያብዛው ። ቤታችሁ ፡ እንደአብርሃም ቤት ፡ ይትረፍረፍ ። እንግዲህ ፡ መቸም ፡ አባታችሁን ፡ አለመርሳት ፡ ነው ፡ » አሉ ፡ ካህኑ ፡ ከጐኑ ፡ እየተራመዱ ።

« ኧረ ፡ አንረሳም ፡ አባ ። ቤቱኳ ፡ አያሳስትም ፡ ነበር ። ግን ፡ ለሁሉም ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ እንልክልዎታለን ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በአባትነትዎ ፡ መጠያየቁ ፡ ደግሞ ፡ የርስዎ ፡ ፈንታ ፡ ነው » አለና ፡ ቢተው ፡ አሰናበታቸው ። ጎሩይ ፡ ነገሩ ፡ ስላልገባው ፡ በጥያቄ ፡ መልክ ፡ ዓይኖቹን ፡ አፈ ጠጠ ።

« የንስሐ ፡ አባትህ ፡ ናቸው ፡ » አለው ፡ ቢተው ።
« ማን ፡ አለ ? »

« እየሰማህ ። ለጊዜው ፡ የፈለጉት ፡ ጉርሻ ፡ ነበር ። እኔ ፡ ግን ፡ ነገሯን ፡ አዞሬ ፡ መለስኳቸው ። እንግዲህ ፡ ጠበል ፡ ሊረጩ ፡ ቀጤማ ፡ ሊሰጡ ፡ ለልጆቻቸው ፡ የእግ ዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሊያሰሙ ፡ ሲመጡ ፡ መቀበል ፡ ነው »

ጎሩይ ፡ በመገረም ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀ ። ይበልጥ ፡ ያስ ገረመው ፡ ደግሞ ፡ የቀጸላ ፡ ዝምታ ፡ ነው ። ቢተውና ፡ እርሱ ፡ ሲነጋገሩ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኗን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ እንደዋዛ ፡ እያመላለሰች ፡ ከመመልከት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አልወጣትም ።

ከነቀጸላ ፡ ቤት ፡ ቁርስ ፡ በልተው ፡ ሙሽሪትን ትተው ፡ ሲወጡ ፡ « መቅረቷ ፡ ነው ፡ እንዴ ? » ሲል ፡ ጠየቀ ።



« እኮ ፡ አትጣደፍ ! በኋላ ፡ መጥተን ፡ እንወስዳታ ለን ። ጫጉላ ፡ ቤቱ ፡ መቸም ፡ ማታ ፡ ነው ፡ » ብሎ ፡ ቢተ ው ፡ አሾፈበት ።

« እንዲያው ፡ ዋና ፡ የነገር ፡ ቋት ፡ ወጣህ ። እኔ ፡ የጠየቅሁት ፡ ለቀልድ ፡ ያህል ፡ ሥርዓቱ ፡ ከዚሁ ፡ ላይ ፡ ቢበቃ ፡ ምን ፡ ነበረበት ፡ ለማለት ፡ ያህል ፡ ነበር ። »

« ለቀልድህም ፡ ሆነ ፡ ለቁም ፡ ነገርህ ፡ ላንተ ፡ ሲባል ፡ ያገር ፡ ወግ ፡ አይሻርም ፡ » አለው ።

ወደቤቱ ፡ ሄዶ ፡ አጃቢዎቹና ፡ ሚዜዎቹ ፡ በየቦታው ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ ሲሉና ፡ ሲጫወቱ ! ወደ ፡ መኝታ ፡ ክፍሉ ፡ ገብቶ ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ እንዲያርፍ ፡ ተፈቀደለት ። ግን ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደውም ፡ ሆነ ፡ መንፈሱ ፡ ሊያርፍ ፡ አልቻለም ።

ከዚያም ፡ የሌሊቱ ፡ ሽርጉድ ፡ እንደገና ፡ ቀጠለ ። እንደገና ፡ ፊቱን ፡ አስታጠቡት ። እንደገና ፡ በቅባት ፡ ታሸ ። ጸጉሩን ፡ አበጠረ ። አሁንም ፡ እንደገና ፡ ከበው ፡ ከጫማው ፡ ጫፍ ፡ እስከ ፡ ጸጉሩ ፡ ቁንጮ ፡ አስተካከሉት ። በጸጉሩ ፡ አበጣጠር ፡ ላይ ፡ አስቸኳይ ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። አንደኛው ፡ በራው ፡ በሽምግልና ፡ እንዳያሳጣ ፡ ወደፊት ፡ ያበጥረው ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ ። ፊቱ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ኩርፋድ ፡ ያስመስለዋል ፡ በማለት ፡ ሌላው ፡ ተቃወመ ። ወደ ፡ ጐንስ ? የለም ! ይኸማ ፡ ያራዳ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ መቅረብ ፡ ነው ። የእያንዳንዱን ፡ ሐሳብ ፡ እየ ምከሩ ፡ ሲማከሩበትና ፡ ሲከራከሩበት ፡ በመጨረሻ ፡ ትዕግሥቱ ፡ አለቀበትና ፡ ንዴቱ ፡ ሲገንፍል ፡ ሳት ፡ ጐርሶ ፡ ሳት ፡ ለብሶ ፡ እየተወራጨ ፡ ከክፍሉ ፡ አባረራቸው ። ዘወ

ትር ፡ እንደሚያደርገው ፡ በጸጉሩ ፡ መካከል ፡ ማበጠሬ
ውን ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ አስኪዶ ፡ ሲወጣ ፡ ቢወዱም
ቢጠሉም ፡ ሁሉም ፡ ተስማምተው ፡ ተቀበሉት ።

« መጥፎ ፡ አይደለም ! » አለ ፡ አንዱ ፡

« ግዴላችሁም ፡ አያሳጣንም ፡ » ሲል ፡ ቢተው ፡ ሁ
ንም ፡ አጽናናቸው ።

የቀጸላ ፡ ቤት ፡ ሠርግ ፡ ከጠላው ፡ ከጠጁ ፡ ከእን
ራው ፡ ከወጡ ፡ ከጮማው ፡ ከአስተነባበሩ ፡ ምንም ፡ እ
ከን ፡ የማይወጣለት ፡ ሞቅ ፡ ደመቅ ፡ ጠፈፍ ፡ ያለ ፡ ነበር
ጎሩይም ፡ ከሴት ፡ ሚዜዎቹ ፡ ጋር ፡ ተለማምዶ ፡ በጨዋ
ታና ፡ በቀልድ ፡ የቀጸላን ፡ ከንፈር ፡ በፈገግታ ፡ ለማስ
ለጥ ፡ በቅቶ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ « ለምን ፡ አትበ
ላም ፡ » ስትል ፡ በሹክሹክታ ፡ ጋበዘችው ። እርሷን ፡
ለማስደሰት ፡ እርሷን ፡ ያስደሰተ ፡ መስሎት ፡ ክትፎውን ፡
አልጫውን ፡ ዝግኑን ፡ የወጣለትን ፡ ሁሉ ፡ እየዘገነ ፡
ይሰለቅጠው ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ከዊስኪው ፡ ሲጐነጭለት ፡
ሰውነቱ ፡ እየተዘናናለት ፡ ሂዶ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ ሴቶች ፡
ሚዜዎችና ፡ የቤት ፡ ልጆች ፡ ወጡን ፡ ቅንጩውን ፡ ዶሮ ፡
ዳቦውን ፡ ቆጮውን ፡ ክትፎውን ፡ ጥብሱን ፡ በሰሐን ፡
እያዞሩ ፡ ሲጋብዙ ፡ የፊታውራሪ ፡ ዘመድ ፡ ግራዝማች ፡
አየኔ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥጋ ፡ ቤት ፡ የመጣ ፡ በሚ
መስል ፡ ያወለወለ ፡ ወጠምሻ ፡ አስቆራጭ ፤ ሽንጡን ፡
ይዘው ፡ ቀረቡ ።

የግራ ፡ እጃቸውን ፡ ከሥር ፡ ደገፍ ፡ አድርገው ፡ እን
ደማስጐምዠት ፡ ያህል ፡ በቢላ ፡ ጮማውን ፡ እየጠበጠቡ ፡
« የት ፡ ላይ ፡ ይሻልሃል ? » ሲሉ ፡ ጎሩይን ፡ ጠየቁት ።



ቀና ፡ ብሎ ፡ አየና ፡ አንገቱን ፡ ቀልበስ ፡ አድርጎ ፡ « እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ » አላቸው ።

« ኤዲያልኝ ፡ የአሰበ ፡ ተፈሪ ፡ ድልብ ። እንዲህ ፡ ያለም ፡ ከብት ፡ አላየሁ ። መቸም ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ ሥጋ ፡ አታውቁም ። እኔው ፡ ልምረጥልህ ። እያት ! ይች ፡ ካፍ ፡ ላይ ፡ እንደቅቤ ፡ ሙክክ ፡ የምትል ፡ ሽንኩርት ፡ ናት ፡ » ብለው ፡ ቢላዋቸውን ፡ በሙዳው ፡ ላይ ፡ ሰነዘሩ ።

« የለም ! የለም ፡ እኔ ፡ በቃኝ ፡ » አለ ፡ ጎሩይ ፡ እንደ መከላከል ፡ ዓይነት ፡ መዳፉን ፡ ወደፊት ፡ ዘርግቶ ።

« ነውና ፡ ልጄ ! ሥጋ ፡ የሚበላው ፡ ሌላው ፡ ከበቃና ፡ ከተጠገበ ፡ በኋላ፡ ነው ፡ » እንደ ፡ ክቡርና ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ በጥንቃቄ ፡ ቆርጠው ፡ ታላቅ ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ዕቃ ፡ እንደሚያበረክት ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ አሳምረው ፡ ይዘው አቀረቡለት ።

« የለም ፡ ይኸኛው ፡ ይሻለኛል ፡ » አለ ፡ ጎሩይ ፡ በሳሕኑ ፡ ላይ ፡ የተቆለለውን ፡ ምግብ ፡ አያሳየ ።

« እንዴ ! መጀመርያ ፡ ሳትቀምሰው ! ሥጋ ፡ ብሎ ፡ ዝም ፡ ነው ፡ »

« የለም ፡ ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ አልበላም ፡ » አለ ፡ ጎሩይ ።
« ምነዋ ? እርምህ ፡ ነው ፡ እንዴ ? » ሲሉ ፡ ጠየቁ ፤
« ኧረ ፡ አይደለም ! » ሲል ፡ እንደሳቅ ፡ ቃጣው ።
« እህሳ ? »

« እንዲሁ ፡ ለኮሶው ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ » ብሎ ፡ እንደዋዛ ፡ ንግግሩን ፡ ሳይጨርስ ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በድንገት ፡ ተደባለቀ ።

« ዘራፍ ! የዳኘው ፡ አሽከር ፡ ! » ሲሉ ፡ ግራዝማች
የጨበጡትን ፡ ቢላዋ ፡ ሲወረውሩት ፡ በእምላክ ፡ ቸርነት
ሰው ፡ ስቶ ፡ እንዱን ፡ ብርጭቆ ፡ ቢለጋው ፡ የአንድዋ
ሚዜ ፡ ልብስ ፡ በጠላ ፡ ተነከረ ። በዳሱ ፡ ውስጥ ፡ የነበረወ
ጫጫታና ፡ ሁካታ ፡ እፍ ፡ እንደተባለ ፡ መብራት ፡ አንድ
ጊዜ ፡ እርጭ ፡ ድብን ፡ አለ ። አሳላፊዎችና ፡ አስተናባ
ዎች ፡ ክንዳቸውን ፡ ለማጠፍ ፡ አፉቸውን ፡ ለመዝጋት
ስንኳ ፡ ፋታ ፡ አጥተው ፡ የያዙትን ፡ ዕቃ ፡ አንቀርፍፈው
እንደተገተሩ ፡ ቀሩ ። ከውጭ ፡ ብቻ ፡ ዜናው ፡ ገና ፡ ያ
ደረሳቸው ፡ የመንደር ፡ ሴቶችና ፡ ጐልማሶች ፡ « እን
ላይሽ ፡ እንዳላይሽ ፡ ደመና ፡ አንግቧል ፡ በላይሽ ፡ » እያሉ
ሲዘፍኑ ፡ ከአታሞው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ይሰማል ። ጎሩይ
መብረቅ ፡ እንደመታው ፡ ክው ፡ አለ ።

ግራዝማች ፡ ወባ ፡ እንደተነሳበት ፡ መላ ፡ ሰውነታ
ቸው ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ እንደመወራጨት ፡ እየቃጣቸው
እንደገናም ፡ አካኪ ፡ ዘራፍ ፡ ለማለት ፡ ከጅለው ፡ «ምነዋ
ልጄ ! እንዲህ ፡ ጉድ ፡ አረከኝ ! » ሲሉ ፡ በአዘኔታ ፡ ራሳ
ቸውን ፡ ነቅንቀው ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገቡ ። ከዚያም ፡ በዳሱ ፡
ውስጥ ፡ ድንገት ፡ የባረቀው ፡ ድንጋጤ ፡ እየተረጋጋ ፡ ሄዶ ፡
ግብዣው ፡ ጨዋታው ፡ ቢቀጥልም ፡ እንደበፊቱ ፡ ሲሟ
ሟቅ ፡ አልቻለም ። አስተናባሪዎቹ ፡ ድንገት ፡ ከወደ
ኋላቸው ፡ ጅራት ፡ እንደበቀለባቸው ፡ በኃፍረት ፡ ተሽማ
ቅቀው ፡ ሲጋብዙ ፡ ዕድምተኞቹ ፡ የመምሕር ፡ ቁጣ ፡ እን
ደፈራ ፡ ተማሪ ፡ ባለሆሳስ ፡ ሲንሾካሾኩ ፡ ያ ፡ ከጥቂት ፡
ደቂቃዎች ፡ በፊት ፡ ደምቆ ፡ የነበረው ፡ ዳስ ፡ ቀዝቀዝ ፡
አለ ። ሙዚዎቹም ፡ ተነስተው ፡ መጨፈር ፡ እንዳለባ
ቸው ፡ ረስተው ፡ ተውት ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ጎሩይ ፡
ከሌሎች ፡ የባሰ ፡ ዙሮበት ፡ ነበር ። ድንጋጤ ፡ አይደለም ።



ኃፍረትም ፡ አይደለም ። አእምሮው ፡ እንዲሁ ፡ ድንገት ፡
ቦዘበት ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ቶሎ ፡ ለመገላገል ፡ እንደፈ
ለጉ ፡ ያህል ፡ ኬኩ ፡ ተቆርሶ ፡ የሻምፓኝ ፡ ፅዋ ፡ ተነስቶ ፡
ለመሰናበት ፡ ሲጠይቁ ፡ እንደወጉ ፡ « ቆዩ ፡ እንጅ ፡ ተጫ
ወቱ ! » ሳይባሉ ፡ ወዲያው ፡ ተፈቀደላቸው ።

ከመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ወንበር ፡ ተደረደረና ፡ አባ
ትና ፡ እናት ፡ አክስት ፡ አጎት ፡ አሮጊት ፡ ገረድ ፡ ሳይቀሩ ፡
ቤተ ፡ ሰብ ፡ በሙሉ ፡ በተርታ ፡ ተቀመጡ ። ሚዜዎቹ ፡
እየመሩ ፡ ሙሽሮቹ ፡ ተነሱ ። ተጋባዥ ፡ ተነሣ ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ለመሰናበት ፡ ከተቀመጡት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ብዙ
ዎቹ ፡ ሴቶች ፡ ዓይናቸውን ፡ በመሐረምና ፡ በኩታቸው ፡
ጫፍ ፡ ሲጠራርጉ ፡ ቀጸላ ፡ ከእናቷ ፡ ጉልበት ፡ ላይ ፡ ተደ
ፍታ ፡ ትንሽ ፡ ተንፈቀፈቀች ። ቀጥላም ፡ አባቷንና ፡ የቀሩ
ትን ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ጉልበት ፡ ትስም ፡ ገባች ። ጎሩይ ፡
ከኋላዋ ፡ ተገትሮ ፡ ዓይነ ፡ ልቦናው ፡ ሳያስተውል ፡ አፍ
ጥጦ ፡ ያያታል ።

« አንተም ፡ ጉልበት ፡ ሳም ፡ » ሲል ፡ ቢተው ፡ በጆ
ሮው ፡ ነገረው ።

ጎሩይ ፡ አልተንቀሳቀሰም ።

« አትሰማም ? አትስምም ፡ እንዴ ? » ሲል ፡ በሹክ
ሹክታ ፡ ተቆጣው ። ጥቂት ፡ እንደመባነን ፡ ብሎ ፡ ሳይነቃ ፡
በከፊል ፡ ደመነፍስ ፡ አጎንብሶ ፡ ጉንጩን ፡ እያገላበጠ ፡
ሰጠ ።

ከበሩ ፡ ሲወጡ ፡ የመጀመርያው ፡ የሽቶ ፡ ርከፍካፊ ፡
ያመለጣቸው ፡ ጥቂቶች ፡ የመንደር ፡ ሴቶች ፡ አንድ ፡ ክበሮ
ከበው ።

«የኛ ፡ ሙሽራ ፡ ነሽ ፡ ወይ ፡ ሌላ ፤

አንቺ ፡ ልጅ ፡ ከረሜላ ፡ » እያሉ ፡ የወጋችን ፡ ሳይ
ጠን ፡ እናሳልፍም ፡ ለማለት ፡ ሲሞክሩ ፡ በወናፍ ፡ የተ
ላውን ፡ አዱ ፡ ኮሎኛ ፡ ረጫጭተውባቸው ፡ አለፉ ።

ከዚያም ፡ አጃቢው ፡ አውቶሞቢል ፡ ተቀሰቅሶ
ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ ወጥቶ ፡ ሲጋራውን ፡ ለኩሶ
በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ የሚገባው ፡ የነፋስ ፡ ሽውታ ፡ ላቡን
ሲመጥለትና ፡ ወበቁን ፡ ሲያቀዘቅዝለት ፡ ጎሩይ ፡ ሰውነቱ
እየተመለሰለት ፡ ሄደ ። « ጉልበት ፡ መሳም ፡ መኖሩን
ለምን ፡ አልነገራችሁኝም ፡ ታዲያ ? » ሲል ፡ ጠየቀ
ቀጸላ ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ዕንባዋን ፡ ትጠራርግ ፡ ነበር ።

« የፕላን ፡ መለዋወጥ ፡ ነው ። እኛ ፡ ያሰብነው ፡ እጅ
ነስታችሁ ፡ ብቻ ፡ ትወጣላችሁ ፡ ነበር ። የቀጸላ ፡ ስሕተት
ነው ፡ » ቢተው ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ተመለከታትና ፡ « ወግ
ነው ፡ ሲዳሩ ፡ ማልቀስ ። እንግዲህ ፡ ታዲያ ፡ አይበቃሽም
እንዴ ? » ሲል ፡ እንደማፌዝ ፡ ዓይነት ፡ ፈገግ ፡ አለ
«ደግሞ ፡ እኒያ ፡ አጎትሽ ፡ ጉድ ፡ አፈሉኮ ። ልብሷ ፡ ምንም
አልተረፈ ። »

« ምን ፡ ነካቸው ፡ በል ? » ሲል ፡ ጎሩይ ፡ ጠየቀ ።
« ፊታቸው ፡ እንዴት ፡ እንደተለዋወጠ ፡ አይተሀል
ኛል ? » አለ ፡ ቢተው ፡ ጥያቄውን ፡ ሳይመልስለት ።

« ብራቅ ፡ እንደመታው ፡ ነፍስና ፡ ሥጋየ ፡ ሲለያይ
ምኑን ፡ አየኋቸው ? » ትዝታው ፡ ብቻ ፡ ሰቅጥጥ ፡ አለው

« አፍረውኮ ፡ ለመሰናበትም ፡ ሳይመጡ ፡ ቀሩ ። እረ
ለመሆኑ ፡ ዛር ፡ ነው ፡ የባርያ ፡ በሽታ ፡ አለባቸው ? » ሲል



ቀጸላን ፡ ጠየቀና ፡ መለሰ ፡ አድርጎ ፡ « ይቅርታሽን ፡ ስቀ
ልድ ፡ ነው ፡ » አለ ።

«የምርህንስ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ያስቀይመኛል ? ነገሩን ፡
ለማያውቅና ፡ ሁናቴያቸውን ፡ እንደዚህ ፡ በድንገት ፡
ለሚያይ ፡ ጤነኛ ፡ ናቸው ፡ አያሰኝም ፡ » ስትል ፡ መለሰ
ችለት ። አሁን ፡ ልቅሶዋን ፡ አቁማ ፡ ነበር ።

« ነገሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ? »
« የኮሶ ፡ ስም ፡ ሲጠራባቸው ፡ አይወዱም ፡ »

« ዘስሙ ፡ መጠራት ፡ እንዲህ ፡ የወገሹ ፡ ራሱ ፡ ሲመ
ጣባቸው ፡ እንዴት ፡ ሊሆኑ ፡ ነው ! » ቢተው ፡ ሳቅ ፡ እንዳ
ፈነው ፡ ሰው ፡ አፉን ፡ በጁ ፡ ከደነ ።

« ያስቃል ። ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እያስ
ቅም ። በሰው ፡ መካከል ፡ ድንገት ፡ እንዲህ ፡ ሲሰቃዩ ፡
ያሳዝኑኛል ። ዛሬ ፡ ሲሰቶዲን ፡ እስታኖክሲልና ፡ ዮሜሳን
መጥቶ ፡ ገላገላቸው ፡ እንጅ ፡ ቀድሞማ ፡ ኮሶው ፡ በዋንጫ
ተበጥብጦ ፡ ሲቀርብላቸው ፡ የሚቀበሉት ፡ ሠራዊት ፡
አስልፈው ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ ዋንጫውን ፡ ጨብጠው ፡
እየተንጐራደዱ ፡ ከሰገሌ ፡ እስከማይጨው ፡ የሠሩትን ፡
ጀብዱ ፡ ከፎከሩ ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ አሽከር ፡ ጥይት ፡ ተኩሶ ፡
መድኃኒቱን ፡ ይከነብሉታል ። ይህንን ፡ ጠባያቸውን ፡
አገሬው ፡ ሁሉ ፡ አውቆላቸው ፡ ሁሉም ፡ ይጠነቀቅላቸዋል»
አለችና ፡ የተቆጠበ ፡ ፈገግታ ፡ አሳየች ።

« አሆ ! ታዲያ ፡ እኝህን ፡ ከኋላቸው ፡ የኮሶ ፡ ስም ፡
እየጠሩ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ቢያዘምቷቸው ፡ ከፊታቸው ፡ የሚ
ቆም ፡ ጠላት ፡ አይኖርም ፡ » ሲል ፡ ቢተው ፡ ሁሉም ፡
ተሳሳቁ ።

በፒያሳ ፡ ተንሸራሽረው ፡ ዑደት ፡ አድርገው ፡ ጎሩ
«እረ ፡ እባካችሁ ፡ ትራፊክ ፡ አታውኩ ፡ የምን ፡ ቂ
ሊባል ፡ ነው ፡ » ሲል ፡ በተከለከለው ፡ የቸርችል ፡ ጐዳና
ወርደው ፡ በመውረጃው ፡ ፍራሽ ፡ ተራ ፡ ወጥተው ፡ የ
ጦጠው ፡ ኢሳማ ፡ ተኩስና ፡ ቀላል ፡ የሚካ ፡ ድግስ ፡ ደህና
ተፈጸመ ።

የርሱም ፡ ቤተሰብ ፡ ሠርግ ፡ የወጣለት ፡ ነበር ። አባ
ያኔ ፡ ሽማግሌ ፡ ሲላክ ፡ የተናቁበትን ፡ ቂም ፡ እንደ ፡ ቋጠ
ኖሮ ፡ « ማ ፡ ከማን ፡ ያንሳል ! እንተያያለን ፡ » በሚል
ስሜት ፡ ከዳሱ ፡ ስፋት ፡ አንስቶ ፡ ድግሱን ፡ በገፍ ፡ አድ
ገውት ፡ ነበር ። የፌታውራሪ ፡ ሰንጋ ፡ ከሐረር ፡ ቢመጣ
የርሳቸውም ፡ የአሩሲ ፡ ድልብ ፡ ነው ። ከባልንጀሮቹ
ከሚያውቃቸውም ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳያስቀር
ነገረውታል ። እርሳቸውም ፡ በጐጃሜ ፡ ተወላጅነትና
በጐሬ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚያውቋቸውንና ፡ የማያ
ቋቸውን ፡ ታላላቅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠርተዋል ። የመ
ደርም ፡ ቢሆኑ ፡ ዘፋኞች ፡ ተከራይተው ፡ ነበር ።

ሙሽሮቹ ፡ ወደዳሱ ፡ ሲገቡ ፡ አባቱ ፡ ካለርሳቸው
ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንዳልወለደ ፡ ካለርሳቸው ፡ አስተምሮ
ለዓቅመ ፡ አዳም ፡ አድርሶ ፡ እንዳልዳረ ፡ ካለርሳቸው
ልጅ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንደሌለ ፡ ክንዶ
ቻቸውን ፡ ከደረታቸው ፡ ላይ ፡ አመሳቅለው ፡ ፊታቸው
በደስታና ፡ በኩራት ፡ ፈክቶ ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ተቀበሉዋ
ቸው ። ከዚያም ፡ ራሳቸው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ « ጌቶቼ
ምነዋ ፡ ተጋበዙልኝ ፡ እንጂ ፡ » እያሉ ፡ ጮማ ፡ ሲቆረጥ
ጠጅ ፡ እንደውሃ ፡ ሲፈስስ ፡ ሻምፓኝ ፡ እምብሽብሹ
ሲወጣ ፡ እንደዋዛ ፡ አሜውተውትና ፡ ተቃልደው ፡ ባያው



ቅም ፡ የአባቱ ፡ ፍቅር ፡ የጠለቀ ፡ መሆኑ ፡ ለጎሩይ ፡ ተሰ
ማው ።

ጭፈሮው ፡ ዘፈኑ ፡ እስከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሲቀልጥ ፡
አመሸ ። ወደሰባት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ እንግዳ ፡ ተጋባዥ ፡
ተሸኝቶ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ጐረቤት ፤ አጃቢና ፡ ጓደኛ ፡ ብቻ ፡
ቀረ ። ሙሽሮቹ ፡ ድካሙም ፡ እንቅልፉም ፡ እያፈዘዛቸው ፡
ሄዶ ፡ ነበር ። ጎሩይማ ፡ ወደመሰላቸቱ ፡ ተቃርቦ ፡ ነበር ።
የምን ፡ መንዛዛት ፡ ነው ? ለምንስ ፡ ሥቃይ ፡ መሆን ፡ አለ
በት ? ሲል ፡ በሐሳቡ ፡ ደጋግሞ ፡ ተራግሟል ።

ዘፈኑና ፡ ጭፈሮው ፡ ደመቅመቅ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡
ቢተው ፡ መጣና ፡ ሚጉላ ፡ ቤት ፡ መሰናዳቱን ፡ ነገረው ።
ገና ፡ በሚጠብቀው ፡ ረፍት ፡ ጐምጅቶ ፡ እፎይ ! አለ ፡
ጎሩይ ፡ በሆዱ ። ተመርተው ፡ ገቡ ። ቀጸላ ፡ አልጋውን ፡
የፈራች ፡ ይመስል ፡ ከፎቴ ፡ ላይ ፡ ተንቆራጣ ፡ ተቀመጠች።

ቢተው ፡ ጎሩይን ፡ ወደበራፉ ፡ ሳብ ፡ አድርጎ ፡ «እኩል ፡
ሰዓት ፡ እንሰጥሃለን ፡ » ሲል ፡ በጆሮው ፡ ነገረው ።

« የምን ፡ እኩል ፡ ሰዓት ? »

ቢተው ፡ በሽሙጥ ፡ ከንፈሩን ፡ አጣሞ ፡ ተመለከ
ተው ፡ « ምን ፡ ብዬ ፡ እንድነግርህ ፡ ትፈልጋለህ ? የሚ
ጉላ ፡ ቤቱን ፡ ወግ ፡ ለመፈጸም ፡ ነዋ ! »

ጎሩይ ፡ ከፊቱኑ ፡ የጠየቀው ፡ ጉዳዩን ፡ አጥቶት ፡ አል
ነበረም ። ሆኖም ፡ ቢተው ፡ ደፍሮ ፡ ሲነግረው ፡ ቱግ ፡
አለበት ። « ወግ ! ወግ ! ለንስሐ ፡ ሞት ፡ ለቀብር ፡ ወግ ፡
እያብቃህና ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ሚስቴን ፡ የምታቃጥረኝ ? »
ቀጸላ ፡ ነገሩን ፡ እንዳትሰማ ፡ ጎሩይ ፡ ወደውጭ ፡ ወጣ ።

« ከኔው ፡ ጋር ፡ ኑሯለች ። ከኔው ፡ ጋር ፡ ትኖራለች ። አታመልጠኝ ። ነገ ፡ ምፅዓት ፡ አይደለም ። በፈጠረህ ፡ ጥቂት ፡ አታፍርም ? » በመደነቅ ፡ ራሱን ፡ አወዛወዘ ። « እኔ ፡ እንዲህ ፡ ደክሞኝ ፡ ሳለ ፡ እርሷም ፡ እንዲህ ፡ ታውካ ፡ ሳለ ፡ እኔን ፡ አውሬ ፡ ማድረግህ ፡ ነው ? ወይስ ፡ ርሷን ፡ እንደ ሰው ፡ አልቆጠርካትም ? » ሲል ፡ ተቆጣ ።

« አውቃለሁ ፡ ይገባኛል ፡ » ቢተው ፡ ሊያባብለው ፡ ሞከረ ። « እንደናንተማ ፡ ቢሆን ፡ ቀስ ፡ ብላችሁ ፡ ትደርሱበት ፡ ነበር ። ስለግብረ ፡ ሥጋ ፡ ከፈረንጅ ፡ መጽሐፍ ፡ ያነበብከውን ፡ ከዚህ ፡ ርሳው ። ሠርጉ ፡ የሁለታችሁ ፡ ጋብቻ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የማኅበር ፡ ሥርዓት ፡ ጭምር ፡ ነው ። ከዳሱ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚጠባበቀው ፡ አንተ ስታንኰራፋ ፡ ለመስማት ፡ አይደለም ። »

« የራሳቸው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ! » ሲል ፡ ደነፋ ።

« የአንተም ፡ ነው ። ለአባትና ፡ ለእናትህ ፡ ስሜት ፡ ስንኳ ፡ ታስብም ? እንዴት ፡ ሲሆኑ ፡ እንደዋሉ ፡ አስብ ። ሰማይ ፡ ነው ፡ የሚደፋባቸው ። »

ጎሩይ ፡ ግዴለኝም ፡ በሚል ፡ ሁናቴ ፡ ትከሻውን ፡ ነቀነቀ ።

« ለዚህ ፡ ወግ ፡ ማዕረግ ፡ ላበቁህ ፡ ወላጆች ፡ እስከዚህ ፡ ደንታ ፡ ቢስ ፡ ትሆናለህ ፡ ብዬ ፡ አላስብም ፡ ነበር። ሁለታችሁ ፡ የምትጠራጠሩት ፡ ነገር ፡ ካለ ፡ ግን ፡ እንደፈረደብኝ ፡ ታፋዬን ፡ እበጣለሁ ፡ » አለው ፡ ቢተው ።

« መብረቅ ፡ ይብጣህና ፡ ጥፋ ፡ ከፊቴ ! » ብሎ ፡ ጎሩይ፡ ሙሽና ፡ ወደክፍሉ ፡ ተመለሰ ። በሸቀ ። አረረ ። ተከነ ። ቢተው ፡ እውነቱን ፡ ነው ። እዬ ! እነርሱማ ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡



ጨርሰውት ! ተብሎ ፡ ይወራል ። ወላጆቹም ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እርማቸውን ፡ ያወጣሉ ። ወግ ፡ ነው ፡ ውጋት ? መጥኔ ፡ ወግ ! ቢተው ፡ ኮርባዜር ፡ ኮኛክ ፡ ከሁለት ፡ ብር ጭቆ ፡ ጋር ፡ ይዞ ፡ መጣና ፡ « ያስፈልጋችሁ ፡ እንደሁ ፡» ሲል ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ወጣ ። እንደረታው ፡ አውቋል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ቀጸላ ፡ እንገቷን ፡ እንደ ፡ ደፋች ፡ ነበር ። የተባባሉትን ፡ ባትሰማም ፡ ነገሩን ፡ ጠርጥራለች ። ጎሩይ ፡ ቀድቶ ፡ አቀረበላትና ፡ ለራሱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አከታትሎ ፡ ለጋ ። አጋለው ። መሆኑም ፡ ካልቀረ ፡ ሰውነቱም፡ ሞቀ ።

« ምን ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ያቅለሰልሰሻል ! ያንቺው ፡ አልባሰም ! » ሲል ፡ ደነፋና ፡ ጐትቶ ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ወረወራት ። አልተነፈሰችም ። በፍርሃት ፡ ዓይኗ ፡ ብቻ ፡ ፈጦ ፡ ነበር ። መብራቱን ፡ አጠፋ ። ዓይኑን ፡ ጨፈነ ። አማልክት ፡ ድፍረት ፡ ስጡኝ ! በጨኸት ፡ ጣሪያውን ፡ ስታደባልቀው ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ተፈናጥሮ ፡ ተነሣ ። እጁ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ሱሪውን ፡ ታጥቆ ፡ መብራቱን ፡ ለኰሰ ። ተዘርራለች ። ቀና ፡ ሊያደርጋት ፡ ሞከረ ። ዝልፍልፍ ፡ አለች ። በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ወጣና ፡ « ያውላችሁ ! ሞተችላችሁ ! » አለ ፡ ዕንባ ፡ እየተናነቀው ። በቅጽበት ፡ ዕልልታው ፡ ቀለጠ ። ጭፋሮው ፡ ድብልቅልቁ ፡ ወጣ ።

« ብር ፡ አምባር ፡ ሰበርልዎ ፡
ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልዎ ፡
ወንዱ ፡ ልጅዎ !
ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልዎ ፡
ጎሩይ ፡ ልጅዎ !»

ምኑ ፡ ያስጨፍራል ? — በመገረም ፡ ከቆመበት ፡ ፈዞ ፡ ቀረ ።

# በሌጣ ፡ አህያ ፤

አዝማች ፡ አስገዶም ፡ የሰንበት ፡ ለታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀድሰው ፡ ወደቤታቸው ፡ ይመለሳሉ ። ልጃቸው ፡ ዘርአይ ፡ በጉልማሳነታቸው ፡ ላጼ ፡ ዮሐንስ ፡ አድረው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የተሸለሙትን ፡ አሮጌ ፡ ሰናዲር ፡ አንግቦና ፡ ዳዊታቸውን ፡ አንግቶ ፡ ከኋላ ፡ ኋላቸው ፡ ይከተላል ። ረባዳውን ፡ ጨርሰው ፡ ወደቤታቸው ፡ የሚያወጣውን ፡ ዳገት ፡ እንደጀመሩ ፡ እንደመቆም ፡ አሉና ፡ ዘርአይ ፡ ወደጐናቸው ፡ ሲጠጋ ፡ ቀኝ ፡ እጃቸውን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አደረጉበት ። መቸም ፡ ሸምገል ፡ እያሉ ፡ ሄደዋልና ፡ ደከሟቸው ፡ ሊደገፉት ፡ የፈለጉ ፡ መስሎት ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ትከሻውን ፡ አደላደለላቸው ። ትከሻውን ፡ በዚያ ፡ ረጅም ፡ መዳፋቸው ፡ ጨበጥ ፡ አድርገው ፡ ረጅም ፡ ናቸውና ፡ ጐንበስ ፡ ብለው ፡ ፊቱን ፡ ተመለከቱት ። « ዘርአይ ፡ እንግዲህ ፡ ኮ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ መሆንህ ፡ ነው ፡ » አሉት ።

ዘርአይ ፡ አልገባውም ። ባንድ ፡ ልቡም ፡ ጥርጣሬ ፡ አረደበት ። ዋ ! አቦይ ፡ ምን ፡ ሰምተው ፡ ይሆን ? ከዚያ ፡ ከሰፈሩ ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ልጃገረዶቹ ፡ ሊቀዱ ፡ ሲመጡ ፡ መረበሻችንን ፡ ነግረዋቸው ፡ ይሆን ? ግንኮ ፡ ለጨዋታና ፡ ለቀልድ ፡ ያህል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልሠራንም ። « አውቃለሁ ፡ » አለ ፡ ምን ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ እንዳለበት ፡ ጠፍቶት ።



« ሰምተሃል ፡ እንዴ ? » ሲሉ ፡ ደግመው ፡ ጠየቁት ።

« ምኑን ፡ »

« እየህ ፡ ሚስት ፡ ታጭቶልሃልና ፡ እንግዲህ ፡ ምራቁን ፡ የዋጠ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ መሆንህ ፡ ነው ። እንደልጅ ፡ ትሠራለህ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። እንዲያው ፡ ለነገሩ ፡ እንድታውቀው ፡ ያህል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ » አሁንም ፡ አዝማች ፡ አስገዶም ፡ አቁልቁለው ፡ የልጃቸውን ፡ ፊት ፡ ተመለከቱ ።

« አልሰማሁም ፡ አቦይ ፡ መቼ ? » ዘርአይ ፡ እንደማፈር ፡ ሲል ፡ አንገቱን ፡ አጐነበሰ ።

« የተጫጫችሁትማ ፡ ዱሮ ፡ ዱሮ ፡ ነው ፡ » አሉት ።

« ሕጻን ፡ ሳለሁ ? » ዘርአይ ፡ አባቱን ፡ የሚፈራበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። እንግዳ ፡ በቤት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ኮስተር ፡ ብለው ፡ ሲያዙት ፡ ከአንድ ፡ ሸንጎ ፡ ቆይተው ፡ እሳት ፡ ለብሰው ፡ እሣት ፡ ጐርሰው ፡ ሲመለሱ — ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የተወለደበት ፡ ማይበላ ፡ ወንዝ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ የቆረቆሯት ፡ አሉላ ፡ አባ ፡ ነጋ ፡ የተሰውላት ፡ ቀበሌ ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ ሰው ፡ ከተማ ፡ አድርጎ ፡ እንደቆረቆራት ፡ ሲያስቡ ፡ ጸጉራቸው ፡ ተንጨብርሮ ፡ ጅማታቸው ፡ ይገታተርና ፡ ዓይናቸውን ፡ ሲያጉረጠርጡበት ፡ መግቢያ ፡ ይጠፋዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እንደአባት ፡ ያቆላምጡታል ። እንደጓደኛ ፡ ይቃለዱታል ። ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ ስሜታቸውን ፡ ለመቅረብ ፡ ችሎ ፡ ነበር ። ደማቸው ፡ መፍላቱን ፡ ሲያውቅ ፡ ከአብራክ ፡ እንደወጣ ፡ ልጅ ፡ ሳይሆን ፡ እንደቤት ፡ አሽከር ፡ ይርበደ

በዳል ። አሁን ፡ ግን ፡ ደማቸው ፡ የሞቀ ፡ ቢሆን ፡ በደስታ
ስሜት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ መሆንህ
ነው ፡ ብለው ፡ አስተካክለውታል ። ዘርአይ ፡ መዝናናት
ተሰማው ። እኩል ፡ መቀለድም ፡ አማረው ። « እምምም
በሕጻንነቴ ፡ ከታጨሁ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ለምን ፡ አልነ
ሩኝም ? » አለ ፡ የፌዝ ፡ መሽኮርመም ፡ እየከጀለው ።

« በሕጻንነትህ ፡ አይደለም ። ገና ፡ ሳትወለድ ፡ ነው ።

« ዋ ፡ አቦይ ! ወንድ ፡ መሆኔን ፡ ገና ፡ በፊት ፡ ታውቅ ፡
ነበር ? » የዘርአይ ፡ አነጋገር ፡ ጥያቄ ፡ አልነበረም ።

« ሴት ፡ ወይም ፡ ወንድ ፡ መሆንክን ፡ ቀርቶ ፡ መወ
ለድህን ፡ አላውቅም ፡ ነበር ፡ » ሲሉ ፡ አዝማች ፡ አስገ
ዶም ፡ መለሱለት ። እንደገመተውም ፡ ደማቸው ፡ በደ
ህና ፡ ስሜት ፡ እንደሞቀ ፡ ነው ።

« ሴት ፡ ብሆን ፡ ኖሮስ ? ሴት ፡ ሚስት ፡ ያገባል ?»
ዘርአይ ፡ በፌዝ ፡ እንደመሳቅ ፡ አለ ።

« ሴት ፡ ብትሆን ፡ ኖሮማ ፡ ባል ፡ ታገባ ፡ ነበር ?» አጠ
ያየቁ ፡ አዝማችንም ፡ አሳቃቸው ።

« አሁን ፡ የታጨችልኝ ፡ ሴት ፡ አይደለችም ፡ እንዴ ?»

« አሁንማ ፡ ሴት ፡ ናት ፡ » ጭውውቱ ፡ አዝማ
ችን ፡ እየጣማቸው ፡ ሄደ ።

« በፊትስ ? » በነገሩ ፡ አካሄድ ፡ ሁለቱም ፡ ከት ፡
ከት ፡ ብለው ፡ ሳቁ ።



ከዚያም ፡ እጃቸውን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ ሳያነሱ ፡
ሁለቱም ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ወደቤታቸው ፡ እያዘገሙ ፡ ከአ
ዛዥ ፡ ዕቁባንክኤል ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እን
ደተጋቡ ፡ ተረኩለት ።

« ዛሬ ፡ እንዲህ ፡ ማይበላ ፡ ላይ ፡ ሊከትም ፡ » አዝ
ማች ፡ በጸጸት ፡ ራሳቸውን ፡ ነቀነቁ ። « ያን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡
ገና ፡ ምፅዋን ፡ ረግጦ ፡ መምጣቱ ፡ ነበርና ፡ ከአባነጋ ፡
አሉላ ፡ ጋር ፡ ደጎአሊ ፡ ላይ ፡ ውለን ፤ ጠላትን ፡ እንደዘን
ጋዳ ፡ ስንቆላው ፡ እንደ ፡ አዝመራ ፡ ስናጭደው ፡ ሬሣ ፡
ተትረፍርፎ ፡ እያደናቀፈ ፡ ሲጥል ፡ ቁስለኛ ፡ ማማ ፡ ውሃ ፡ እያለ ፡
ሲለምን ፡ እኔና ፡ አዛዥ ፡ ዕቁባ ፡ ንክኤል ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡
ሆነን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ስናራግበው ፡ ድንገት ፡ በጥይት ፡ ከታ
ፋዬ ፡ ላይ ፡ ቆስየ ፡ » ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጠባሳውን ፡ ያሳዩትን ፡
አሁንም ፡ ጐንበስ ፡ ብለው ፡ በዓይናቸው ፡ አመለከቱት ፡
«ድንገት ፡ ከፈረሴ ፡ ላይ ፡ ወደቅሁ ። ወዲያውም ፡ መድረሻ
ያጣ ፡ ሶልዳቶ ፡ ሸጉጡን ፡ ቀስሮ ፡ ወደኔ ፡ ሲገሰግስ ፡ አዛዥ
ሰይፉን ፡ መዞ ፡ እንደጦር ፡ ተወረወረና ፤ ሶልዳቶው ፡ በሽ
ጉጡ ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ ሲያቆስለው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አንገቱን ፡
በጥሶ ፡ ጣለው ። ወዲያው ፡ ድሉ ፡ ለይቶ ፡ ጐበዝ ፡ ምርኮ
ውን ፡ ሲጥል ፡ አዛዥ ፡ እኔን ፡ ተሸክሞ ፡ ከአንድ ፡ ጥላ ፡
ሥር ፡ አረፍን ። ደማችን ፡ ተቀላቅሎ ፡ የተጋደልንላትን ፡
መሬት ፡ ሲያርስ ፡ ሕይወቴን ፡ ላተረፈልኝ ፡ ውለታ ፡ ደማ
ችን ፡ ተቀላቅሎ ፡ ለፈሰሰላት ፡ መሬት ፡ መታሰቢያ ፡ ለዚ
ያች ፡ ቀን ፡ ድል ፡ ማስታወሻ ፤ ከእኛ ፡ ወዳጅነት ፡ እልፎ ፡
ልጆቻችን ፡ እንዲተሳሰሩ ፡ ሴት ፡ ብወልድ ፡ ለወንድ ፡
ልጁ ፡ ልሰጠው ፡ ሴት ፡ ቢወልድ ፡ ለልጄ ፡ ሊሰጠኝ ፡
ተማማልን ። »

አዝማች ፡ ሥዕሉ ፡ የሚታያቸው ፡ ይመስል ፡ ዙሪያ ፡ ገቡን ፡ አፍጥጠው ፡ እየተመለከቱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ ተራመዱ ። ቀጥሎም ፡ ፊታቸው ፡ በኀዘን ፡ ተኮማተረ ። ታሪካቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ቃላቸው ፡ ዜማ ፡ ነበረበት ። « ታዲያ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፤ በሰማይ ፡ ነፍሷን ፡ ይማርና ፡ ያች ፡ ደግ ፡ እናትህን ፡ እጭቼ ፡ ነበር ። አዛዥ ፡ ደግሞ ፡ የዘመተው ፡ ከሜጉላ ፡ ቤቱ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ እንደ አጋጣሚ ፡ አንተ ፡ ስትወለድ ፡ አዛዥም ፡ በመጀመርያ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ። ቀጥሎም ፡ ወንድ ፡ ሆነለት ። በመካከሉ ፡ በሰማይ ፡ ነፍሷን ፡ ይማርና ፡ እናትክን ፡ እርሱ ፡ እንደፈጠረ ፡ ጠራት ። በሶስተኛው ፡ ግን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለደችለት ። የምሥራቹን ፡ ልኮብኝ ፡ የአራስ ፡ ቤቱን ፡ ድግስ ፡ ስበላ ፡ ስንብቼ ፡ ተመለስኩ ። በሰማይ ፡ ነፍሱን ፡ ይማርና ፡ ልጁ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሳትደርስ ፡ አዛዥ ፡ ከጠላት ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ባደረበት ፡ ሕመም ፡ ተሰቃይቶ ፡ ሞተ ። ግን ፡ በዚያች ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ የተማማልናትን ፡ ተናዞ ፡ ነበር » ንግግራቸውን ፡ ሲጨርሱ ፡ በሰፊው ፡ ተንፈሱ ።

ዘርአይ ፡ ሰውነቱ ፡ ሲኮማተርና ፡ ዓይኖቹ ፡ ዕንባ ፡ ሲቋጥሩ ፡ ተሰማው ። መልካቸውንና ፡ ፍቅራቸውን ፡ የማያውቀው ፡ እናቱ ፡ አዲስ ፡ ሹርባ ፡ ተሠርተው ፡ በሐሳቡ ፡ መጡበት ። አባቱ ፡ ስለእናቱ ፡ ብዙም ፡ አውርተውለት ፡ አያውቁም ። ድንገት ፡ ሲጠይቃቸው ፡ ፊታቸውን ፡ ዘወር ፡ አድርገው ፡ ሌላ ፡ ጨዋታ ፡ ያመጣሉ—ሌላ ፡ ሚስት ፡ ያላገቡት ፡ እናቴን ፡ ስለሚወዱ ፡ እኔም ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፡ እጅ ፡ እንዳላይ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ከወደዱዋቸውም ፡ እናቴ ፡ ውብ ፡ ነበሩ ፡ ማለት ፡ ነው—ሲል ፡ አሰበ ። ለአዛዥ ፡ ዕቁባ—እንኪልም ፡ አዘነላቸው ። የተመኙት ፡ ነገር ፡



ሳይፈጸም ፡ ለምን ፡ ወሰዳቸው ? እናቴ ፡ ውብ ፡ ነበረች ፡ አማቼም ፡ ጀግና ፡ ነበሩ—አለ ፡ በሆዱ ።

አዝማች ፡ አስጎዶም ፡ መዳፋቸውን ፡ ከልጃቸው ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ሳያነሱ ፡ እንደ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ሳይሆን ፡ እንደባልንጀራ ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ እየተራመዱ ፡ ከቤታቸው ፡ ደረሱ ። ቀርስ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ አሽከሮችን ፡ ለማዘዝ ፡ ዘርአይ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወደጓዳ ፡ ገባ ።

አዝማች ፡ አስገዶም ፡ ፍጥምጥሙን ፡ የፈጸሙት ፡ ለልጃቸው ፡ ከመንገራቸው ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ በፊት ፡ ነበር ። የወዲያኛው ፡ ዓርብ ፡ ለት ፡ ብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ አለብኝ ፡ ብለው ፡ ለአዳር ፡ ወደ ፡ አዲ ፡ ቀይሀ ፡ መሔዳቸው ፡ ትውስ ፡ አለው ። የአክስቱ ፡ ባል ፡ ሁለት ፡ የመንደር ፡ አዛውንቶች ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ አብረዋቸው ፡ ሄደው ፡ ነበር ።

ከዚያም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለልጅቷ ፡ እንደአባትም ፡ እንደ ፡ ሞግዚትም ፡ በሆኑት ፡ በአዛዥ ፡ ዕቁባንክኤል ፡ ትልቁ ፡ ወንድም ፡ ቤት ፡ ተፈጸመ ። አዲቀይሕ ፡ ከሌላ ፡ ቤት ፡ ሲያድሩ ፡ ማምሻውን ፡ በመላከተኛ ፡ አስታውቀው ፡ ኖሮ ፡ ቅዳሚ ፡ ጧት ፡ ሲደርሱ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ ተሰናድቶ፡ ጠበቃቸው ።

ቆመዉ ፡ ተቀበሏቸውና ፡ ሲቀመጡ ፡ የወንድ ፡ ወገኖች ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ቀሩ ።

« ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ቆማችሁ ? » ሲሉ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ጠየቁ ።

« እንደ ፡ ዋርካ ፡ ተንሰራርተን ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡ ሰፍተን ፡ እንደወንዝ ፡ ረዝመን ፡ እንደጋራ ፡ ደርጅተን ፡ ልታ

ስጡትን ፡ መጠጊያ ፡ ልትሆኑን ፡ ብለን ፡ ከትልቁ ፡ ከጀግናው ፡ ሰባጋዲስ ፡ ትውልድ ፤ ከታወቀው ፡ ስብሐት ፡ ከሹም ፡ አጋመኩመሌት ፡ ሹም ፡ አጋመኩመሌት ፡ ቢወልዱ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ አምላክን ፤ ከዚያም ፡ እነደጊያት እንግዳ ፡ የእነአውራሪስ ፡ ሀረጐትን ፡ ትልቁን ፡ ዘር ፡ የደቂ ፡ ሐርሽን ፡ ዛፍና ፡ ጥላ ፡ መርጠን ፡ የአዛዥ ፡ ዕቁባንክኤልን ፡ ቤት ፡ ፈልገን ፡ ልጅ ፡ ልታደርጉን ፡ ብለን ፡ ቁመናል ፡ » ሲሉ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ጠየቁ ።

የሴት ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ በበኩላቸው ፡ ተነሱ ። « እናንተስ ፡ ብትሆኑ ፡ የስመጥሩ ፡ ደቂ ፡ ለዋይ ፡ አይደላችሁም ? የስመጥሩ ፡ የገብረየስ ፡ ልጅ ፡ የተስፋንክኤል ፡ የስመራ ፡ ልጅ ፡ ከንቲባ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የከንቲባ ፡ ነጋሲ ፡ የደቂ ፡ ዓንደላይ ፡ የነይስሐቅ ፡ የነተስፈገርጊስ ፡ ልጆች ፡ አይደለችሁም ? አዝማች ፡ አስገዶም ፡ እንደዋርካ ፡ ተንሰራርታችሁ ፡ እንደሜዳ ፡ ሰፍታችሁ ፤ እንደወንዝ ፡ ረዝማችሁ ፡ እንደጋራ ፡ መጠጊያችንን ፡ ስትፈልጉ ፡ እንቀበላችላን ፡ እንጅ ፡ » አሉ ።

እንግዶቹ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ከተጋበዙ ፡ በኋላ ፡ ጥሎሹን ፡ ተጠየቁ ። ለሙሽራይቱ ፡ ጥለቱ ፡ የደመቀ ፡ ጥልፉ ፡ የተንቦገቦገ ፡ ሁለት ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ጉትቻው ፡ አልቦው ፡ አሸን ፡ ክታቡ ፡ አምባሩ ፡ መቀነቱ ፡ ወለባው ፡ ተሰጠ ። አጎትየው ፡ አጀጠባብና ፡ ሱሪ ፤ አንድ ፡ ጋቢ ፡ አንድ ፡ ጐራዴ ፡ ከነጋሻው ፡ ቀረበላቸው ። አስር ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ ተቆጥሮ ፡ ተጣለ ።

«ምነዋ ! ምነዋ !» አሉ ፡ የሴት ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ። «ምንስ ፡ ቢሆን ፡ የሰባጋዲስ ፡ የስብሐት ፡ የአጋመኩመሌት



የፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፡ የእነአውራሪስ ፡ ሐረጎት ፡ የጀግናው ፡ የቁባንክኤል ፡ ልጅ፡ የደቂ ፡ ሐርሽን ፡ ዋርካ ፡ ናት ። እንደክብርዋ ፡ አክብሯት ። »

« እንደ ፡ ከበሬታዋ ፡ እናከብራለን ። ይኸው ፡ ደግሞ» ብለው ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ጭማሪ ፡ ጥሎሽ ፡ አቀረቡ ። ለአጎትየው ፡ ባለቤት ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ለሙሽራይቱ ፡ የተጠለፈ ፡ ልብ ፡ አልማ ፡ ነበር ። በብቃቱ፡ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ ተስማሙ ።

« ማደሪያዋስ ? » ሲሉ ፡ የወንድ ፡ ወገን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ዓይናቸውን ፡ ወደ ፡ አጎትየው ፡ አተኩረው ፡ ጠየቁ ።

አጎትየው ፡ ለአፈጉባኤው ፡ ሹክ ፡ አሉ ። አፈጉባኤው ፡ « አስር ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ አምስት ፡ የጋማ ፡ ከብት ፡ መቶ ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ » ሲሉ ፡ መለሱ ።

የወንድ ፡ ወገኖች ፡ ራሳቸውን ፡ በቅሬታ ፡ ነቀነቁ ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ የሰባጋዲስ፡ የስብሐት ፡ የሹም ፡ አጋመኩመሌት ፡ የዕቁባንክኤል ፡ ልጅ ፡ ናት ። እኛም ፡ የከንቲባ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወገኖች ፡ ነን ። አይበቃም ፡ አሉ ። አምስት ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ሶስት ፡ የጋማ ፡ ከብት ፡ አስር ፡ በግ ፡ አስራ ፡ አምስት ፡ ፍየል ፡ ሶስት ፡ ጭነት ፡ ጨው ፡ ተጨመረላቸው ። በቃን ፡ ብለው ፡ ተስማሙ ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሙሽራይቱ ፡ አዲሱን ፡ የጥሎሽ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ጌጣ ፡ ጌጡን ፡ አድርጋ ፡ ወጣችና ፡ አባቷን ፡ ስማ ፡ ተመርቃ ፡ ተመለሰች ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ቀረበ ። ፍጥምጥሙ ፡ የተፈጸመው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነበር ።

በዓመቱ ፡ የሠርጉ ፡ ለት ፡ ዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ሲቃረብ ፣ ሚዜዎቹ ፡ እየተሯሯጡና ፡ እየተተራመሱ ፣ ሜጉላ ፡ ቤቱ ፡ ተጋርዶና ፡ ተከቦ ፣ የሙሽሪትን ፡ እሪታ ፡ በጭብጨባ ፡ በሆታና ፡ በጩኸት ፡ ለመዋጥ ፡ ዘፈኑ ፡ ድብልቅልቁ ፡ ወጣ ። ግን ፡ መዳፉ ፡ እስኪጎርብ ፡ የሚያጨበጭበውም ፣ አንገቱ ፡ እስኪበጠስ ፡ እስክስታ ፡ የወረደውም ፣ ላንቃው ፡ እስኪሰነጠቅ ፡ የሚያቀነቅነውም ፡ ጆሮውን ፡ አንቅቶ ፡ ያዳምጥ ፡ ነበር ። መብረቅ ፡ ቢጮህ ፣ ነጐድጓድ ፡ ቢያስተጋባ ፣ የዘፈኑ ፡ ጩኸት ፡ ሰማይና ፡ ምድሩን ፡ የሚያናጋው ፡ ቢመስል ፣ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ሞትን ፡ እንደሚጠራ ፡ ጦር ፡ በቀጭኑ ፡ የሚወረወረው ፡ የልጃ ፡ ገረድ ፡ ኡኡታ ፡ ተለይቶ ፡ ይታወቃል ። አንዱ ፡ ቢስት ፡ ከሌላው ፡ ጆሮ ፡ አያመልጥም ።

ጭፋሮው ፡ ገልቱን ፡ ሳይቀንስ ፡ ቀጠለ ። ያ ፡ የሚጠበቀው ፡ ኡኡታ ፡ ግን ፡ አልተሰማም ። ዶሮ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲጮህ ፡ ጨፋሪ ፡ መድከም ፡ ጀመረ ። ሌሎችም ፡ በጥያቄ ፡ መልክ ፡ እርስበርሳቸው ፡ መተያየቱና ፡ ፀጉራቸውን ፡ ማከክ ፡ ጀመሩ ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ መቆየት ፡ ለደግ ፡ አይደለም ።

የራሱና ፡ የግር ፡ ሚዜዎች ፡ ተከታትለው ፡ ወደጫጉላው ፡ ቤት ፡ ገቡ ። ጭፈራው ፡ ጋብ ፡ ብሎ ፡ ሁሉም ፡ ዓይኑን ፡ ወደጫጉላ ፡ ቤት ፡ ወረወረ ። አዝማች ፡ አስገዶም ፣ ደህና ፡ በመፈጸሙ ፡ ተደስተው ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ መካከል ፡ ተዝናንተው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ጥርጣሬ ፡ ገብቷቸው ፣ እርሳቸውም ፡ ጥርጣሬ ፡ አድሮባቸው ፡ ሰውነታቸው ፡ ከውስጥ ፡ እየተሸማቀቀ ፣ ትንፋሻቸው ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይል ፡ ገባ ። በአ



ጠገባቸው ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፣ ሆነ ፡ ብለው ፣ ጥርጣሬአቸውን ፡ እያሳወቁ ፡ የማያውቁ ፡ በመምሰል ፡ የሚያቀርቡት ፡ ጨዋታ ፡ ሁሉ ፡ አልተሰማቸውም ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሚዜዎቹ ፡ ተመልሰው ፡ ወጡ ። ምልክቱን ፡ ግን ፡ አልያዙም ። ሁሉም ፡ አፉን ፡ እንደከፈተ ፡ ቀረ ። አጃቢዎቹና ፡ ሌሎችም ፡ ጥቂቶች ፣ ጭፋሮውን ፡ በማድመቅ ፡ የሰፈነውን ፡ ጥርጣሬ ፡ ለማወናበድ ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ግን ፡ አልሆነም ። ምንም ፡ ያህል ፡ ቢጨፈር ፣ ሶስቱ ፡ ሚዜዎች ፡ ፊታቸው ፡ ከሰል ፡ መስሎ ፡ ሳለማስመሰል ፡ ጥርሳቸውን ፡ አግጥጠው ፣ አዝማች ፡ አስገዶምን ፡ በዓይኖቻቸው ፡ ጠቅሰው ፡ ወደአልፍኝ ፡ ሲያመሩ ፡ የሁሉም ፡ ዓይን ፡ ተከተላቸው ።

አዝማች ፡ አስገዶም ፡ በመጀመርያ ፡ የተጠራጠሩት ፡ ልጃቸውን ፡ ነበር ። እርግጥ ፡ እስከሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቢቆጠር ፡ እንኳ ፡ በዘር ፡ ማንዝራቸው ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ጉድለት ፡ አይገኝም ። ለሐሜት ፡ ፍንጭ ፡ ያልሰጡ ፡ የጐበዝ ፣ የጀግና ፡ የወንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ። የወንድ ፡ ወንድ ዘር ፡ ናቸው ። ግን ፡ ድክሙም ፣ ኃፍረቱም ፡ ድንጋጤውም ፣ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ስጋት ፡ አድሮባቸው ፡ ነበር ።

ሚዜዎቹ ፡ ሲነግሯቸው ፡ ግን ፣ ጆሮዋቸውንም ፡ እነሱንም ፡ ማመን ፡ አቃታቸው ። ልጃቸው ፡ ድርሻውን ፡ ግዳጁን ፡ ፈጽሞአል ። ግን ፡ ሙሽሪት ፣ የክብር ፡ ምልክት ፣ የሥርየት ፣ ፡ የፍኖተ ፡ መስቀል ፡ ምልክት ፡ የሆነ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ አልተገኘባትም ።

ደጋና ፡ ቆላ ፡ ያልተመላለሱበትን ፣ ጦር ፡ ሜዳ ያልዋሉበትን ፣ ታግለው ፡ ያልጣሉበትን ፡ ያህል ፡ ያ ፡

በከፉና ፡ በደግ ፡ ቀን ፤ በሐሩርና ፡ በቁር ፡ የደነደነው ፡ አጥንታቸው ፡ ድንገት ፡ ከውስጥ ፡ የሚሸሽ ፡ ይመስል ፤ አዝማች ፡ አስገዶም ፤ እንደመፃጉዕ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ድጋፍ ፡ እየፈለጉ ፤ ከቆሙበት ፡ ሽብረክ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ። ከዚያም ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ደግፈው ፤ ዓይናቸውን ፡ አፍጥጠው ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ እንደ በድን ፡ ሆነው ፡ ቆዩ ። ድንጋጤ ፡ አልነበረም ። በሕይወተ ፡ ሥጋ ፤ ወይም ፡ በእውን ፡ ሕልውና ፡ ሊታመን ፡ ወደማይቻል ፡ የሕልም ፡ ዓለም ፡ ውሰጥ ፡ መግባት ፡ ነበር ። የሚያውቁት ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ተከንብሎ ፤ ጭልጥ ፡ ወደአለ ፡ ቀዝቃዛ ፡ የሲኦል ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። ምንም ፡ ማሰብ ፡ ማየት ፡ አልቻሉም ። እንደገና ፡ ወደእውንት ፡ ዓለም ፡ ሲመለሱ ፤ ከእንቅልፋ ፡ እንደባነነ ፡ ሰው ፡ ዓይናቸውን ፡ እያንከራተቱ ፡ በዙሪያቸው ፡ የቆሙትን ፡ ሚዜዎቹና ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶች ፡ ተመለከቱ ። እንደመማጠን ፡ ዓይነት ፡ ነበር ።

« ታዲያ ፡ መቸስ ፡ ጉድለቱ ፡ ከኛ ፡ በኩል ፡ አይደል ። » ብሎ ፡ አንደኛው ፡ ሚዜ ፡ ንግግሩን ፡ ሳይጨርስ ፡ አዝማች ፡ እጃቸውን ፡ በማወራጨት ፡ አቋረጡትና ፤ «ተው ! ሌላ ፡ ቃል ፡ አትናገር ። ደሜን ፡ እንዳታስቆጣ ! በእኛ ፡ በኩል ? ማነን ፡ እኛ ? እቁባንክኤል ፡ ከሁላችሁም ፡ ይቀርብኝ ፡ ነበር ። ምን ፡ መቅረብ ፡ ብቻ ! ኧረ ፡ አንድ ፡ ነበርን ! » አሉ ። እንደ ፡ ዕብድም ፡ ጥርሳቸውን ፡ አፋጩ ። እንደገናም ፡ ተመልሰው ፡ ወደሰመመን ፡ ዓለም ፡ ገቡ ። በዚህ ፡ ላይ ፡ በሥራ ፡ ደከመው ፡ ሰንብተው ፡ ነበርና ፡ አዲስ ፡ የመጣውን ፡ የፈረንጅ ፡ ነጭ ፡ አረቂ ፡ አስጐንጭተው ፡ ከመደብ ፡ ላይ ፡ አጋደሙዋቸው ። ከዚያ ፡ ዕንቅልፍ ፡ ጭልጥ ፡ አድርጎ ፡ ወሰዳቸው ።



ከንጋቱ ፡ ላይ ፡ ከንቅልፋቸው ፡ ሲነቁ ፡ ትንሽ ፡ ተረጋግተው ፡ ነበር ። መንቃታቸውን ፡ ሲያውቁ ፡ ሚዜዎችና ፡ ቁርጠኛ ፡ ዘመዶች ፡ ተጠራርተው ፡ በዙሪያቸው ፡ ተሰበሰቡ ። ከዚያም ፡ አዝማች ፡ ከአንድ ፡ በኩል ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ሲማከሩ ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ ሲነታረኩ ፡ አረፈዱ ። እንደ ፡ አዝማች ፡ አስተያየት ፡ ምንም ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ የለበትም ። አንድ ፡ ቀርቶ ፡ ለምን ፡ አስር ፡ ሕግ ፡ አይታጣም ! እርግጥ ፡ ያሳዝናል ። ግን ፡ ለእቁባንክኤል ፡ ውለታ ፡ ይኸም ፡ ሲያንሰው ፡ ነው ። ቤተ ፡ ሰብ ፤ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ደግሞ ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ አፍ ፡ አንድ ፡ ስሜት ፡ ሆኖ ፡ በነገር ፡ በቁጣ ፡ ፍጥርቅ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ።

« ፈጽሞ ፡ የማይታሰበውን ! » አሉ ፡ አንዱ ፡

« መታሰብ ፡ ቀርቶ ፡ የማይታለመውን ! »

« ዕቁባንኬል ፡ ባለውለታህ ፡ ቢሆን ፡ ውለታውን ፡ በዚያው ፡ በክብር ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ መልሰለት ፡ እንጂ ፡ ገናናውን ፡ ስማችንን ፡ በማዋረድ ፡ [illegible] ! » አሉ ፡ አንደኛው ፡ የአጎታቸው ፡ ልጅ ። [illegible] ፡ ጥጥ ፡ የመሰለው ፡ አጎታቸውማ ፡ ሰውነታቸው ፡ በንዴት ፡ እየተንዘፈዘፈ ፡ « አንተ ፡ ብትወልደው ፡ ዘርአይ ፡ ለኔም ፡ ልጄ ፡ ነው ። ከነውር ፡ ላይ ፡ ልትጥለው ፡ አስበሃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ምስክሬ ፡ ነገ ፡ እፋለምሃለሁ ። በጥንቱ ፡ በጦር ፡ በጋሻ ፡ በአዲሱ ፡ በጠመንጃ ፡ መሣሪያህን ፡ ምረጥ ! » ሲሉ ፡ ከልባቸው ፡ ፎከሩ ።

ጦር ፡ መወርወር ፡ ጐራዴ ፡ መምዘዝ ፡ የማይችሉት ፡ ሴት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ደግሞ ፤ በዚያው ፡ ባላቸው ፡ ኃይል ፡ « ከመቃብርህ ፡ አያውለን ። ከመቃብራችን ፡ አያው

ልህ ። እሷን ፡ ቀርቶ ፡ የርሱን ፡ ፊት ፡ በከፉም ፡ በደግም ፡ አናይም ፡ » ሲሉ ፡ ተገዘቱባቸው ።

አዝማች ፡ አስገዶም ፡ አገጫቸውን ፡ በሁለት ፡ መዳፋቸው ፡ መካከል ፡ ቀብረው ፡ አይናቸውን ፡ አፍጥጠው ፡ ወለል ፡ ወለሉን ፡ እያዩ ፡ በታከተ ፡ ሁናቴ ፡ የሁሉንም ፡ ነገር ፡ አዳመጡ ። በመጨረሻም ፡ « ዋ ! አላምንም ። ፈጽሞ ፡ አላምንም ! » ሲሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ነቅነቁና ፡ ለማመን ፡ የማይፈልጉት ፡ ነገር ፡ ደርሶም ፡ እንደሆን ፡ በተአምር ፡ ወደጥንቱ ፡ ይመለስላቸው ፡ ይመስል ፡ «ዋ! አንተ ፡ ፈጣሪ ፡ እንታይ ፡ ገበርኩ ፡ ዋ ፡ አንተ ፡ ኤሎሄ ፡ ለማ ፡ ሰበቅታኒ ፡ » ብለው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠጡ ። ቤተ ፡ ዘመዶቻቸውም ፡ የመንፈሳቸውን ፡ መጨነቅ ፡ ተመልክተው ፡ አዘኑላቸው ። ከንፈራቸውን ፡ በመምጠጥ ፡ ራሳቸውን ፡ በመነቅነቅ ፡ ፊታቸውን ፡ በመጨፍገግ ፡ አስተዛዘኑዋቸው ።

አዝማች ፡ ማመን ፡ ስላለፈለጉ ፡ ማመን ፡ አቅቷቸው ፡ « ለመሆኑ ፡ ነገሩ ፡ እርግጥ ፡ ለመሆኑ ፡ እርግጠኞች ፡ ናችሁ ፡ ? » ሲሉ ፡ አሁንም ፡ እንደገና ፡ ጠየቁ ።

« እርግጠኞችስ ፡ ነን ። ግን ፡ ደግሞ ፡ ደግመን ፡ ማረጋገጥ ፡ እንችላለን ፡ » ሲሉ ፡ አንዱ ፡ ሚዜ ፡ መለሰላቸው ።

ምርመራውን ፡ የሚያጣሩት ፡ ሁለት ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ባልቴቶች ፡ ተመረጡና ፡ ወደ ፡ ጫጉላ ፡ ቤቱ ፡ ተላኩ ። ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ከተሰበሰቡበት ፡ እልፍኝ ፡ ሲጠብቁ ፡ ቆዩ ። ባልቴቶቹ ፡ ከአሩብ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ መጡ ። ከአንደበታቸው ፡ የሚወጣውን ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ አላስፈለገም ። መልሱ ፡ ከፊታቸው ፡ በጉልህ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ።



« እንደፈለጋችሁ ፡ አድርጉ ። እኔ ፡ ከደሙ ፡ ከደማችሁ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ » አሉ ፡ አዝማች ፡ አስገዶም ፡ ተስፋ ፡ በቆረጠ ፡ አንደበት ። ገና ፡ ተናግረው ፡ ሳይጨርሱ ፡ ቤተ ዘመዶቹ ፡ ስብሰባውን ፡ በትነው ፡ በየበኩላቸው ፡ ይጣደፉ ፡ ጀመር ። አንዱ ፡ አህያዋን ፡ ከጎረቤት ፡ በረት ፡ አመጣ ። ሌላው ፡ አሮጌ ፡ በርኖስ ፡ ከየትም ፡ ይዞ ፡ መጣ ። ሶስተኛው ፡ በሁለት ፡ ጎረምሶች ፡ እየተረዳ ፡ የሙሽራይቱን ፡ ጸጉር ፡ በደረቁ ፡ ለመላጨት ፡ ወደጫጉላ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ዘርአይ ፡ ወጣና ፡ አባቱ ፡ ወደተቀመጡበት ፡ እልፍኝ ፡ ሄደና ፡ ከጎናቸው ፡ ተቀመጠ ። ዓይን ፡ ላይን ፡ በሙሉ ፡ ለመተያየት ፡ የተፈራሩና ፡ የተፋፈሩ ፡ ይመስል ፡ ሁለቱም ፡ አንገታቸውን ፡ አቀርቅረው ፡ ላንዳፍታ ፡ በጎሪጥ ፡ ተሰራረቁ ። አዝማች ፡ ሣር ፡ ቢጤ ፡ አነሱና ፡ ወለሉን ፡ ይጫጭሩ ፡ ጀመር ። አልተነጋገሩም ። በየበኩላቸው አንዱ ፡ በሌላው ፡ አእምሮ ፡ የሚመላለሰውን ፡ ሐሳብና ፡ ጭንቀት ፡ ለመረዳት ፡ ይሞክሩ ፡ ነበር ።

«ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተደራጅቷል ፡ » አለ ፡ አንደኛው ፡ ሚዜ ፡ መጥቶ ።

« እንደፈለጋችሁኮ ፡ አልኳችሁ ! » አሉ ፡ አዝማች ፡ ከአቀረቀሩበት ፡ ዓይናቸውን ፡ ቀና ፡ ሳያደርጉ ።

ከውጭ ፡ ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ ተከማችቶ ፡ ቁሞ ፡ የአህያቱን ፡ አገጭ ፡ ለልጓም ፡ እንደሚረዳ ፡ ያህል ፡ በገመድ ፡ ሸብበው ፡ በጀርባዋ ፡ ላይ ፡ አሮጌ ፡ አጐዛ ፡ ጣል ፡ አድርገው ፡ ጸጉሯን ፡ በደረቁ ፡ ተላጭታ ፡ በርኖስ ፡ የለበሰችውን ፡ ሙሽሪት ፡ አሳፈርዋት ። ትናንት ፡ የደመቀ ፡ ሠርግ ፡ የነበረበት ፡ ግቢ ፡ የሀዘን ፡ ቤት ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ሁሉም ፡ ፊቱን ፡ ጨፍግጎ ፡ አርምሟል ። አድምሟል ፡ ዋናዋ ፡ ኀዘንተኛም ፡ ሙሽራይቱ ፡ ነበረች ። ግን ፡ ዕንባ ፡ አውጥታ ፡ አላለቀሰችም ። ስሜቷ ፡ ከዕንባ ፡ በላይ ፡ ነበር ።

ሙሽራ ፡ የተሜነችው ፡ ሌጣ ፡ አህያ ፡ ወሽ ! ተብላ ፡ ተነድታ ፡ ግቢውን ፡ ስትወጣ ፡ ብዙዎቹ ፡ ከንፈራቸውን ፡ እየመጠጡ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። አዝማች ፡ ተግባሩ ፡ መከናወኑን ፡ ሲያውቁ ፡ አላስችላቸው ፡ አለና ፡ ተነስ ተው ፡ ወጡ ። ዘርአይም ፡ ከኋላ ፡ ተከተላቸው ። ቀኝ ፡ መዳፋቸውን ፡ ከደረታቸው ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አደረጉና ፡ በአ ሻገር ፡ ተመለከቱ ። የኑሮ ፡ መብራቷ ፡ ጠፍቶ ፡ የት ፡ እን ደምትሔድ ፡ የማታወቀው ፡ ሙሽሪት ፤ ቁልቁለቱን ፡ ዘልቃ ፡ ረባዳውን ፡ መሬት ፡ ተያይዛዋለች ። ከፍርሃትና ፡ ከጭንቀት ፡ የተነሣ ፡ የገመዱን ፡ ልጓም ፡ ጨምድዳ ፡ የያ ዘች ፡ ይመስላል ። በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ብቻዋን ፡ እንደ ቀረችው ፡ ሂሩት ፡ ትመስላለች ። አዝማች ፡ ብቸኝነቷ ፡ ተሰማቸው ። ራሳቸውም ፡ የበለጠ ፡ ብቸኝነት ፡ ተሰማ ቸው ። ሰውነታቸው ፡ ተኮማተረ ። «እቁባንክኤል ፡ ይቅር ፡ ትለኛለህ? የለም ። ይቅር ፡ በለኝ ፡ ብዬስ ፡ አልጠይቅህም ፡ ትታዘበኛለህ ። እንዳሻህ ! ዋ ! አንተ ፡ ፈጣሪ ፡ እንታይ ሞ ፡ ገበርኩሃ ! አንተ ፡ ኢሎሄ ፡ ለማ ፡ ሰበቅታኒ ፡» አሉ ና ፡ ዓይናቸውን ፡ ዕንባ ፡ እስኪሸፍነው ፡ ድረስ ፡ በዚ ያች ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ አፍጥጠው ፡ ቀረ ።

(ይቀጥላል)